
IslamHouse.com
مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com
Rabwah



Amharic
አማርኛ
أمهري

# الفرائض في الإسلام

# እስላማዊ የውርስ ህግጋት

ዝግጅት፡
ሐቢብ አሕመድ
እርማት፡
ሼኽ ጀማል ሙሀመድ

# الفـــرائض في الإسلام

مركز أصول
مراجعة
الداعية جمال محمد أحمد

Amharic
አማርኛ
أمهري

**ح جمعية الدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالربوة، ١٤٤٢هـ**

**فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر**

مركز أصول

الفرائض في الإسلام – اللغة الأمهرية. / مركز أصول - ط١.- الرياض، ١٤٤٢هـ

٩٢ ص، ١٤ سم x ٢١ سم

ردمك : ٩٧٨-٦٠٣-٨٣٢٣-٣١-١

١- المواريث   أ. العنوان

**ديوي ٢٥٣,٩٠١   ١٤٤٢/٢٦٩٨**

**رقم الايداع: ١٤٤٢/٢٦٩٨**

**ردمك : ٩٧٨-٦٠٣-٨٣٢٣-٣١-١**

This book is the property of the Osoul Center. Permission is granted for it to be stored, transmitted, and published in any print, electronic, or other format - as long as the Osoul Center is clearly mentioned on all editions, no changes are made without the express permission of the Osoul Center, and a high level of quality is maintained.

+966 11 445 4900

+966 11 497 0126

P.O.BOX 29465 Riyadh 11457

osoul@rabwah.sa

www.osoulcenter.com

بسم الله الرحمن الرحيم

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ
እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው



# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 9 |
| 2 | ዘርፉ በእስላም ያለው ቦታ | 9 |
| 3 | ውርስን አስመልክቶ ማወቅ ያለብን አበይት ነጥቦች | 11 |
| 4 | የውርስ ምክኒያቶች | 12 |
| 5 | ውርስን ክልክል የምያደርጉ ነገሮች | 13 |
| 6 | ከህዴት (ኩፍር) | 14 |
| 7 | ግድያ | 14 |
| 8 | ባሪያ መሆን | 14 |
| 9 | ዝሙት | 15 |
| 10 | ሊዓን (መረጋገም) | 15 |
| 11 | ስወለድ ድምጽ አልባ የሆነ ህፃን/ ሙቶ ተወለደ | 15 |
| 12 | የውርስ መስፈርቶች /ሸርጦች/ | 16 |
| 13 | ወንድ ወራሾች | 16 |
| 14 | ሴት ወራሾች | 17 |
| 15 | ዙፈርድ ብቻ ሆነው የምወርሱ | 19 |
| 16 | ዐሰባህ ብቻ ሆነው የምወርሱ (ብቻቸውን ሲሆኑ ጨርሰው የምወርሱ) | 20 |
| 17 | ዙፈርድ እና ዐሰባህ ሆነው የምወርሱ ነገር ግን በአንድ ጊዜ ሁለቱንም መሆን ፈጽሞ የማይችሉ | 20 |
| 18 | በቁርኣን የተደነገጉ ድርሻዎች | 21 |
| 19 | ግማሽ የምወርሱ | 21 |
| 20 | ባል | 22 |
| 21 | ሴት ልጅ | 22 |
| 22 | የወንድ ልጅ ሴት ልጅ | 22 |
| 23 | እህት (በሁለቱም በኩል) | 23 |
| 24 | እህት በአባት በኩል | 23 |
| 25 | ሩብ (1/4) የምወርሱ | 24 |
| 26 | ባል | 24 |
| 27 | ምስት | 24 |
| 28 | አንድ ስምንተኛ የምወርሱ | 25 |
| 29 | ሁለት ሦስተኛ የምወርሱ | 25 |
| 30 | ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የሟች ሴት ልጆች | 26 |
| 31 | ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የወንድ ልጅ ሴት ልጆች | 26 |
| 32 | ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ እህቶች (በሁለቱም በኩል እህት የሆኑ) | 27 |
| 33 | እህቶች (በአባት በኩል) | 27 |

| | | |
|---|---|---|
| 34 | አንድ ሦስተኛ (1/3) የምወርሱ | 28 |
| 35 | በእናት በኩል ብቻ ወንድም /እህት/ የሆኑ እና ቁጥራቸው ሁለት እና ከዝያ በላይ የሆኑ | 28 |
| 36 | ሱሉሱል ባቂ (ቀሪ አንድ ሦስተኛ) የምወርሱ | 29 |
| 37 | አንድ ስድስተኛ የምወርሱ | 29 |
| 38 | አባት | 30 |
| 39 | እናት | 30 |
| 40 | ወንድ አያት | 31 |
| 41 | ሴት አያት | 31 |
| 42 | አንድ ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የወንድ ልጅ ሴት ልጆች | 32 |
| 43 | እህት (በአባት በኩል) | 32 |
| 44 | የእናት ልጅ (በእናት በኩል ብቻ ወንድም /እህት/ የሆነ/ች) | 33 |
| 45 | ዐሰባህ /ያለገደብ የምወርሱ/ | 33 |
| 46 | ሀ- ለብቻቸው ጨርሰው የምወርሱ | 33 |
| 47 | ለ- በሌላ ሰው ምክኒያት ጨርሰው የምወርሱ | 35 |
| 48 | ሐ- ከሌሎች ጋር በመሆን ጨርሰው የምወርሱ | 35 |
| 49 | እገዳ (ሑጅብ) | 36 |
| 50 | ሑጅቡ ሑርማን /ሙሉ በሙሉ ማገድ/ | 36 |
| 51 | ሑጅቡ-ነቅስ /በከፊል ማገድ/ | 37 |
| 52 | ሽርከና /መጋራት/ | 39 |
| 53 | የአያት እና የወንድሞች/የእህቶች/ አወራረስ | 40 |
| 54 | አል-አክደሪያህ /ተወሳሳቢ/ | 42 |
| 55 | የውርስ ድርሻን ማስተካከል /ተስሒሑል ፈራእድ/ | 43 |
| 56 | ዐውል | 45 |
| 57 | አመዳደብ | 48 |
| 58 | አራቱ ምልከታዎች | 49 |
| 59 | መመሳሰል (አት-ተማሱል) | 49 |
| 60 | አንዱ በአንዱ ውስጥ መገኘት /መግባት/ (አት-ተዳኹል) | 50 |
| 61 | መስማማት (አት-ተዋፉቅ) | 50 |
| 62 | መለያየት /አለመስማማት/ አት-ተኻሉፍ/ | 52 |
| 63 | የማይካፈል ሲሆን (አል-እንክሳር) | 52 |
| 64 | እንክሳር በሁለት ወገኖች ላይ ሲሆን እና በወራሾች መካከል መመሳሳል ሲኖር | 55 |
| 65 | እንክሳር በሦስት ወገኖች ላይ ስገኝ እና ተዳኹል እና ተኻሉፍ የምባሉት አሰራሮች ሥራ ላይ ስውሉ | 57 |
| 66 | እንክሳር በአራት ወገኖች ላይ ሲሆን እና መስማማት ስኖር | 58 |
| 67 | መለያየት እና ምሳለው | 59 |
| 68 | ሽረት (አልሙናሰኻ) | 60 |

# መግቢያ

ምስጋና ለዐለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፤ አንድ ነው፤ አጋር የለውም፤ ከአላህ ሌላ በእውነት የምመለክ አምላክ እንደለሌ እመሰክራለሁ፤ ሙሐመድም የአላህ መልህክተኛ እና ባሪያ መሆናቸውን እመሰክራለሁ፤ የአላህ እዝነትና ሠላም በእርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው እንድሁም እነርሱን በመልካም በተከተሏቸው ሁሉ ላይ ይሁን።

በመቀጠል የሀገራችንን እና የህዝባችንን ተጨባጭ በማየት እስላማዊ የውርስ ህግጋትን የምታብራራ ይህችን አጭር ጽሁፍ ለማዘጋጀት ወሰንኩ፤ ይህቺ ጽሑፍ በአላህ ፍቃድ በርካታ ጥቅሞችን ያዘለችና ህዝበ ሙስልሙን ስለ ውርስ ህግጋቶች ጥሩ እውቀት የምታስጨብጥና በሙስልሙ መካከል መበዳደል እንዳይነኖር ከማድረግ አንጻር ሚናዋ ላቅ ያለ ነው። ስለሆነም ሙስልም እንደመሆናችን መጠን ከእኛ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች ማወቅ እና ማሳወቅ ግዴታችን መሆኑን አውቀን ለማወቅ እና ያወቅነውን ለመተግበር ልንተጋ ይገባል እላለው።

ይህ ዘርፍ እጅግ አሳሳቢ ከመሆኑ አንጻር በሙስልሙ ህብረተሰብ ዘንድ ያለው ተግባራዊነት ግን እጅግ ያነሰ መሆኑ የምያሳዝን ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ ሙስልም እስላማዊ የውርስ ህግጋቶችን ማወቅ እና ቤተሴቦቹንም የማሳወቅ ግዴታ አለቤት። አደጋ ብከሴት ያለውን ንብረት ወራሾች መከፋፈል የምችሉት በእስላማዊ የውርስ ህግጋቶች ብቻ መሆን እንዳለበት ሁሉም ሙስልም ማወቅ እና ተግባራዊ እንድሆን መጣር አለበት። ምክኒያቱም አንዱ የአንዱን ሐቅ ያለ አግባብ መውሰድ ሐራም (ክልክል) መሆኑን አላህ (ሱ.ወ) በቁርኣን፤ ነብዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) በሐዲሳቸው ገልጸዋል። ስለዝህ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል እላለው። እኔንም በጻፍኩት እና ባሰብኩት፣ እናንተንም ባነበባችሁትና በተገበራችሁት ተጠቃሚዎች ያድርገን! ኣሚን!

# ዘርፉ በእስላም ያለው ቦታ

ውርስ በሙስልሞች መካከል ግዴታ መሆኑ በቁርኣን እና በሱና ተደንግጓል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿لِّلرِّجَالِ نَصِيبٌ مِّمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ وَلِلنِّسَآءِ نَصِيبٌ مِّمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ مِمَّا قَلَّ مِنْهُ أَوْ كَثُرَ نَصِيبًا مَّفْرُوضًا﴾ [النساء: ٧]

ለወንዶች ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት (ንብረት) ድርሻ አላቸው፤ ለሴቶችም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ከእርሱ ካነሰው እና ከበዛው ድርሻ አላቸው፤ ግዴታ የተደረገ ድርሻ (ተደርጓል።) *(አል-ንሳእ፡ 7)*

﴿يُوصِيكُمُ ٱللَّهُ فِىٓ أَوْلَٰدِكُمْ ۖ لِلذَّكَرِ مِثْلُ حَظِّ ٱلْأُنثَيَيْنِ﴾ [النساء: ١١]

"አላህ በልጆቻችሁ (ውርስ በሚከተለው) ያዛችኋል። ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ብጤ አለው፤..." *(አል ንሳእ፡ 11)*

ቡኻሪ እና ሙስልም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«الحقو الفرائض بأهلها، فما بقي فلأولى رجل ذكر».

«የውርስ ድርሻን ለባለ ድርሻው አድርሱ። የተረፈው ከሁሉም በበለጠ በዝምድና ቅርብ ለሆነው ወንድ ነው።» ብለዋል። ነሳኢ፣ አቡ ዳውድ፣ ትርሚዚ እና እብን ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

«إن الله قد أعطى كلّ ذى حقّ حقه، فلا وصية لوارث». رواه النسائى وغيره

"አለህ በእርግጥ ለሁሉም ባለ ሐቅ ሐቁን ሰጥቶታል፤ ስለዚህ ለወራሽ ኑዛዜ አይኖረውም።"

ልብ በሉ! ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የውርስ ህግጋቶችን አስመልክቶ ሰዎች እንድማሩ አነሳስተዋል። በብዙ ሐዲሶቻቸውም ውስጥ ሰዎች እንድማሩ ቀስቅሰዋል። ከነዝህ ሐዲሶች መካከል አቡዳውድ፣ አብደላህ እብን ዐምርን (ረ.ዐ) ዋቢ አድርገው እንደዘገቡት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡-

أنّ النبيّ صلى الله عليه والسلم قال: «العلم ثلاث. آية محكمة، أو سنة قائمة، أو فريضة عادلة. وما كان سوى ذلك فهو فضل». رواه ابن ماجه والدارقطني.

"እውቀት ሶስት (ዓይነት) ነው። በጥበብ የተሞላ አንቀጽ (ቁርአን) ወይም ቋሚ የሆነች (የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)) ሱና (ፈለግ) ወይም ፍትሓዊ የሆነች የውርስ ህግ (ሲሆኑ) ከዝህ ውጭ ያለው እርሱ ትርፍ ነው።" ብለዋል።

እብን ማጃህ እና ዳረ ቁጠኒ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸውን ዘግቧል፡-

«تعلّموا الفرائض و علّموها الناس فإنه نصف علم وهو ينسى وهو أوّل شيء ينزع من أمّتي».

رواه ابن ماجاه والدار قطني

የውር «ስ ህግጋቶችን ተማሩ፤ ሰዎችንም አስተምሩ፤ እርሱ የእውቀት ግማሽ ነውና፤ እርሱም ይረሳል፤ ከህዝቦቼ መጀመሪያ የምነጠቀውም እርሱ ነው።» ብለዋል።

ሱፍያን ብን ዑየይና አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ብለዋል፡- “የእውቀት ግማሽ ነው የተባለበት ምክኒያት ሁሉም ሰዎች ስለምፈተኑበት ነው።” ሲሉ፣ ሓፍዝ ብን ረጀብ ደግሞ፡- “የእውቀት ግማሽ መሆን የቻለበት ለአቅሜ አዳም እና ለአቅሜ ሔዋን የደረሱ ሰዎች ጉዳይ በሁለት ይከፈላል። (እነሱም)፡- ከህይወት ጋር የተያያዘ ጉዳይ እና ከሞት ቡኃላ ካለው ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነቸው። ይህ ሁለተኛው (ከሞት ቡኃላ ካለው ጋር የተያያዘው) የውርስ ድንጋጌ ነው።” ብለዋል። በአጭሩ ዘርፉ በእስላም ያለው ቦታ ይህንን ይመስላል።

## ውርስን አስመልክቶ ማወቅ ያለብን አበይት ነጥቦች

ውርስ በሙስልሞች መካከል በቁርኣንና በሱና የተደነገገ ግዴታ መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። አሁን ደግሞ

ለውርስ ምክኒያት ወደ ሆኑት እና ከዚያ ቡኃላ ወዳሉት ነገሮች ከመግባታችን በፊት ማወቅ ያለብንን አበይት ነጥቦች ልጠቁማችሁ። እነሱም፡-

01 ኛ፡ የውርስ ህግጋቶችን እና ከእርሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች በጥልቀት ማወቅ

02 ኛ፡ የምወረሱ ነገሮችን ማወቅ (ንብረት ወይንም ጥሬ ገንዘብ)

03 ኛ፡ ውጠቱን (ለእያንዳንዱ ማግኘት ያለበትን ድርሻ እንዴት ልደርሰው እንደምችል) ማወቅ እና መስጠት

04 ኛ፡ በሸሪዓ ሑክሙ (ብይኑ) ምን እንዴሆነ ማወቅ

05 ኛ፡ የውርስ መሠረቶችን ማወቅ

06 ኛ፡ መስፈርቶቹን ማወቅ

07 ኛ፡ ሟቹ ከተዋቸው ሐብቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሐቆች[1] ለይቶ ማወቅ ናቸው።

## የውርስ ምክኒያቶች

### ሀ. የውርስ ሚክኒያቶች ሶስት ናቸው። እነሱም፡-

01 ዝምድና

02 ጋብቻ (ንካሕ)

03 ባሪያን ነጻ ማውጣት ናቸው።

### ሀ. ዝምድና፡-

ዝምድናን በሶስት ከፍለን ማየት እንችላለን። እነሱም፡-

01 አባት፣ እናት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ እያለ በሁለቱም በኩል ርቆ የምሄድ

02 ልጅ፣ የልጅ ልጅ፣ እያለ የምወርድ

03 ወንድም፣ የወንድም ልጅ፣ እህት የእህት ልጅ፣ ... አጎት፣ የአጎት ልጆች፣... አክስት፣ የአክስት ልጆች፣ ... እያለ የምቀጥል

### ለ. ጋብቻ (ንካሕ)፡-

ትክክለኛ የጋብቻ ህግ የተፈጸመበት የባልና ምስት ትስስር ወይም ጥምረት ሲሆን፣ ጎጆ ባይወጡ እና የግብረ ስጋ ግንኙነት ባይፈጽሙም እንኳ ትክክለኛ ንካሕ ከተደረገ መወራረስ ይችላሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

1 በብዛት ከሟች ንብረቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሐቆች አምስት ናቸው። እነሱም፡-
ሀ፡ ሟቹን ለመሸፈን የምወጡ ወጪዎች ለምሳሌ፡- ከፈን መግዣ፣ ለቀብር ቁፋሮ፣...ወዘተ
ለ፡ ዕዳ (በመያዣነት የተያዘ ንብረት)
ሐ፡ ዕዳ (የሰውም ይሁን የአላህ)
መ፡ ኑዛዜ
ሠ፡ ውርስ ናቸው።

﴿وَلَكُمْ نِصْفُ مَا تَرَكَ أَزْوَاجُكُمْ إِن لَّمْ يَكُن لَّهُنَّ وَلَدٌ﴾ [النساء: ١٢]

“ለእናንተም ሚስቶቻችሁ ከተውት (ንብረት) ለእነርሱ ልጅ ባይኖራቸው ግማሹ አላችሁ፤…” *(አል ኒሳእ: 12)*

## ሐ. ባሪያን ነጻ ማውጣት፡-

አንድ ሰው አንድ ባሪያን ሴትም ይሁን ወንድ ነጻ ካወጣ እና ከባሪነት ነጻ የተደረገው ሰው ወራሽ ከለለው ለዋለለት ውለታ ስባል ነጻ ያወጣው ሰውዬ ይወርሰዋል፤ ነጻ ያወጣውም ሰውዬም ሞቶ ከሆነ የእርሱ ዐሰባዎች[1] ወንድ የሆኑት ብቻ ይወርሱታል። ቡኻሪ፣ ነሳኢ እና ሌሎችም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) «الولاء لمن أعتق»:- “ዝምድና (ከባረነት) ነጻ ላደረገ ሰው ነው።” ብለዋል።

# ውርስን ክልክል የምያደርጉ ነገሮች

ውርስን ክልክል የምያደርጉ ነገሮች ስድስት ናቸው ። እነሱም፡-

01 ኩፍር (ክህዴት)

02 ግድያ (ተወራሹን መግደል)

03 ባሪያ መሆን

04 ዝሙት (በዘሙት የተወለደ ልጅ እና በዝሙት የወለደ አባት አይወራረሱም)

05 መረጋገም (ሊዓን)[2]

06 ሙት ሆኖ የተወለደ ህጻን ናቸው።

---

1 ዐሰባህ፡ ማለት ብቻውን ሲሆን ያለውን ንብረት ጨርሶ (አጠቃሎ) መውረስ የምችል ዘመድ ማለት ነው።

2 ሊዓን፡- ባል ምስቱን ዝሙት ሰርታለች ብሎ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ይከሳል፤ ነገር ግን፣ ከእርሱ ውጪ ሌላ ምስክር አልተገኘም፤ ምስት ውሼቱን ነው በማለት ክሱን ትቃወማለች፤ በዝህ ጊዜ ዳኛው ባልዩውን አራት ገዜ ወላህ እውነቴን ነው ብሎ ምስክርነቱን እንድሰጥ ካደረገው ቡኃላ በአምስተኛው ለይ ውሼቴን ከሆነ የአላህ እርግማን ይውረድብኝ ብሎ እንድሚል ያደርገዋል፤ ሴትዬዋም በተራዋ በአላህ ስም አራት ጊዜ ምላ ውሼቱን መሆኑን ካረጋገጠች ቡኃላ በአምስተኛው ለይ ባሌ የተናገረው እውነቱን ከሆኔ የአላህ እርግማን በእኔ ላይ ይሁን በማለት ዝሙት ላለመስራትዋ በመሓላ ካረጋገጠች ቅጣቱ ይቀርላታል። ባልም ዋሽህ ተብሎ አይገረፍም።ከዝያም የሁለቱም ትዳር እንድፈርስ ይደረጋል። ይህ መሃላቸው ሊዓነ ይባላል። አላህ ይጠብቀን!

# ከህዴት (ኩፍር)

አንድ ሙስልም ካፍር የሆነ ዘመዱን መውረስ አይችልም፤ እንደዝያውም አንድ ካፍር ሙስልም የሆነ ዘመዱን መውረስ አይችልም። ቡኻሪ እና ሙስልም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልህክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፡-

«لايرث المسلم الكافر ولا الكافر المسلم». (أخرجه البخاري ومسلم)

"ሙስልም ካፍርን አይወርስም፤ ካፍርም ሙስልምን አይወርስም" ብለዋል።

በሌላ ዘገባ፡-

«لا يتوارث أهل ملّتين»

"የተለያየ ዓይማኖት ያላቸው ሰዎች አይወራረሱም" ማለታቸውን አሕመድ፣ አቡ ዳውድ፣ ነሳኢ እና እብኑ ማጃሕ እብን ዑመርን አጣቅሰው ዘገበዋል።

# ግድያ

ግድያ ስባል (እንደ እስላም) ሞት የምያስፈርድ ወይም የደም ካሳ የምያስከፍል ለማለት ነው። ይህን የማያስደነግግ ከሆነ ከውርስ አያስከለክልም። ገዳይ የገደለውን ሰው ንብረት አይወርስም አውቆ የገደለ ከሆነ፤ ይህም እርሱን ለመቅጣት ስባል ነው። የአላህ መልህክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፡-

«ليس للقاتل من تركة المقتول شيء»

"ለገዳይ ከተገዳይ ንብረት ምንም (ውርስ) አይኖረውም"[1] ብለዋል።

# ባሪያ መሆን

ባሪያ አይወርስም አይወረስምም ሌሎችንም ከውርስ መጋረድ አይችልም። በከፍል

1 እብን አብድል በር ዘግበውታል።

ነጻ የሆነ ከሆነ ግን ነጻ በሆነው መጠን ልክ ይወርሳል ይወረሳል ብለዋል። ኺላፍ (የአቋም ልዩነት) ብኖርበትም ተከታዩን የእብን ዐባስን (ረ.ዐ) ሐዲስ ተንተርሰው ከፍል ምሁራን ነጻ በተደረገው ልክ ይወርሳል የምለውን አቋም ደግፈዋል።

عن ابن عباس أن النبيّ صلى الله عليه وسلم قال : «في العبد يعتق بعضه: يرث ويورث على قدر ماعتق منه».

"ነበዩ (ሶ.ዐ.ወ) በከፍል ነጻ የተደረገን ባሪያ አስመልክተው፡- "ከእርሱ ነጻ በተደረገው ልክ ይወርሳል፤ ይውረሳል" ብለዋል።[1]

## ዝሙት

ያለኒካ በዝሙት የተወለደ ልጅ አባቱን አይወርስም፤ አባቱም አይወርሰውም፤ ልጁ መውረስ የምችለው እናቱን ነው፤ እርሷም ትወርሰዋለች። ቡኻሪ፣ አቡዳውድ፣ እብን ማጃህ እና ትርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልህክተኛ (ሶዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧልና፡-

«الولد للفراش وللعاهر الحجر»

"ልጁ የፍራሹ (የባለ አልጋው)ነው፤ ዝና ላደረገው ዴግሞ ድንጋይ ነው።"ብለዋል።

## ሊዓን (መረጋገም)

ባል እና ምስት ከተረጋገሙ እና ባል ልጁ የእኔ አይደለም ካለ አባት ያን ልጅ አይወርሰውም፤ ልጁም እርሱን አይወርስም። በዝሙት እንደ ተወለደው ልጅ ይታያል።

## ስወለድ ድምጽ አልባ የሆነ ህፃን/ ሙቶ ተወለደ

ሙት ሆኖ የተወለደ / ስወለድ ያልጮኼ ወይም ድምፅ ያላ ሰማ/ ህፃን አይወርስም፤ አይወረስምም። ምክኒያቱም ለውርስ ምክኒየት ከሚሆኑ ነገሮች መካካል አንዱ

1 ሳሂቡል ሙግኒ

በህይወት መገኘት ነውና። ምክኒየቱም ይህ ሙት ሆኖ የተወለደው ህፃን ሰውዬው ስሞት በህይወት ይኑር አይኑር አይታወቅምና ነው። ሰውዬው ስሞት በህይወት መኖሩ ብታወቅ ይወርስ ነበር።

## የውርስ መስፈርቶች /ሸርጦች/

ውርስ ትክክለኛ ለመሆኑ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው። እነሱም፡-

01 ከልካይ አለመኖር፡- ውርስን ከሚከለክሉ ነገሮች ቀደም ብለን ከጠቀስናቸው ከ6ቱ አንድ አለመኖር

02 የተወራሹ መሞት መረጋገጥ ወይንም አንድ የጠፋን ሰው ቃዲ እንደ ሞተ ቆጥሮት ንብረቱ ለወራሾች እንድከፋፈል ከፈቀደ

03 ሟች በምሞትበት ገዜ ወራሹ በህይወት መኖር፡ ለምሳሌ፡- አንዲት ነፍሰጡር እናት ከልጆቿ መካከል አንዱ ብሞትባት በሆዷ ውስጥ ያለው ጽንስ የሞቴ ወንድሙን መውረስ የምችለው ስወለድ ድምጽ ካሰማ ወይንም በህይወት መኖሩ ከታወቀ ነው። ወንድሙ ከሞተ ቡኃላ አርግዛው ከሆነ ግን መውረስ አይችልም ምክኒያቱም በወቅቱ ስላልተፈጠረ።

## ወንድ ወራሾች

ወንድ ወራሾች በዝርዝር አስራ አምስት ይደርሳሉ። እነሱም፡- ልጅ፣ የልጅ ልጅ፣ … እያለ ይቀጥላል፤ አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ … እያለ ይቀጥላል፤ ወንድም (በሁለቱም በኩል)፣ ወንድም (በአባት በኩል ብቻ)፣ ወንድም (በእናት በኩል ብቻ)፣ የወንድም ልጅ (በሁለቱም በኩል)፣ የወንድም ልጅ (በአባት በኩል)፣ እያለ ይቀጥላል፤ አጎት (በሁለቱም በኩል)፣ አጎት (በአባት በኩል)፣ እያለ ይቀጥላል፤ የአጎት ልጅ (በሁለቱም በኩል)፣ የአጎት ልጅ (በአባታ በኩል) እያለ ይቀጥላል፤ ባል እና ባሪያን ነጻ ያደረገ ናቸው።

ባል ምስቱን ይወርሳል፤ እንደዝያውም የተፈታች ሆና ነገር ግን ዕዳዋን ሳትጨርስ (ሶስት የወር አበባ ሳይመጣባት) ከሞተችም ይወርሳታል። ዕዳዋ ካለቀ ግን መውረስ አይችልም። ባሪያን ነጻ ያወጣ ሰውም እንደዝሁ ነፃ የተደረገው ስሞት እና ወራሽ ዘመድ የለለው ከሆነ ነፃ ያወጣው ሰውዬ (ውለታ ስላለው) እርሱ ይወርሰዋል። እርሱም ቢሞት የእርሱ ወንድ ዐሰባዎች ብቻ ይወርሱታል።

ዘመዶች በሶስት ይከፈላሉ (ወንድ የሆኑት)። እነሱም፡- ኡሱል፣ ፉሩዕ እና ሐዋሺ ናቸው።

**ኡሱል የምባሉት፡-** አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ .... እያለ ይቀጥላል።

**ፉሩዕ፡-** የምባሉት ልጅ፣ የልጅ ልጅ፣ .... እያለ ይቀጥላል።

**ሐዋሺ፡** የምባሉት ሩቅ እና ቅርብ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

**ቅርብ ሐዋሺ የምባሉት ፡-** ወንድም፣ የወንድም ለጆች፣ የወንድም የልጅ ልጆች፣ ... እያለ ይቀጥላል፤ የእህት ልጆች፣ የእህት የልጅ ልጆች፣ ...እያለ ወደ ታች ይወርዳል።

**ሩቅ ሐዋሺ የምባሉት፡-** አጎት (በሁለቱም በኩል ወይም በአባት በኩል ብቻም ቢሆን)፣ የአጎት ልጅ፣ የአጎት የልጅ ልጅ፣ ... እያለ ወደ ታች ወርዳል።

እነዚህ ሁሉ ወንድ ወራሾች በአንድ የውርስ ክፍፍል ላይ አንድ ጊዜ ፈጽሞ መገኘት አይችሉም። ምክኒያቱም አንዳቸው አንዳቸውን ስለምጋርድ ነው። ለምሳሌ፡- አባት አያትን ይጋርዳል፤ እንደዝያውም በእናት በኩል ወንድም የሆኑትንም ይጋርዳል፤ ልጅ ዴግሞ ወንድሞች እንዳይወርሱ ይጋርዳቸዋል፤ ወንድም ዴግሞ አጎት እንዳይወርስ ያግደዋል። ስለዝህ በአንድ የውርስ ክፍፍል ላይ ሁሉም ብሰባሰቡ መውረስ የምችሉት ሶስቱ ብቻ ናቸው። እነሱም፡- ባል፣ ልጅ እና አባት ብቻ ናቸው።

## ሴት ወራሾች

ወራሽ ሴቶች በሶስት ይከፈላሉ። እነሱም፡- 1ኛ ምስት 2ኛ ዝምድና ያላት እና 3ኛ ባሪያን ነጻ ያወጣች ሴት ናቸው።

ምስት ባሏ ስሞት ከእርሱ ንብረት 1/4 ትወርሳለች ልጅ ካልኖረው። ልጅ ካለው ግን 1/8 ብቻ ትወርሳለች።

የሴቶቹንም ዝምድና በሶስት ከፍለን እናያለን። እነሱም፡-

**ዑሱል ፡** የምባሉት፡- እናት፣ አያት (በአባት ይሁን በእናት)

**ፉሩዕ የምባሉት፡-** ሴት ልጅ፣ የወንድ ልጅ ሴት ልጅ፣ … እያለ ወደ ታች የቀጥላል።

**ቅርብ ሓሺያ (ሓሺያ ቀሪባህ) ስትሆን እርሷም እህት ነች።** (በእናት ይሁን በአባት) ፣ ሩቅ ሐዋሽ የሆኑ ሴቶች አይወርሱም። እንደዝያውም አክስቶች (የእናትም ይሁኑ የአባት) ፣ የሴት ልጅ ሴት ልጅ፣ የሴት ልጅ ወንድ ልጅ፣ የወንድም ሴት ልች፣ እንድሁም የአጎት ሴት ልጅ (የአባት ይሁን በሁለቱም) እነዝህ ሁሉም አይወርሱም።

ሴት ወራሾችን ሰፋ ባለ መልኩ ስንዘረዝር አስራ አንድ ይደርሳሉ። እነሱም፡- ሴት ልጅ፣ የወንድ ልጅ ሴት፣ … እያለ ወደ ታች ይቀጥላል፤ እናት፣ ሴት አያት (በእናት በኩል) ፣ ሴት አያት (በአባት በኩል) ፣ ሴት ቅድሜ አያት (በወንድ አያት በኩል) ፣ እህት (በሁለቱም በኩል) ፣ እህት በአባት በኩል፣ እህት በእናት በኩል፣ ምስት እና ባሪያን ነጻ ያወጣች ሴት ናቸው።

በጥቅሉ ከወንድ እና ከሴት መውረስ የምችሉት 26 ሰዎች ናቸው። ሴት ቅድሜ አያት (የአባት አባት እናት) ስትቀር ሁሉም እንደምወርሱ ምሁራን ተስማምተዋል። በእርሷ መውረስና አለመውረስ ላይ ኸላፍ (ልዩነት) ብኖርም ይበልጥ ተቀባይነት ያለውና እማሙ አሕመድን ጨምሮ በርካታ ምሁራን የደገፉት መውረስ ትችላለች የምለውን ነው።

ውርስ በሁለት ይከፈላል። እነሱም ፡- ፈርድ እና ተዕሲብ ናቸው።

**ፈርድ፡-** የምባለው በሸሪዓ ለአንድ ወራሽ ይህን ያህል ይደርሰዋል ተብሎ በግልጽ የሰፈረ ድርሻ ሲሆን ወራሾቹ ዴግሞ “ዙፈርድ” (የውርስ መጠናቸው የታወቀ) ይባላሉ።

**ተዕሲብ፡-** የምባለው ዴግሞ መጠኑ ያልተገለጸ ሲሆን ወራሾቹ ዴግሞ “ዓስብ” (ያለገደብ የምወርሱ) ይባላሉ።

**ዓስብ፡-** ብቻውን ሲሆን ሁሉንም ንብረት አጠቃሎ ይወርሳል፤ ዙፈርድ አብረውት

ካሉ ዴግሞ ከእነርሱ የተረፈውን አጠቃሎ ይወርሳል፤ ካልተረፈ ዴግሞ ያጣል። ዓስብ ከሆኑት ውስጥ በፍጹም ማጣት የማይችሉት አባት እና ልጅ ብቻ ናቸው። ለዓስብ የምደርሰው ለዙፈርዶች በቀርአን የተወሰነለቸውን ድርሻ ከተሰጣቸው ቡኃላ ነው።ቡኻሪ እና ሙስልም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልህክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋልና:-

«الحقو الفرائض بأهلها، فما بقي فلأولى رجل ذكر». (رواه البخاري ومسلم)

«የውርስ ድርሻን ለባለ ድርሻው አድርሱ። የተረፈው ከሁሉም በበለጠ በዝምድና ቅርብ ለሆነው ወንድ ነው።» ብለዋል።

ፈርድ እና ተዕሲብ ለይ ተንተሪሰን ወራሾችን በአራት እንከፍላቸዋለን። እነሱም:-

01 ዙፈርድ ብቻ ሆነው የምወርሱ

02 ዐሰባህ ብቻ ሆነው የምወርሱ

03 ዙፈርድ እና ዐሰባህ ሆነው የምወርሱ ነገር ግን በአንድ ጊዜ ሁለቱንም መሆን ፈጽሞ የማይችሉ

04 ዙፈርድ እናዐሰባህ ሆነው የምወርሱ እና አንዳንድ ጊዜም በሁለቱም በኩል የምወርሱ

## ዙፈርድ ብቻ ሆነው የምወርሱ

ዙፈርድ /በቁርኣን የተደነገገላቸውን ድርሻ/ ብቻ የምወርሱት ሰባት ናቸው። እነሱም:-

01 እናት

02 ወንድ ልጅ (በእናት በኩል ብቻ የሆነ)

03 ሴት ልጅ

04 ባል

05 ምስት

06 ወንድ አያት

07 ሴት አያት ናቸው።

## ዐሰባህ ብቻ ሆነው የምወርሱ (ብቻቸውን ሲሆኑ ጨርሰው የምወርሱ)

ዐሰባህ ሆነው የምወርሱ 15 ናቸው። እነሱም፡-

01 ልጅ (ወንድ)
02 የልጅ ልጅ (ወንድ)፣ … እያለ ወደ ታች ብወርድም
03 አባት
04 ወንድ አያት (በአባት በኩል)
05 ወንድም (በሁለቱም በኩል)
06 ወንድም (በአባት በኩል)
07 የወንድም ልጅ (በሁለቱም)
08 የወንድም ልጅ (በአባት በኩል)
09 አጎት (በሁለቱም በኩል)
10 አጎት (በአባት በኩል)
11 የአጎት ልጅ (በሁለቱም)
12 የአጎት ልጅ (በአባት)…
13 ባሪያን ነጻ ያወጣ እና
14 ባሪያን ነጻ ያወጣች (ሴት ጨርሳ መውረስ የምትችለው እዝህ ቦታ ብቻ ነው።)
15 በይተል ማል (እስላማዊ ግምጃ ቤት) ናቸው።

## ዙፈርድ እና ዐሰባህ ሆነው የምወርሱ ነገር ግን በአንድ ጊዜ ሁለቱንም መሆን ፈጽሞ የማይችሉ

እነሱም አራት ናቸው።

01 ሴት ልጅ

02 የወንድ ልጅ ሴት ልጅ (የልጅ ልጅ ... ብትሆንም)

03 እህት (በሁለቱም በኩል)

04 እህት (በአባት በኩል) ሲሆኑ እነዝህ የጠቀስናቸው አራቱም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ብሆንም ያው ነው።

## ዙፈርድ እናዐሰባህ ሆነው የምወርሱ እና አንዳንድ ጊዜም በሁለቱም በኩል የምወርሱ

እነሱም ሁለት ሲሆኑ ፡- አባት እና አያት (የአባት አባት) ናቸው።

## በቁርኣን የተደነገጉ ድርሻዎች

በቁርኣን የተጠቀሱት ድርሻዎች ስድስት ናቸው። እነሱም ፡- ግማሽ፣ ሩብ፣ አንድ ስምንተኛ፣ ሁለት ሦስተኛ፣ አንድ ሦስተኛ እና አንድ ስድስተኛ ሲሆኑ ሰባተኛው በእጅትሃድ (ቀርኣን እና ሱና ላይ በተንተራሰ መላምት) የተደነገገ ሲሆን እርሱም ሱሉሱልባቂ (ቀሪ አንድ ሦስተኛ) ይሰኛል።

ድርሻ በማለት ለማለት የተፈለገው ለአንድ ወራሽ እንድሰጠው ሸሪዓው የደነገገው የውርስ መጠንን ለማለት ሲሆን በዝህ የውርስ ድርሻ ላይ ዐውል እና ረድ በምባሉት የስሌት ዜዴዎች ካልሆነ በስተቀር መጨመርም ሆነ መቀነስ አይፈቀድም።

ረድ በምባለው የስሌት ዜዴ ድርሻው ላይ ጭማሪ የምደረግ ሲሆን አውል በምባለው ዴግሞ ይቀንሳል። ረድ እና ዐውል የምባሉ አሰራሮች በሸሪዓው ተቀባይነት ያላቸው ሲሆኑ አብደላህ እብን ዐባስ (ረ.ዐ) ስቀሩ ሁሉም ሲሓቦች (ረ.ዐ) ተስማምተውበታል።

## ግማሽ የምወርሱ

ግማሽ የምወርሱት አምሰት ሰዎች ናቸው። እነርሱም ብቻቸውን ሲሆኑ ነው።

01 ባል

- 02 ሴት ልጅ
- 03 የወንድ ልጅ ሴት ልጅ
- 04 እህት (በሁለቱም በኩል)
- 05 እህት (በአባት በኩል)

## ባል

ባል ምስቱ ስትሞት ግማሽ ንብረቷን መውረስ የምችለው ሟቿ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካልኖራት ነው። ልጅ ስባል ፆታ አይለይም። በዝሙት የተወለደ እንኳ ቢሆን። አለህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَكُمْ نِصْفُ مَا تَرَكَ أَزْوَاجُكُمْ إِن لَّمْ يَكُن لَّهُنَّ وَلَدٌ﴾ [النساء: ١٢]

"ለእናንተም ምስቶቻችሁ ከተውት (ንብረት) ግማሽ አላችሁ ለእነርሱ ልጆች ካልኖራቸው፤ …" *(አል-ንሳእ፡ 12)*

## ሴት ልጅ

ሴት ልጅ የወላጇቿን ንብረት ግማሽ መውረስ የምትችለው ሁለት ሰዎች ካልኖሩ ነው። እነርሱም ፡- ወንድሟ እና እህቷ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِن كَانَتْ وَاحِدَةً فَلَهَا النِّصْفُ﴾ [النساء: ١١]

"… አንድ ከሆነች (ከተዋችሁት ንብረት) ግማሽ አላት፤ …" *(አል-ንሳእ፡ 11)*

## የወንድ ልጅ ሴት ልጅ

የወንድ ልጅ ሴት ልጅ የአያቷን ንብረት ግማሹን መውረስ የምትችለው የሚከተሉት ሦስት ዓይነት ሰዎች ካልኖሩ ነው። እነርሱም፡-

01 ወንድሟ ወይንም በእርሷ ደረጃ ውስጥ የምገኝ የአጎቷ ልጅ ካልኖረ

02 እህቷ ወይንም በእርሷ ደረጃ ውስጥ የምትገኝ የአጎቷ ልጅ ካልኖረች

03 የሟች ልጅ ካልኖረ/ች

# እህት (በሁለቱም በኩል)

በእናትም በአባትም በኩል እህት የሆነችው የወንድሟን ንብረት ግማሽ መውረስ የምትችለው የሚከተሉት አራት ሰዎች ካልኖሩ ነው።

01 ወንድሟ ካልኖረ (በእናትም በአባትም በኩል ወንድም የሆነ)

02 እህቷ ካልኖረች (በእናትም በአባትም በኩል እህት የሆነች)

03 የሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካልኖረ

04 የሟች አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ … ካልኖሩ (ወንዶች የሆኑት ብቻ)። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنِ ٱمْرُؤٌا۟ هَلَكَ لَيْسَ لَهُۥ وَلَدٌ وَلَهُۥٓ أُخْتٌ فَلَهَا نِصْفُ مَا تَرَكَ﴾ [النساء: ١٧٦]

"…ለእርሱ ልጅ የለለው ሰው ቢሞት ለእርሱም እህት ብትኖረው ለእርሷ ከተወው (ንብረት) ግማሽ አላት። …" *(አለ- ንሳእ፡ 176)*

# እህት በአባት በኩል

በአባት በኩል ብቻ እህት የሆነችው የወንድሟን ንብረት ግማሽ መውረስ የምትችለው የሚከተሉት አምስት ሰዎች ካልኖሩ ነው። እነርሱም ፡-

01 ወንድሟ ካልኖረ (በአባት በኩል የሆነ)

02 እህቷ ካልኖረች (በአባት በኩል)

03 የሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካልኖረ

04 የሟች አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ ... ካልኖሩ (ወንዶች የሆኑት ብቻ)

05 በሁለቱም በኩል ወንድም/እህት የሆኑ ካልኖሩ

# ሩብ (1/4) የምወርሱ

ሩብ የምወርሱ ሁለት ሰዎች ናቸው። እነሱም፡- ባል እና ምስት ናቸው።

## ባል

ባል ከምስቱ ንብረት ሩብ (1/4) መውረስ የምችለው ምስቱ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ስኖራት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن كَانَ لَهُنَّ وَلَدٌ فَلَكُمُ ٱلرُّبُعُ مِمَّا تَرَكْنَ﴾ [النساء: ١٢]

"... ለእነርሱም (ለምስቶች) ልጅ ብኖራቸው ከተውት (ንብረት) ለእናንተ ሩብ አላችሁ፤ ..." *(አል-ንሳእ፡ 12)*

## ምስት

ምስት ከባሏ ንብረት 1/4 (ሩብ) መውረስ የምትችለው ባሏ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካልኖረው ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡

﴿وَلَهُنَّ ٱلرُّبُعُ مِمَّا تَرَكْتُمْ إِن لَّمْ يَكُن لَّكُمْ وَلَدٌ﴾ [النساء: ١٢]

"... ለእናንተም ልጅ ባይኖራችሁ ከተዋችሁት (ንበረት) ለእነርሱ (ለምስቶች) ሩብ አላቸው። ..." *(አል-ንሳእ፡ 12)*

ግማሽ ንብረት የምስት ነው የምባል ነገር በፍጹም የለም። ምሰቶች (ሴቶች) አላህን ፍሩ። ሐቃችሁ ያልሆነን ነገር አትውሰዱ። ምናልባትም እየወሰዳችሁት ያላችሁት

ንብረት የየቲሞች ሐቅ ልሆን ይችላል። የየቲምን ሐቅ የምበሉ ሰዎች እየበሉ ያሉት እሳት መሆኑን አላህ (ሱ.ወ) በቁርኣን በግልጽ ተናግሯል። የየቲሞችን ሐቅ ብቻ ሳይሆን የአንድ ሙስልምን ሐቅ ያለ አግባብ የበላ ሰውም የበላው እሳት መሆኑን ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ተናግረዋል። የካፍርንም ሐቅ ቢሆን መብላት ክልክል ነው። ትርፉ በዱንያም በአኼራም ፀፀት ብቻ ነው። ጥበበኛው አምላክ አላህ የወሰነልሽን በውዴታ ተቀበይ። የእርሱ ውሳኔ ልያስደስትሽ ይገባል። በእርሱ ውሳኔ የማትደሰቺ ከሆንሽ በአላህ እና በመልህክተኛው እንዳላመንሽ እወቂ እርሱ ማንንም አይበደልምና። እሱ ስለ እኛ ከማናችንም በላይ ያውቃል። የእርሱ ፍርድ ከማንም በላይ ትክክል ነው። ለማንኛውም ማሕበረሰብ እና ለየትኛውም ዘመን የምሰራ ፍጹም ፊትሓዊ ነው።

## አንድ ስምንተኛ የምወርሱ

አንድ ስምንተኛ የምወርሱ ምስቶች ብቻ ናቸው። ምስት አንድም ትሁን ከአንድ በላይ ባል ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ሴትም ይሁን ወንድ ካለው 1/8 ትወርሳለች። ምስቶቹ ከአንድ በላይ ብሆኑም እሱኑኑ እኩል ይካፈላሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن كَانَ لَكُمْ وَلَدٌ فَلَهُنَّ ٱلثُّمُنُ مِمَّا تَرَكْتُم﴾ [النساء: ١٢]

"… ለእናንተም ልጅ ብኖራችሁ ከተዋችሁት (ንብረት) ለእነርሱ (ለምስቶች) አንድ ስምንተኛ አላቸው፤ …" *(አል-ንሳእ፡ 12)*

## ሁለት ሦስተኛ የምወርሱ

ሁለት ሦስተኛ የምወርሱ አራት ሰዎች ናቸው። እነሱም፡-

01 ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የሟች ሴት ልጆች

02 ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የወንድ ልጅ ሴት ልጆች

03 ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ እህቶች (በሁለቱም በኩል እህት የሆኑ)

04 ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ እህቶች (በአባት በኩል)

## ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የሟች ሴት ልጆች

የሟች ሴት ልጆች የአባታቸውን ንብረት 2/3 መውረስ የምችሉት በሁለት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሁለት እና ከዝያ በላይ ሲሆኑ

02 ወንድ ልጅ /ወንድማቸው/ ካልኖረ

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن كُنَّ نِسَآءً فَوۡقَ ٱثۡنَتَيۡنِ فَلَهُنَّ ثُلُثَا مَا تَرَكَ﴾ [النساء: ١١]

"... (ሁለት ወይም) ከሁለት በላይ የሆኑ ሴቶች ከሆኑ ለእነርሱ (ሟች) ከተወው (ንብረት) ሁለት ሦስተኛ አላቸው፤ ..." *(አል-ንሳእ፡ 11)*

ትርሚዚ፣ ሓኪም እና ሌሎችም ሶሒሕ (ትክክል ነው) ባሉት ሐዲስ የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለሠዕድ ሁለት ሴት ልጆች አባታቸው ከተወው ንብረት 2/3 ወስነውላቸዋል።

## ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የወንድ ልጅ ሴት ልጆች

የወንድ ልጅ ሴት ልጆች ከአያታቸው ንብረት 2/3 የምወርሱት በሦስት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሁለት እና ከዝያ በላይ ሲሆኑ

02 የሟች ልጅ (ሴትም ይሁን ወንድ) ያለመኖር

03 ወንድማቸው የሆነው የልጅ ልጅ ያለመኖር

# ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ እህቶች (በሁለቱም በኩል እህት የሆኑ)

እህቶች የወንድማቸውን ንብረት 2/3 የምወርሱት በአራት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሁለት እና ከዝያ በላይ ሲሆኑ

02 ወንድማቸው ካልኖረ

03 የሟች ልጅ (ሴትም ይሁን ወንድ) ያለመኖር

04 የሟች አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ ... ካልኖሩ (ወንዶች የሆኑት ብቻ)

አለህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن كَانَتَا ٱثۡنَتَيۡنِ فَلَهُمَا ٱلثُّلُثَانِ مِمَّا تَرَكَ﴾ [النساء: ١٧٦]

"... (እህቶች) ሁለት ከሆኑም (ወንድማቸው) ከተወው (ንብረት) ሁለት ሦስተኛ አላቸው፤ ..." *(አል-ንሳእ፡ 176)*

# እህቶች (በአባት በኩል)

በአባት በኩል እህት የሆኑት ከወንድማቸው ንብረት 2/3 ውን የምወርሱት በአምስት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሁለት እና ከዝያ በላይ መሆን

02 ወንድማቸው ካልኖረ (በሁለቱም በኩል ወንድም የሆነ ወይም በአባት በኩል ብቻ)

03 የሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ (ሴትም ይሁን ወንድ) ያለመኖር

04 የሟች አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ ... ካልኖሩ (ወንዶች የሆኑት ብቻ)

05 በሁለቱም በኩል ወንድም/እህት/ የሆነ ሰው ካልኖረ

# አንድ ሦስተኛ (1/3) የምወርሱ

አንድ ሦስተኛ የምወርሱ ሁለት ሰዎች ናቸው። እነሱም፡-

01 እናት

02 በእናት በኩል ብቻ ወንድም /እህች/ የሆኑ እና ቁጥራቸው ሁለት እና ከዝያ በላይ የሆነ

እናት ከልጇ ንብረት 1/3 የምታገኘው በሦስት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ … (ሴትም ይሁን ወንድ) ካልኖረው

02 ሟች ሁለት እና ከዝያ በላይ የሆኑ ወንድሞች/እህቶች/ ካልኖሩት ፆታቸው ብለያይም

03 ከእርሷ ጋር ባል /ምስት/ ፣ እና አባት አንድ ላይ ካልተሰባሰቡ ነው። ተሰባስበው ከተገኙ ግን እናት የምታገኘው ድርሻ ቀሪ አንድ ሦስተኛ (ሱሉሱል ባቂ) ይሆናል። ይህም ማለት 1/6 ወይም 1/4 ማለት ነው።

# በእናት በኩል ብቻ ወንድም /እህት/ የሆኑ እና ቁጥራቸው ሁለት እና ከዝያ በላይ የሆኑ

በእናት በኩል ብቻ ወንድም /እህት/ የሆኑት ከወንድማቸው ንብረት 1/3 ውን መውረስ የምችሉት በሦስት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሁለት እና ከዝያ በላይ መሆን

02 ሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ … (ሴትም ይሁን ወንድ) ካልኖረው

03 የሟች አባት፣ አያት፣ ቅድሜ አያት፣ … ካልኖሩ (ወንዶች የሆኑት ብቻ)

አለህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن كَانُوٓاْ أَكۡثَرَ مِن ذَٰلِكَ فَهُمۡ شُرَكَآءُ فِي ٱلثُّلُثِۚ﴾ [النساء: ١٢]

"… ከዝህም (ከአንድ) በላይ የበዙ ከሆነ እነርሱ አንድ ሦስተኛ ተጋሪዎች ናቸው፤ …" *(አለ-ንሳእ፡ 12)*

የእናት ልጆች ወንዱ ከሴቷ ጋር እኩል ይታያሉ፤ የውርስ ድርሻቸውም እኩል ነው፤ በሌሎች ወራሾች ላይም የምፈጥሩት ተጽዕኖ እኩል ነው፤ አንዳንድ ጊዜም የእነርሱ መኖር የሌሎችን ድርሻ እንድቀንስ ያደርጋል ባይወርሱም እንኳ። በደረጃ ከምቀርቡት ሰው ጋርም ይወርሳሉ።

## ሱሉሱል ባቂ (ቀሪ አንድ ሦስተኛ) የምወርሱ

ሱሉሱል ባቂ (ቀሪ አንድ ሦስተኛ) የምትወርስ እናት ብቻ ነች። ይህም የሚሆነው አንድ ሰው ምስቱን፣ እናቱን እና አባቱን ትቶ ቢሞት መደቡን ከአራት አድርገን አንዱን ለምስት እንሰጣታለን፤ ከተረፈው ከሦስቱ አንዱን ለእናት እንሰጣታለን። ይህም ሱሉሱል ባቂ (ቀሪ አንድ ሦስተኛ) ይባላል። አባት ደግሞ የተረፈውን ሁለቱን ይወስዳል።

ሌላው ደግሞ ሟቿ ሴት ብትሆንና ባሏን፣ አባቷን እና እናቷን ትታ ብትሞት መደቡን ከስድስት አድርገን ግማሹን (3) ለባል እንሰጠዋለን፤ ከተረፈው ከሦስቱ አንዱን ለእናት እንሰጣታለን፤ ይህም ሱሉሱል ባቂ (ቀሪ አንድ ሦስተኛ) ይባላል። የተረፈውን አባት ይወስዳል። ይህ ማለት እንግዲህ በመጀመሪያው ውርስ ላይ እናት ያገኘችው 1/4 ሲሆን በሁለተኛው ደግሞ 1/6 ነው።

## አንድ ስድስተኛ የምወርሱ

አንድ ስድስተኛ የምወርሱ ሰባት ሰዎች ናቸው። እነሱም፡-

01 አባት

02 እናት

03 አያት

04 ሴት አያት

05 የወንድ ልጅ ሴት ልጅ

06 እህት (በአባት በኩል)

07 የእናት ልጅ ወንድ ይሁን ሴት (በእናት በኩል ብቻ ወንድም/እህት የሆነ/ች) ናቸው።

## አባት

አባት ከልጁ ንብረት 1/6 የምወርሰው ሚች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካለው ነው። አለህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلِأَبَوَيۡهِ لِكُلِّ وَٰحِدٖ مِّنۡهُمَا ٱلسُّدُسُ مِمَّا تَرَكَ إِن كَانَ لَهُۥ وَلَدٞ﴾ [النساء: ١١]

"… ለእርሱ ልጅ ካለው ለእናት እና ለአባት ለእያንዳንዳቸው (ልጃቸው) ከተወው ንብረት አንድ ስድስተኛ አላቸው። …" (አል-ንሳእ፡ 11)

## እናት

እናት ከልጇ ንብረት 1/6 የምትወርሰው በሁለት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሚች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካለው

02 ሚች ሁለት እና ከዝያ በላይ ወንድሞች /እህቶች/ ካሉት

﴿فَإِن كَانَ لَهُۥٓ إِخۡوَةٞ فَلِأُمِّهِ ٱلسُّدُسُ﴾ [النساء: ١١]

አለህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- "… ለእርሱ ወንድሞች/እህቶች/ ካሉት ለእናቱ አንድ ስድስተኛ አላት፤ …" (አል-ንሳእ፡11)

## ወንድ አያት

ወንድ አያት ከልጅ ልጁ ንብረት 1/6 መውረስ የምችለው በሁለት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካለው

02 የሟች አባት ካልኖረ

## ሴት አያት

ሴት አያት ከልጅ ልጇ ንብረት 1/6 መውረስ የምትችለው በሁለት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 ሟች እናት ከለለው

02 ዝምድናዋ መውረስ በምችል ሰው በኩል የመጣ መሆን አለቤት። መውረስ በማይችል ሰው መንገድ ከሆነ መውረስ አትችልም። ለምሳሌ፡ አያት የተባለችው የእናት አባት እናት ከሆነች መውረስ አትችልም፤ ምክኒያቱም የእናት አባት መውረስ ስለማይችል ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ከሴት አያቶች የምወርሱት ሦስት ናቸው። እነሱም፡-

01 የእናት እናት፣ … እያለ ይቀጥላል።

02 የአባት እናት፣ … እያለ ይቀጥላል።

03 የአባት አባት እናት፣ … እያለ ይቀጥላል።

ሴት አያት ብቻዋን ስትሆን 1/6 ውን ለብቻዋ ትወስዳለች፤ ከእርሷ ጋር በደረጃ እኩል የሆኑ ሌሎች ካሉ 1/6 ውን እኩል ይካፈላሉ። በደረጃ (በዝምድና) ይበልጥ ቅርብ የሆነች ካለች እሷ ብቻ ትወስድና ራቅ ያሉት ያጣሉ።

# አንድ ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ የወንድ ልጅ ሴት ልጆች

የወንድ ልጅ ሴት ልጆች የአያታቸውን ሐብት 1/6 መውረስ የምችሉት በሁለት መንገድ ነው። እነሱም፡-

01 አንዷት የሟች ሴት ልጅ ብቻ አብራቸው ካለች

02 ወንድማቸው ወይም በደረጃ ከእነርሱ ጋር እኩል የሆነ የአጎታቸው ልጅ ካልኖረ

የወንድ ልጅ ሴት ልጅ ብቻዋን ብትሆንም ከአንድ በላይ ብሆኑም ልዩነት የለውም። ድርሻቸው 1/6 ብቻ ነው። ብዛት ካላቸውም እሱኑኑ እኩል ይካፈላሉ። ብቻዋን ከሆነችም ያው ነው።

# እህት (በአባት በኩል)

በአባት በኩል እህት የሆነችው የወንድሟን ሐብት 1/6 መውረስ የምትችለው በሚከተለው መልኩ ነው።

01 ከአንዷት በእናትም በአባትም በኩል እህት ከሆነች ልጅ ጋር ስትሆን (ይህች በሁለቱም በኩል እህት የሆነችው ብቻዋን ስትሆን ግማሽ ትወርሳለች።)

02 ዐሰባህ (ወንድም (በአባት በኩል)፣ ወንድ አያት፣ ወንድ ልጅ፣ የልጅ ልጅ፣) ካልኖሩ እና እንደዝያውም እናት ካልኖረች ነው።

በአባት በኩል እህት የሆኑት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ብሆንም እሱኑኑ እኩል ይካፈላሉ።

## የእናት ልጅ (በእናት በኩል ብቻ ወንድም /እህት/ የሆነ/ች)

በእናት በኩል ብቻ ወንድም የሆነ ወይም እህት የሆነች ከወንድሟ/ሙ ሐብት 1/6 ለማግኘት የምከተሉት መሟላት አለባቸው። እነሱም፡-

01 የሟች ልጅ ወይም የልጅ ልጅ አለመኖር

02 የሟች አባት፣ አያት፣ … አለመኖር

03 ብቻውን/ብቻዋን መሆን

አለህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَهُۥٓ أَخٌ أَوۡ أُخۡتٌ فَلِكُلِّ وَٰحِدٍ مِّنۡهُمَا ٱلسُّدُسُ﴾ [النساء: ١٢]

"… ለእርሱ (ወላጅና ልጅ ሳይኖረው ለሞተው ሰው) ወንድም ወይም እህት ብኖሩት ለእያንዳንዳቸው አንድ ስድስተኛ አላቸው፤ …" (አል-ንሳእ፡12)

## ዐሰባህ /ያለገደብ የምወርሱ/

በሦስት ይከፈላሉ። እነሱም፡-

01 ለብቻው ጨርሶ የምወርስ

02 በሌላ ሰው ምክኒያት ጨርሰው የምወርሱ

03 ከሌሎች ጋር በመሆን ጨርሰው የምወርሱ

## ሀ- ለብቻቸው ጨርሰው የምወርሱ

ለብቻቸው ሆነው ጨርሰው የምወርሱ 14 ናቸው። እነሱም፡-

01 ልጅ (ወንድ)

02 የልጅ ልጅ (ወንድ)፣ ... እያለ ወደ ታች ብወርድም

03 አባት

04 ወንድ አያት (በአባት በኩል)

05 ወንድም (በሁለቱም በኩል)

06 ወንድም (በአባት በኩል)

07 የወንድም ልጅ (በሁለቱም) ...

08 የወንድም ልጅ (በአባት በኩል) ...

09 አጎት (በሁለቱም በኩል)

10 አጎት (በአባት በኩል)

11 የአጎት ልጅ (በሁለቱም)...

12 የአጎት ልጅ (በአባት)...

13 ባሪያን ነጻ ያወጣ እና

14 ባሪያን ነጻ ያወጣች ናቸው። (ሴት ጨርሳ መውረስ የምትችለው እዝህ ቦታ ብቻ ነው።)

ሴቶች ባሪያን አስመልክቶ ለራሳቸው ነፃ ካደረጉዋቸው ወይንም እነርሱ ነፃ ያደረጉት ሰው ነፃ ያደረገውን ካልሆነ በስተቀር መውረስ አይችሉም።

ለብቻ ጨርሶ መውረስ የምቻለው በ 6 መንገዶች ሲሆን እነሱም በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ናቸው።

01 ልጅ መሆን

02 አባት መሆን

03 አያት መሆን

04 ወንድም መሆን እና የወንድም ልጅ መሆን

05 አጎት መሆን እና የአጎት ልጅ መሆን

06 ባሪያን ነፃ ማውጣት ናቸው።

እነዝህ ሁሉ ስወርሱ በቅደም ተከተላቸው መሆን አለበት። በቅደም ተከተላቸው እኩል ከሆኑ በዝምድና ደረጃቸው አንዱ ከአንዱ እንድቀድም ይደረጋል። በዝምድናም እኩል ከሆኑ ይበልጥ ጠንከር የምለውን እናስቀድማለን።

ልጅ በማለት ለማለት የተፈለገው የሟች ወንድ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ፣ ... ለማለት ሲሆን፣ አባት በማለት ደግሞ አያት ቅድሜ፣ ወንድ የሆኑትን ብቻ ... ለማለት ነው። ወንድም እና ልጆቻቸው ስባል ለማለት የተፈለገው በሁለቱም በኩል ወይም በአባት በኩል ብቻ ወንድም የሆኑትን እና ወንዶች ልጆቻቸውን፣ የልጅ ልጆቻቸውን፣ ... ለማለት ነው አጎት ስባልም እንደዚያው ነው። ነገር ግን በእናት በኩል ብቻ ወንድም ወይም አጎት የሆኑትን አይጨምርም።

## ለ- በሌላ ሰው ምክኒያት ጨርሰው የምወርሱ

ይህ ማለት አንድ ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ ሴቶች ከአንድ ወንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ወንዶች ጋር ተጣምረው ስወርሱ ነው። በዝህ ጊዜ ለወንዱ ሁለት እጅ ስሰጠው ለሴቷ ደግሞ አንድ እጅ ይሰጣታል። በዝህ ሁኔታ ጨርሰው ይወርሳሉ።

እነሱም አራት ሰዎች ናቸው።

01 የሟች ሴት ልጅ ከሟች ወንድ ልጅ ጋር (ብዛት ብኖራቸውም)

02 የወንድ ልጅ ሴት ልጅ ከወንድሟ ጋር ወይም በእሷ ደረጃ ውስጥ ከምገኝ የወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ጋር የአጎቷ ልጅም ልሆን ይችላል። ወይም በደረጃ ከእርሷዝቅ ከምለው የወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ጋር መውረስ ከፈለገችም ትችላለች። ይህ የምሆነው ግን በሸሪዓ የተወሰነላት ድርሻ ካልኖራት ነው። የተወሰነላት ድርሻ ካላት በደረጃ ከእርሷዝቅ ከምለው የወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ጋር ዐሰባህ ሆና መውረስ አትችልም።

03 በእናትም በአባትም በኩል እህት የሆነችው በእናትም በአባትም በኩል ወንድም ከሆነው ጋር

04 በአባት በኩል እህት የሆነችው በአባት በኩል ወንድም ከሆነው ጋር

## ሐ- ከሌሎች ጋር በመሆን ጨርሰው የምወርሱ

ይህ ደግሞ ሴቶች በመሰባሰብ ዐሰባህ ሆነው ጨርሰው ስወርሱ ነው። እነሱም በሁለት ይከፈላሉ።

01 እህት (በሁለቱም በኩል) ከሚች ሴት ልጅ ጋር ወይም ከወንድ ልጅ ሴት ልጅ ጋር (ብዛት ብኖራቸውም)

02 እህት (በአባት በኩል) ከሚች ሴት ልጅ ጋር ወይም ከወንድ ልጅ ሴት ልጅ ጋር (ብዛት ብኖራቸውም) ናቸው።

በአባት በኩል እህት የሆነችው በዝህ ቦታ ልክ በሁለቱም በኩል እህት እንደሆነችው ስለምትወሰድ ከሴት ልጅ ወይም ከልጅ ልጅ የተረፈውን ብቻዋን ከሆነች በማጠቃለል ትወርሳለች። እህቶቿ ካሉ ዴግሞ እኩል ይካፈላሉ። እዝህ ጋር መርሳት የለለብን ጉዳይ በሁለቱም በኩል እህት የሆነችው በሁለቱም በኩል ወንድም እንደሆነው ስለምትወሰድ በአባት በኩል ብቻ እህት የሆነችውን እንዳትወርስ ትጋርዳታለች። በአባት በኩል ብቻ እህት የሆነችው በአባት በኩል ብቻ ወንድም እንደሆነው ስለምትወሰድ የወንድም ልጆችን እንዳይወርሱ ትጋርዳቸዋለች።

## እገዳ (ሑጅብ)

በዝህ ዘርፍ እገዳ ማለት አንድ ሰው እንዳይወርስ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መከልከል ማለት ነው። በዝህ ዘርፍ ውስጥ ስለ እገዳ ማወቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው። እንድሁም አንዳንድ ምሁራን ስለ እገዳ የማያውቅ ሰው ውርስን አስመልክቶ ፈትዋ (ብይን) መስጠት በእርሱ ላይ ሐራም ነው እስከማለት ደርሰዋል።

እገደ በሁለት ይከፈላል። እነርሱም :-ሙሉ በሙሉ ማገድ እና በከፊል ማገድ ናቸው።

## ሑጅቡ ሑርማን /ሙሉ በሙሉ ማገድ/

ይህ ዓይነቱ እገዳ ወራሹን ሙሉ በሙሉ ከውርስ ድርሻ እንዳይኖረው ያደርገዋል። ለምሳሌ:- ልጅ እያለ የልጅ ልጅ አይወርስም፤ አባት እያለ አያት አይወርስም፤ እናት እያለች አያት አትወርስም፤ ልጅ እያለ ወንድም አይወርስም፤ ወንድም እያለ አጎት አይወርስም፤ በሁለቱም በኩል ወንድም የሆነው እያለ በአንድ በኩል ብቻ ወንድም

የሆነው አይወርስም፤ እንደዝያውም ሴት ልጅ እያለች በእናት በኩል ብቻ ወንድም ወይም እህት የሆኑት አይወርሱም። በሁለቱም በኩል አጎት የሆነው እያለ በአባት በኩል ብቻ አጎት የሆነው አይወርስም።

## ሑጅቡ-ነቅስ /በከፊል ማገድ/

ይህ ዓይነቱ እገዳ ወራሹ የምያገኘውን ድርሻ በከፊል እንድያጣ ወይም እንድቀንስ ያደርጋል። ከብዙ ወደ ትንሹ ዝቅ ስለምያደርገው። ለምሳሌ፡- ባል ምስቱ ልጅ ከለላት ከምስቱ ንብረት መውረስ የምችለው ግማሹን ነው። ልጅ ካላት ግን መውረስ የምችለው 1/4ውን ብቻ ነው። ምክኒያቱም የልጅ መኖር ባል ማግኘት ያለበትን ድርሻ ይቀንስበታልና። አባት ብቻውን ከሆነ የልጁን ሐብት ጨርሶ ይወርሳል፤ ነገር ግን ልጁ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካለው መውረስ የምችለው 1/6ውን ብቻ ይሆናል። ምክኒያቱም የልጅ መኖር የአባትን ድርሻ ይቀንስበታልና። ሴት ልጅ ብቻዋን ስትሆን የአባቷን ሐብት ግማሹን ትወርሳለች፤ ነገር ግን እህቶቿ አብረዋት ካሉ 2/3ውን በጋራ ይካፈላሉ። የልጅቷ ድርሻ በእህቶቿ መኖር የቀንሳል።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن كُنَّ نِسَآءً فَوۡقَ ٱثۡنَتَيۡنِ فَلَهُنَّ ثُلُثَا مَا تَرَكَۖ وَإِن كَانَتۡ وَٰحِدَةً فَلَهَا ٱلنِّصۡفُۚ وَلِأَبَوَيۡهِ لِكُلِّ وَٰحِدٍ مِّنۡهُمَا ٱلسُّدُسُ مِمَّا تَرَكَ إِن كَانَ لَهُۥ وَلَدٌۚ فَإِن لَّمۡ يَكُن لَّهُۥ وَلَدٌ وَوَرِثَهُۥٓ أَبَوَاهُ فَلِأُمِّهِ ٱلثُّلُثُۚ فَإِن كَانَ لَهُۥٓ إِخۡوَةٌ فَلِأُمِّهِ ٱلسُّدُسُ﴾ [النساء: ١١]

«... (ሁለት ወይም) ከሁለት በላይ የሆኑ ሴቶች ብሆኑም ለእነርሱ (ሟቹ) ከተወው (ሐብት) ሁለት ሶስተኛ አለቸው። ለእርሱ ልጅ ብኖረው ለአባት እና ለእናቱም ከሁለታቸው ለእያንዳንዳቸው ከስድስት አንድ አላቸው። ለእርሱም ልጅ ባይኖረውና ወላጆቹ ብወርሱት ለእናቱ ሲሶው አላት። ለእርሱም ወንድሞችና እህቶች ብኖሩት ለእናቱም ከስድስት አንድ አላት። ...” *(አል-ንሳእ፡ 11)*

ይህ አንቀጽ ሙሉ እገዳንና ከፊል እገዳንም አንድ ላይ የያዜ ነው። የአባት መኖር እና የልጅ መኖር ወንድሞችን እንዳይወርሱ ከልክሏቸዋል። የወንድሞች መኖር ባይወርሱም እንኳ እናትን ከሲሶ ወደ 1/6 ዝቅ አድርጓታል። የልጆች መኖር ዴግሞ ወላጆችን እያንዳንዳቸውን ወደ 1/6 ዝቅ እንድሉ አድርጓቸዋል።

ሙሉ በሙሉ እገዳ /ሑጅቡ ሑርማን/ የማይመለከታቸው ስድስት ዓይነት ሰዎች ናቸው። እነሱም:-

01 ባል

02 ምስት

03 አባት

04 እናት

05 የሟች ወንድ ልጅ እና

06 የሟች ሴት ልጅ

እነዝህ በማንኛውም መልኩ ከውርስ ድርሻ አያጡም። የምጋርዳቸው ሰው ካለ ብቻ ከትልቁ ድርሻ ወደ ትንሹ ዝቅ ይላሉ እንጂ።

ሙሉ በሙሉ እገዳን አስመልክቶ ወራሾች በአራት ይከፈላሉ። እነሱም:-

01 ሌሎችን የምያግዱ ለራሳቸው የማይታገዱ እነሱም ፡ ወላጆችና ልጆች ናቸው።

02 ይታገዳሉ፤ ነገር ግን ሌሎችን ማገድ የማይችሉ። እነሱም:- በእናት በኩል ወንድም / እህት/ የሆኑ ናቸው።

03 ለራሳቸው የማይታገዱ ሌሎችንም የማያግዱ ናቸው። እነሱም:- ባል እና ምስት ናቸው።

04 ሌሎችንም ያግዳሉ፤ ለራሳቸውም ይታገዳሉ። እነሱም ከነዝህ ውጭ ያሉ ወራሾች ናቸው።

የእናት ልጆች (በእናት በኩል ብቻ ወንድም / እህት የሆኑት) በ 6 ሰዎች ይታገዳሉ። እነሱም፡:-

01 ልጅ

02 የልጅ ልጅ

03 አባት

04 አያት (ወንድ)

05 ሴት ልጅ

06 የወንድ ልጅ ሴት ልጅ ናቸው።

# ሸርከና /መጋራት/

ይህ ርዕስ ሸርከና /መጋራት/ የተባለበት ምክኒያት በእናት እና በአባት በኩል ወንድም ወይም እህት የሆኑት በእናት በኩል ብቻ ወንድማቸው ወይም እህታቸው ከሆኑት ጋር 1/3 እኩል በመካፈላቸው ነው። ይህ የምሆነው በሚከተለው መልኩ ነው። ለምሳሌ ወራሾቹ፡ ባል፣ እናት ወይም ሴት አያት እና በሁለቱም በኩል ወንድም ወይም እህት የሆኑ እንደዝሁም በእናት በኩል ብቻ ወንድም ወይም እህት የሆኑት በአንድ ውርስ ላይ ስሰባሰቡ ነው። ፆታቸው ቅልቅል ብሆንም ችግር የለውም፤ ነገር ግን ሴቶች ብቻ መሆን የለባቸውም፤ እንደዝያውም በአባት በኩል ብቻ የሆኑትንም አይጨምርም። በዝህ ምዕራፍ ውስጥ ይበልጥ ትኩረት የምሰጠው ለወንድማማቾቹ ነው።

ለምሳሌ፡- አንዷት ሴት ባሏን፣ እናቷን፣ በእናት በኩል ወንድሞቿ/ እህቶቿ/ የሆኑትን እና በሁለቱም በኩል ወንድሟ የሆነውን ሰው ትታ ብትሞት መደቡን ከስድስት አድርገን ለባል ግማሽ (3) እንሰጠዋለን፤ ለእናት 1/6 እንሰጣታለን፤ በእናት በኩል ወንድም/እህት/ ለሆኑት ዴግሞ 1/3 እንሰጣቸዋለን። በሁለቱም በኩል ወንድሟ የሆነው ያጣል። ምክኒያቱም ዐሰባህ (ያለ ገደብ ወራሽ) ስለሆነ። ዐሰባ የሆነ ሰው ከዙፈርዶች የተረፈውን ይወርሳል፤ የተረፈ ነገር ከለሌ ዴግሞ ያጣል። ምክኒያቱም ቡኻሪ እና ሙስልም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልህክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋልና፡-

«الحقو الفرائض بأهلها، فما بقي فلأولى رجل ذكر.» (رواه البخاري ومسلم)

«የውርስ ድርሻን ለባለ ድርሻው አድርሱ። የተረፈው ከሁሉም በበለጠ በዝምድና ቅርብ ለሆነው ወንድ ነው።» ብለዋል።

| 6 | |
|---|---|
| ባል | 3 |
| እናት | 1 |
| የእናት ልጆች | 2 |
| ወንድ ወንድም (በሁለቱም በኩል) | - |

ከላይ ያየነውን ክፍፍል እማሙ አሕመድ እና አቡ ሐኒፋ የደገፉት ሲሆን ከሶሐቦች ዴግሞ ዐሊይ፣ እብኑ መስዑድ፣ ኡበይ ብን ካዕብ፣ እብኑ አባስ እና አቡ ሙሳም

(ረ.ዐ) ደግፈውታል፤ ዑመርም መጀመሪያ ላይ ፈርደውበታል። እማሙ ሻፈዕ እና እማሙ ማሊክ ግን በሁለቱም በኩል ወንድም የሆኑት በእናት በኩል ብቻ ወንድም ከሆኑት ጋር 1/3 ውን በቁጥራቸው ልክ እኩል መካፈል አለባቸው እንጂ ማጣት የለባቸውም፤ ሴቷም እንደ ወንድ ትታያለች የምለውን አቋም ስደግፉ ከሶሓቦች ዑስማን እና ዘይድ ብን ሳቢት (ረ.ዐ) ደግፈውታል፤ ዑመርም ቡኃላ ላይ በዝህ ፈርደዋል።

ዑመር (ረ.ዐ) መጀመሪያ ላይ በከለከሏቸው ጊዜ በሁለቱም በኩል ወንድም የሆኑት ዑመርን፡- “ወስንልን አባታችን ድንጋይ ነው፤ እናታችንስ አንድ አይደለችምን? ወንድሞቻችን እየወረሱ እንዴት እናጣለን?” አሏቸው። ዑመርም (በንግግራቸው) ተብቃቅተው 1/3ውን ከእናታቸው ልጆች ጋር እኩል እንድካፈሉ ወሰኑላቸው።

አባታችን ድንጋይ ነው ማለታቸው የዐረቦች ፈሊጣዊ አነጋገር እንጂ አባታቸውን ለመንቀፍ አይደለም። ለማለት የፈለጉት አባታችንን ተውና እናታችን አንድ መሆኗን ብቻ አይተይ ወስንልን ለማለት ነው።

ቀደም ብለን የጠቀስነውን ሐዲስ ተንተርሰው ትክክለኛው አቋም የመጀመሪያው ነው ያሉ ምሁራን አሉ። አላህ ከሁሉም በላይ (ትክክል የሆነውን) አዋቂ ነው።

## የአያት እና የወንድሞች/የእህቶች/ አወራረስ

አያት ስንል የአባት አባት ለማለት ሲሆን ወንድም በማለት ዴግሞ ለማለት የተፈለገው በሁለቱም በኩል ወይም በአባት በኩል ብቻ ወንድም የሆኑትን ለማለት ነው።

ልጅ ካልኖረ የልጅ ልጅ እንደ ልጅ እንደምታየው ሁሉ አባት ካልኖረ አያትም እንደ አባት ይታያል። አባት ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ካለ 1/6 እንደምወርሰው ሁሉ አያትም ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ስኖር 1/6 ይወርሳል። ምክኒያቱም የሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ እሱንም ይመለከታልና።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-“… (ሟች) ልጅ ብኖረው (ለወላጆች) ለእያንዳንዳቸው ከተወው (ሐብት) አንድ ስድስተኛ አላቸው።…” (አለ-ንሳእ፡ 11)

አያት ዐሰባ ስለሆነ ብቻውን ሲሆን ሁሉንም ንብረት ይወርሳል፤ ዙፈርዶች ካሉ

ዴግሞ ከእነርሱ የተረፈውን ይወርሳል። አባት ካልኖረ አያት ሁሉም ቦታ ላይ እንደ አባት ይታያል። ከአባት የምለይበት ቦታ ብኖር ወንድሞች ባሉበት የውርስ ክፍፍል ላይ ብቻ ነው። አባት ወንድሞች እንዳይወርሱ ሙሉ በሙሉ ይጋርዳቸዋል። አያት ዴግሞ ከእነርሱ ጋር አብሮ ይወርሳል። ምክኒያቱም ከሟች ጋር ያላቸው ዝምድና ተመሳሳይ በመሆኑ ነው። ወንድሞች ለሟች የምቀርቡት በአባታቸው በኩል ሲሆን አያትም ለሟች የምቀርበው በሟች አባት (በራሱ ልጅ) በኩል ነው።

ልብ በሉ! የአያትን እና የወንድሞችን ጉዳይ አስመልክቶ ሰለፎች ሁለት ዓይነት አመለካከት አላቸው። አንደኛው ወንድም ከአያት ጋር ይወርሳል የምል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አያት በአባት ቦታ ስለሆነ ወንድሞች እንዳያገኙ ያደርጋል የምለው ነው። አብረው ይወርሳሉ ከምሉት መካከል: ዐሊ.ይ፣ እብኑ መስዑድ፣ እና ዘይድ ብን ሳቢት (ረ.ዐ) ይገኙበታል። አላህ ይዘንላቸውና እማሙ ማሊክ እና እማሙ ሻፊዒይም አወራረሳቸው ላይ ኽላፍ ብኖራቸውም ይህንን አቋም ደግፈዋል።

ወንድሞች አይወርሱም የምለውን አቋም ከደገፉት መካከል ዴግሞ አቡበክር አስ-ስዲቅ እና እናታችን ዓእሻን (ረ.ዐ) ጨምሮ አስራ ምናምን ሶሓቦች (ረ.ዐ) ደግፈውታል። ከነዝህ መካከል እብን ዐባስ፣ ጃብር፣ አቢሙሣ፣ እና ዕምራን እብኑ ሑሰይን (ረ.ዐ) ይገኙበታል። እንደዝሁም በርካታ ታቢዒዮችና እማም አቡ ሐኒፋ፣ … እስሐቅ፣… እማሙ አሕመድ፣ ሸይኹል እስላም ብን ተይሚያ እና ተማሪያቸው እውቁ ምሁር እብኑል ቀይም፣ ሸይኽ አልሙጀድድ ሙሐመድ ብን አብዱልወሃብ አላህ ይዘንላቸው ይህን አቋም ደግፈዋል። በርካታ ማስረጃዎች ስላሉት ትክክለኛውም ይህ ነው ይባላል። አላህ ከሁሉም በላይ አዋቂ ነው!

አያት ከወንድሞች/ እህቶች/ ጋር ስወርስ በአምስት መንገዶች ነው። እነሱም:-

01 አባት ካልኖረ: ምክኒየቱም አባት ዐሰባ ሆኖ ጨርሶ ይወርሳልና።

02 ከእርሱ ጋር ዙፈርዶች ብቻ ስኖሩ: -በዝህ ጊዜ 1/6 ይወርሳል። ከክፍፍሉ ቡኃላ የተረፈ ነገር ካለ ዐሰባ ሆኖ ጨርሶ ይወርሳል።

03 ከእርሱ ጋር ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ስኖር: -በዝህ ጊዜ 1/6 ብቻ ይወርሳል።

04 ከእርሱ ጋር ወንድም/ እህት/ የሆኑት ብቻ ስኖሩ: - በዝህ ጊዜ 1/3 ከመውሰድ ወይም ከመካፈል የተሻለው ድርሻ ታይቶ ይሰጠዋል። የወንድሞች ቁጥር ከሁለት ካልበለጠ መካፈሉ ይሻለዋል።

05 ከእርሱ ጋር ወንድም/ እህት/ የሆኑት እና ዙፈርዶች ስኖሩ: - በዝህ ጊዜ 1/6

ከመውሰድ ወይም ከመካፈል ወይም ቀሪ አንድ ሦስተኛ (ሱሉሱል ባቂ) ከመውሰድ የተሻለው ድርሻ ታይቶ ይሰጠዋል። ዙፈርዶች በመብዛታቸው የተነሳ የምተርፍ ነገር ብታጣ ወንድሞች ያጣሉ። አያት ግን በቁርአን የተደነገገለት አንድ ስድስተኛ ድርሻ ስላለው ከውርሱ ማጣት አይችልም። ዐውል የተባለው አሰራር ሥራ ላይ ብውልም እንኳ።

ሌላው አየት እና ወንድሞችን አስመልክቶ ያለው፡ በአንድ የውርስ ክፍፍል ላይ አያት በሁለቱም በኩል ወንድም ከሆኑት እና በአባት በኩል ብቻ ወንድም ከሆኑት ጋር ብገኝ የውርስ መደቡ በቁጥራቸው ልክ ይሆናል። አያትም ከወንድሞች ጋር እኩል ይካፈላል። በምካፈሉበት ጊዜ በሁለቱም በኩል ወንድም የሆኑት በአባት በኩል ብቻ ወንድም የሆኑትን ወደ ራሳቸው በመቁጠር ቁጠራቸውን አበርክተው የአያት ድርሻ እንድቀንስ ያደርጋሉ። በመቀጠል በሁለቱም በኩል ወንድም የሆኑት እያሉ በአባት በኩል ወንድም የሆኑት መውረስ ስለማይችሉ በሁለቱም በኩል ወንድም የሆኑት በአባት በኩል ብቻ ወንድም ከሆኑት የደረሳቸውን ድርሻ በማስመለስ ብቻቸውን ውርሱን ይወስዳሉ።

## አል-አክደሪያህ /ተወሳሳቢ/

አል-አክደሪያ /ተወሳሳቢ/ የተባለበት ምክኒያት በሟች እህት ላይ ስለተወሳሰበባት ነው ይባላል። ምክኒያቱ ዴግሞ ብዙ ተወስኖላት ትንሽ በመውሰዷ ነው። በሌላ ምክኒያት ነው ያሉም አሉ። ይህ የምሆነው ምስት ባሏን፣ እናቷን፣ አያቷን እና እህቷን (በሁለቱም በኩል ወይም በአባት በኩል ብቻ) እህት የሆነችውን ትታ ስትሞት ነው።

አያት እና ወንድሞችን አስመልክቶ መሆን የነበረበት አያት እያለ ወንድም/እህት/ የሆኑት መውረስ አልነበረባቸውም፤ ነገር ግን እዝህ ቦታ ላይ ብቻ ትወርሳለች ያሉ ስላሉ አወራረሳቸው እንደሚከተለው ይሆናል።

1/6 የምወርስ ሰው ስላለ መደቡን ከስድስት እናደርጋለን። በመቀጠል ሟች ልጅ ስለላት ለባል ግማሽ (3) እንሰጠዋለን፤ 1/3ውን ለእናት እንሰጣታለን፤ እህት ለሆነችውም ግማሽ (3) እንሰጣታለን፤ የተረፈውን አንዱን ለአያት እንሰጠዋለን። በዝህ ጊዜ ከስድስት የነበረው መደብ ወደ ዘጠኝ ከፍ ይላል። በመቀጠል አያት እና

እህት የደረሳቸውን ድርሻ ቀላቅለው አያት ሁለት እጅ ስወስድ እህት አንድ እጅ ትወስዳለች።

ድርሻቸውን ስንመለከት አያት የደረሰው አንድ ሲሆን እህት የደረሳት ሦስት ነው። ድርሻቸውን በምቀላቅሉበት ጊዜ አራት ይሆናል። አራትን ለሦስት[1] ማካፈል ስለማይቻል ሶስትን በዋናው መደብ (በዘጠኝ) እናባዛለን። 27 ይሆናል። ከዝያም አያት ሁለት እጅ (18) ስወስድ እህት ዴግሞ አንድ እጅ (9) ትወስዳለች። መጨረሻ ላይ ስታይ እህት የደረሳት ድርሻ 1/6 ሲሆን አያት ዴግሞ 1/3 ደርሶት ይገኛል። በዝህም ምክኒያት እህት ነገሩ ይወሳሰብባታል። ምክኒያቱም መጀመሪያ ላይ የደረሳት ድርሻ ብዙ ነበር። ቡኃላ ላይ ግን ቀንሶባት ተገኘ። በዝህም የተነሳ ተወሳሳቢ እንደተባለ ይነገራል።

በላጩ አካሄድ ግን እህት ከአያት ጋር መውረስ አትችልም፤ እርሱ ካለ ከውርስ ድርሻ አይኖራትም የምለው ነው። ተብሏል። አላህ ከሁሉም በላይ አወቂ ነው።

## የውርስ ድርሻን ማስተካከል /ተስሒሑል ፈራእድ/

ይህም ማለት የውርስ መደቡ ከስንት መሆን እንዳለበት፣ እያንዳንዱ ወራሽ ምን ያህል ማግኘት እንዳለበት እና ለወራሾች ያለ ቀሪ እንዴት መካፈል እንደምችል ማውቅ ማለት ነው።

ምሁራን የተስማሙበት የውርስ ድርሻ መሠረቶች ሰባት ናቸው። እነሱም፡-

01 መደብ ሁለት

02 መደብ ሦስት

03 መደብ አራት

04 መደብ ስድስት

05 መደብ ስምንት

06 መደብ አስራ ሁለት እና

1 አንድ ወንድ እንደ ሁለት ሴቶች ስለምቆጠር እሱን ሁለት አድርገን እህት የሆነችውን አንድ አድርገን ስንደምር 3 ይሆናል።

07 መደብ ሃያ አራት ናቸው። በተቀሩት ሁለቱ ላይ ልዩነት ያለ ሲሆን እነሱም መደብ 18 እና መደብ 36 ናቸው።

ለምሳሌ:-

ግማሽ ከሁለት ይገኛል።

ሲሶ (1/3) ከሦስት ይገኛል።

ሩብ (1/4) ከአራት ይገኛል።

አንድ ስድስተኛ (1/6) ከስደስት ይገኛል።

አንድ ስምንተኛ (1/8) ከስምንት ይገኛል።

ለምሳሌ፡ በአንድ የውርስ ክፍፍል ላይ 1/4 እና 1/6 የምያገኙ ሁለት ሰዎች ብኖሩ መደቡ ከ 12 ይሆናል። እንደዝያውም 1/8፣ 1/6 ወይም 1/3 የምያገኙ ባለ ድርሻዎች ብኖሩ መደቡ ከ 24 ይሆናል። ምክኒያቱም 1/8፣ 1/6 እና 1/3 ሁሉም ከ24 ልገኙ ስለምችሉ ነው።

## ምሳሌ

01 አንዲት ሴት ባሏን እና ወንድሟን ትታ ብትሞት የውርስ መደቡ ከሁለት ይሆናል። አንዱን ባል ስወስድ አንዱን ዴግሞ ወንድም ይወስዳል። ምክኒያቱም ምስት ልጅ ከለላት የባል ድርሻ ግማሽ ነውና። ወንድም ዴግሞ ዐሰባ ስለሆነ የተረፈውን ግማሽ ይወርሳል።

02 ወራሾቹ አባት እና እናት ብቻ ብሆኑ መደባቸው ከ 3 ይሆናል። ምክኒያቱም ሟች ልጅ ከለለው እናት ከልጁ ንብረት 1/3ውን ትወርሳለች። አባት ዴግሞ ዐሰባ (ያለ ገደብ ወራሽ) ስለሆነ የተረፈውን ሁለቱን ይወርሳል።

03 ወራሾቹ ምስት እና ወንድም ብቻ ከሆኑ መደቡ ከ4 ይሆናል። ምክኒያቱም ሟች ልጅ ከለሌው የምስት ድርሻ 1/4 ስለሚሆን 1/4ውን እንሰጣታለን። የተረፈውን ዐሰባ ስለሆነ ለወንድም እንሰጠዋለን።

04 አንድ ሰው አባቱን፣ እናቱን እና ልጁን ትቶ ብሞት የውርስ መደቡ ከስድስት ይሆናል። እናት እና አባት እያንዳንዳቸው 1/6 ስወርሱ የተረፈውን ልጅ ዐሰባ ስለሆነ ጨርሶ ይወርሳል። ምክኒያቱም ሟች ልጅ ካለው እናት እና አባት የምወርሱት 1/6 ብቻ ነውና።

05 አንድ ሰው ምስቱን እና ልጁን ትቶ ብሞት የውርስ መደቡ ከስምንት ይሆናል። ምስት 1/8 ስትወስድ ልጅ ደግሞ ዐሰባ ስለሆነ የተረፈውን ጨርሶ ይወርሳል።

06 አንድ ሰው ምስቱን፣ እናቱን እና አጎቱን ትቶ ብሞት የውርስ መደቡ ከ 12 ይሆናል። ምክኒያቱም 1/4 እና 1/3 የምወርሱ ሰዎች ስላሉ። ሟች ልጅ ስለሌለው ለምስት 1/4 = 3 እንሰጣታለን። ለእናት ደግሞ 1/3 = 4 እንሰጣታለን። የተረፈውን 5ቱን ለአጎት እንሰጠዋለን ዐሰባ ስለሆነ።

07 አንድ ሰው አባቱን፣ ምስቱን እና ልጁን ትቶ ብሞት የውርስ መደቡ ከ 24 ይሆናል። ምክኒያቱም 1/8 እና 1/6 የምገኘው ከ 24 ነውና። አባት 1/6 = 4 ስወርስ ምስት ደግሞ 1/8 = 3 ትወርሳለች። ልጅ ደግሞ ዐሰባ ስለሆነ የተረፈውን ጨርሶ ይወርሳል።

## ዐውል

በዝህ ዘርፍ ዐውል የምባለው መደቡን (ዕጣውን) በመጨመር የወራሾችን ድርሻ እንድቀንስ ማድረግ ነው። ይህም የምሆነው በመጀመሪየው የውርስ መደብ የወራሾችን ድርሻ ያለ ቀሪ ለወራሾች በትክክል ማድረስ ሳይቻል ስቀር ነው። ይህን አሰራር ከዐብደላህ እብን ዐባስ በቀር ሁሉም ሶሃቦች ተስማምተውበታል። ሙስልሞችም እስካሁን ድረስ እየሰሩበት ይገኛሉ።

ዐውል የምገኝባቸው መደቦች ሦስት ናቸው። እነሱም፡-

01 መደብ ስደስት

02 መደብ አስራ ሁለት እና

03 መደብ ሃያ አራት ናቸው።

**መደብ ስደስት፡** መደብ ስድስትን እስከ አስር ማሳደግ ይቻላል። ይህም ማለት በመደብ ስደስት ውርሱን ለወራሾች በትክክል ማድረስ ካልተቻለ መደቡን ወደ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ እና አስር በማሳደግ መስራት ማለት ነው።

**ለምሳሌ፡-** መደብ ስድስትን ወደ ሰባት ማሳደግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት

ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም ባል፣ እህት እና ሴት አያት ሲሆኑ ነው። እህት ስንል በእናትም በአባትም በኩል እህት የሆነች ለማለት ነው። በዝህ ጊዜ መደቡ ከስድስት ይሆናል። ምክኒያቱም አንድ ስድስተኛ የምደርሰው ሰው ስላሌ። እሷም አያት ነች። ለባል ግማሽ = 3 እንሰጠዋለን። ለእህትም እንደዝሁ ግማሽ = 3 እንሰጣታለን ብቻዋን ስለሆነች። ለአያት 1/6 = 1 እንሰጣታለን። በዝህ መልኩ ከስድስት የነበረው መደብ ወደ ሰባት ከፍ ይላል።

መደብ ስድስትን ወደ ስምንት ማሳደግ የምቻለው በምከተለው መልኩ ነው። ይህም ባል፣ ሁለት እህቶች እና እናት ሲሆኑ ነው። እህት ስንል በሁለቱም በኩል እህት የሆነች ለማለት ነው። በዝህ ጊዜ መደቡን ከስድስት እናደርጋለን። ምክኒያቱም 2/3 እና 1/6 የምገኘው ከ 6 ነውና። ለባል ግማሹን = 3 እንሰጠዋለን፤ ለሁለቱ እህቶች 2/3 = 4 እንሰጣታለን፤ ለእናት ዴግሞ 1/6 = 1 እንሰጣታለን። አጠቃላይ ስንደምረው ስምንት ስለምመጣ መደቡ ከስድስት ወደ ስምንት ከፍ ይደረጋል።

መደብ ስድስትን ወደ ዘጠኝ ከፍ ማድረግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም፡- ባል፣ እናት፣ እህት (በሁለቱም በኩል) እህት (በአባት በኩል) እና ወንድም (በእናት በኩል) ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ መደቡ ከስድስት ይሆናል። ባል ግማሽ = 3 ይወስዳል፣ በሁለቱም በኩል እህት የሆነችውም እንደዝያው ግማሽ = 3 ትወስዳለች። የተቀሩት ሦስቱ እያንዳንዳቸው 1/6 = 1 ስወስዱ ስድስት የነበረው መደብ ወደ ዘጠኝ ከፍ ይላል።

መደብ ስድስትን ወደ አስር ከፍ ማድረግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም፡- ባል፣ እናት፣ እህት (በሁለቱም በኩል) እህት (በአባት በኩል) እና ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ ወንድሞች ወይም እህቶች (በእናት በኩል) ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ መደቡ ከስድስት ይሆናል። ባል ግማሽ = 3 ይወስዳል፣ በሁለቱም በኩል እህት የሆነችውም እንደዝያው ግማሽ = 3 ትወስዳለች። በአባት በኩል እህት የሆነችው 1/6 = 1 ትወስዳለች። እናትም እንደዝሁ 1/6 = 1 ትወስዳለች። የእናት ልጆች ደግሞ 1/3 = 2 ይወስዳሉ። በዝህ መልኩ ስድስት የነበረው ወደ አስር ከፍ ይላል።

መደብ አስራ ሁለት፡- መደብ አስራ ሁለትን በጎደሎ ቁጥሮች ብቻ እስከ አስራ ሰባት ማሳደግ ይቻላል። ይህም ማለት በመደብ አስራ ሁለት ውርሱን ለወራሾች በትክክል ማድረስ ካልተቻለ መደቡን ወደ አስራ ሦስት፣ አስራ አምስት እና አስራ

ሰባት በማሳደግ መሥራት ማለት ነው። ነገር ግን በአስራ አራት እና በአስራ ስደስት መሥራት አይቻልም።

ለምሳሌ፡- መደብ አስራ ሁለትን ወደ አስራ ሦስት ማሳደግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም፡- ምስት፣ እናት እና ሁለት እህቶች (በአባት በኩል) ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ መደቡን ከ 12 እናደርጋለን። ለምስት 1/4 = 3 እንሰጣታለን፤ ለእናት 1/6 = 2 እንሰጣታለን። ለእህቶቹ 2/3 = 8 እንሰጣቸዋለን። በዝህ መልኩ 12 የነበረው መደብ ወደ 13 ከፍ ይላል።

ወደ አስራ አምስት ማሳደግ መደብ አስራ ሁለትን ወደ አስራ አምስት ማሳደግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም፡- ምስት፣ እናት፣ እህት በእናት በኩል፣ እህት በአባት በኩል እና እህች (በሁለቱም በኩል) ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ መደቡን ከ 12 እናደርጋለን። ለምስት 1/4 = 3 እንሰጣታለን፤ ለእናት 1/6 = 2 እንሰጣታለን፤ በእናት በኩል እህት ለሆነችውም 1/6 = 2 እንሰጣታለን፤ በአባት በኩል እህት ለሆነችውም 1/6 = 2 እንሰጣታለን፤ በሁለቱም በኩል እህት ለሆነችው ዴግሞ ግማሽ = 6 እንሰጣታለን። በዝህ መልኩ 12 የነበረው መደብ ወደ 15 ከፍ ይላል።

ወደ አስራ ሰባት ማሳደግ መደብ አስራ ሁለትን ወደ አስራ ሰባት ማሳደግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም፡- ምስት፣ እናት፣ እህቶች/ወንድሞች በእናት በኩል፣ እህት በአባት በኩል እና እህች (በሁለቱም በኩል) ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ መደቡን ከ 12 እናደርጋለን። ለምስት 1/4 = 3 እንሰጣታለን፤ ለእናት 1/6 = 2 እንሰጣታለን፤ በእናት በኩል ብቻ እህት/ወንድም ለሆኑት 1/3 = 4 እንሰጣቸዋለን፤ በአባት በኩል እህት ለሆነችው 1/6 = 2 እንሰጣታለን፤ በሁለቱም በኩል እህት ለሆነችው ዴግሞ ግማሽ = 6 እንሰጣታለን። በዝህ መልኩ 12 የነበረው መደብ ወደ 17 ከፍ ይላል።

መደብ ሃያ አራት፡- መደብ ሃያ አራትን ማሳደግ የምቻለው አንድ ጊዜ ብቻ ወደ መደብ ሃያ ሰባት ነው። ይህም በመደብ ሃያ አራት ውርሱን ለወራሾች በትክክል ማድረስ ካልተቻለ መደቡን ወደ ሃያ ሰባት ማሳደግ ማለት ነው።

ለምሳሌ፡- መደብ ሃያ አራትን ወደ ሃያ ሰባት ማሳደግ የምቻለው ወራሾቹ የሚከተሉት ሰዎች ሲሆኑ ነው። እነሱም፡- ምስት፣ እናት፣ አባት እና ሁለት ሴት ልጆች ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ መደቡን ከ 24 እናደርጋለን። ምክኒያቱም 1/8 እና

1/6 የምወርሱ ሰዎች ስላሉ። ለምስት 1/8 = 3 እንሰጣታለን፤ ለእናት 1/6 = 4 እንሰጣታለን፤ ለአባትም እንደዝያው 1/6 = 4 እንሰጠዋለን፤ ለሁለቱ ሴት ልጆች ዴግሞ 2/3 = 16 እንሰጣቸዋለን። በዝህ መልኩ 24 የነበረው መደብ ወደ 27 ከፍ ይላል።

## አመዳደብ

መደቡ ከስንት መሆን እንዳለበት ለመወሰን መጀመሪያ ወራሾች መታወቅ አለባቸው። ወራሾች አራት ዐይነት ናቸው። እነሱም:-

01 ወንድ ዐሰባዎች ብቻ

02 ወንድ እና ሴት የተቀላቀሉበት ዐሰባ (ዐሰባ ብልገይር)

03 ዙፈርድ ብቻ

04 ዐሰባ እና ዙፈርድ ቅልቅል ናቸው።

ቀደም ብለን እንደገለጽነው ዐሰባ ማለት ብቻውን ሲሆን ሁሉንም ንብረት ጨርሶ የምወርስ ማለት ሲሆን ዙፈርዶች አብረውት ካሉ ግን ከእነሱ የተረፈውን የምወርስ ነው። ካልተረፈም ያጣል።

ዙፈርድ የምባሉት ዴግሞ የውርስ መጠናቸው በቁርኣን የተደነገገላቸው ናቸው። እነሱ ካሉ የውርስ መደቡ በእነሱ በኩል ይታያል።

ወራሾቹ ወንድ ዐሰባዎች ብቻ ከሆኑ መደቡ በቁጥራቸው ልክ ይሆናል። ለምሳሌ: ወራሾቹ ሦስት ወንድ ልጆች ቢሆኑ መደቡ በቁጥራቸው ልክ ከ 3 ይሆንና አንዳንድ ይወስዳሉ።

ወንድ እና ሴት ዐሰባ ቅልቅል ከሆኑ ለወንዱ ሁለት እጅ ስሰጠው ለሴቷ አንድ እጅ ይሰጣታል። ለምሳሌ:- ወራሾቹ አንድ ወንድ ልጅ እና ሁለት ሴት ልጆች ቢሆኑ መደቡ በቁጥራቸው ልክ ከ 4 ይሆናል፤ ምክኒያቱም፣ አንድ ወንድ በሁለት ሴቶች ስለምቆጠር። ከዝያም ወንዱ 2 ስወስድ ሴቶቹ ዴግሞ አንዳንድ ይወስዳሉ።

ዐሰባ እና ዙፈርድ ቅልቅል ከሆኑ ዴግሞ መደቡ በዙፈርዶች በኩል ታይቶ ይወሰናል። ለምሳሌ:-

ወራሾቹ:- ባል፣ አንድ ወንድ ልጅ እና አንዲት ሴት ልጅ ቢሆኑ መደቡ የምወሰነው ባልዬው ታይቶ ነው። ስለዝህ መደቡ ከ 4 ይሆናል። ባል 1/4 = 1 ይሰጠዋል፤ ቀሪውን 3ቱን ወንዱ ሁለት እጅ ስወስድ ሴቷ አንድ እጅ ትወስድና ዐሰባ ሆነው ጨርሰው ይወርሳሉ።

## አራቱ ምልከታዎች

ከወራሾች መካከል አንድ ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ ዙፈርዶች ቢኖሩ አራቱ ምልከታዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። እነሱም:-

01 መመሳሰል (አት-ተማሱል)

02 አንዱ በአንዱ ውስጥ መገኘት /መግባት/ (አት-ተዳኩል)

03 መስማማት (አት-ተዋፉቅ)

04 መለያየት (አት-ተኻሉፍ) ናቸው።

## መመሳሰል (አት-ተማሱል)

መመሳሰል የምባለው ወራሾቹ የምደርሳቸው ድርሻ ተመሳሳይ ወይም አንድ ዐይነት ሲሆን ነው። በዝህ ጊዜ በአንዱ ብቻ በመብቃቃት መደቡን እንወስናለን።ለምሳሌ:- ወራሾቹ ባል እና እህት (በሁለቱም በኩል እህት የሆነች) ቢሆኑ መደቡ ከሁለት ይሆናል። ምክኒያቱም ባል ድርሻው ግማሽ ሲሆን የእህትም እንደዝያው ግማሽ ነውና። ስለዝህ መደቡን ከሁለት አድርገን አንዳንድ እንሰጣቸዋለን።

| 2 | |
|---|---|
| ባል | 1 |
| እህት | 1 |

# አንዱ በአንዱ ውስጥ መገኘት /መግባት/ (አት-ተዳኩል)

| 6 | |
|---|---|
| እናት | 1 |
| ወንድሞች | 2 |
| አጎት | 3 |

አንዱ በአንዱ ውስጥ መገኘት ወይም መግባት የምባለው አንዱ ለአንዱ ያለቀሪ ስካፈል ነው። ለምሳሌ፡ 6 እና 3፣ 8 እና 4 የመሳሰሉት ሲሆኑ ነው። በዝህ ጊዜ በትልቁ በመብቃቃት ትንሹን እንተወዋለን። ለምሳሌ፡ ወራሾቹ እናት፣ ሁለት ወንድሞች በእናት በኩል እና አጎት ቢሆኑ የውርሱ ክፍፍል እንደሚከተለው ይሆናል። የእናት ድርሻ 1/6 ስለሆነ የምገኘው ከ6 ነው። የወንድሞች ድርሻ ዴግሞ 1/3 ነው። የምገኘውም ከ 3 ነው። አጎት ዐሰባ ስለሆነ ከእነርሱ የተረፈውን ይወርሳል። በመቀጠል መደቡን ለመሰየም 6ን እና 3ን እንመለከታለን።ስንመለከት 3 በስድስት ውስጥ የምገኝ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዝህ ሶስትን በመተው መደቡን ከ 6 እናደርጋለን።

እናት፡ 1/6 = 1

የእናት ልጆች/ወንድሞች፡ 1/3 = 2

አጎት፡ የተረፈውን = 3 ይወርሳል።

# መስማማት (አት-ተዋፉቅ)

መስማማት የምባለው ሁለት እና ከዝያ በላይ የሆኑ ወራሾች በአንድ ነገር ላይ ስስማሙ ነው። ይኸውም እያንዳንዱ ወራሽ የውርስ ድርሻው ከስንት መደብ ልደርሰው እንደምችል ከታወቀ በኋላ መደባቸው መስማማት የምችሉባቸውን ትንሹን የጋራ ብዜታቸውን በመውሰድ ለአንዱ መደብ እናካፍላለን። ተካፍሎ የተገኘውን ውጤት

ከአንደኛው መደብ ጋር እናባዛለን። ተባዝቶ የተገኘውም ውጤት የውርስ መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል።

ለምሳሌ:- ሁለት የተለያዩ ወራሾች ብኖሩና አንዱ 1/4 የምደርሰው ቢሆንና ሌላኛው ዴግሞ 1/6 የምደርሰው ቢሆን 1/4 የምወርሰው መደቡ ከ 4 ይሆናል። 1/6 የምደርሰው ዴግሞ መደቡ ከ6 ይሆናል። ታዲያ እነዝህ ሁለቱ ወራሾች በአንድ የውርስ ክፍፍል ላይ ብገኙ በቅድሚያ ሁለቱ መደቦች የምስማሙበትን የጋራ ቁጥር እንመለከታለን። በምንመለከትበት ጊዜ ሁለቱም ቁጥሮች ለሁለት መካፈል የምችሉ ሆነው እናገኛቸዋለን።ሁለቱንም ለሁለት ስናካፍላቸው ግማሽ ግምሽ ይኖራቸዋል። ስለዝህ የአንዱን ግማሽ እንወስድና በአንደኛው ሙሉ እናባዛለን። የተገኘውም ውጤት የውርስ መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል።

ለምሳሌ:- ወራሾቹ ባል፣ እናት፣ ሶስት ወንድ ልጆች እና አንዷት ሴት ልጅ ቢሆኑ ባል ድርሻው 1/4 ስለሆነ የምገኘው ከ 4 ነው፤ እናት ድርሻዋ 1/6 ስለሆነ የምገኘው ከ 6 ነው፤ ልጆቹ ዴግሞ ከእነዝህ የተረፈውን ወንዱ ሁለት እጅ ስወስድ ሴቷ አንድ እጅ ይወስዳሉ። በመቀጠል አራትን እና ስድስትን ስንመለከት በግማሽ ወይም በ 1/2 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። የ6 ግማሽ 3 ሲሆን የ4 ግማሽ ዴግሞ 2 ነው። ስለዝህ የአንዱን ግማሽ ወስደን ከሌላኛው ሙሉ ጋር ስናባዛ መደባቸውን እናገኛለን። ይኸውም $4/2 \times 6 = 12$ ወይም $6/2 \times 4 = 12$ ይሆናል። ይህም ማለት $3 \times 4 = 12$ ወይም $2 \times 6 = 12$ ማለት ነው። ስለዝህ መደባቸው ከ 12 ይሆናል ማለት ነው። ክፍፍሉም እንደሚከተለው ይሆናል።

ባል ¼ = 3 ስደርሰው እናት ዴግሞ 1/6 = 2 ይደርሳታል። የተቀረውን ሦስቱ ወንዶቹ ሁለት ሁለት ስወስዱ ሴቷ ልጅ አንድ ይደርሳታል።

| 12 | |
|---|---|
| ባል | 3 |
| እናት | 2 |
| ወንድ ልጅ | 2 |
| ወንድ ልጅ | 2 |
| ወንድ ልጅ | 2 |
| ሴቷ ልጅ | 1 |

# መለያየት /አለመስማማት/ አት-ተኻሉፍ/

ይህ ደግሞ የወራሾች መደብ በማንኛውም መልኩ ሳይስማማ ስቀር ነው። ለምሳሌ 3 እና 4ን ብንወስድ በማንኛውም መልኩ አይስማሙም። በዝህ ጊዜ አንዱን መደብ በሌላኛው በማባዛት መደቡን እንሰይማለን። የዝህን ምሳሌ በሚከተሉት ወራሾች ውስጥ መመልከት እንችላለን።

ለምሳሌ ወራሾቹ፡- ባል፣ እናት እና ወንድም ቢሆኑ ባል ግማሽ ስለምወርስ መደቡ ከ2 ይሆናል፤ እናት 1/3 ስለምትወርስ መደቧ ከ 3 ይሆናል፤ ወንድም ደግሞ ዐሰባ ስለሆነ ከእነርሱ የተረፈውን ይወርሳል።ወንድም ስንል በሁለቱም በኩል ወንድም የሆነ ለማለት ነው። የባል እና የእናትን መደብ (2 እና 3ን) ስንመለከት አይስማሙም። ስለዝህ አንዱን በአንዱ እናባዛለን። 2×3 = 6 ስለሚሆን መደባቸው ከ 6 ይሆናል ማለት ነው።

| 6 | |
|---|---|
| ባል | 3 |
| እናት | 2 |
| ወንድም | 1 |

ባል ድርሻው ግማሽ ስለሆነ 3 እንሰጠዋለን።

እናት ድርሻዋ 1/3 ስለሆነ 2 እንሰጣታለን።

ወንድም ደግሞ ዐሰባ ስለሆነ ከእነርሱ የተረፈውን 1ይወርሳል።

# የማይካፈል ሲሆን (አል-እንከሳር)

ይህ ማለት ከፍል ድርሻ ለወራሾች ያለቀሪ ሳይካፈል ስቀር ነው። በዝህ ጊዜ የደረሳቸው ድርሻ መጠን እና የወራሾቹ ቁጥር ይታያል። የምስማሙ ከሆነ የምስማሙበት የጋራ ቁጥራቸው ይወሰድና ከዋናው መደብ ጋር ይባዛል። ተባዝቶ የተገኘውም ውጤት

ዋና መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። የማይስማሙ እና የተለያዩ ከሆኑ ደግሞ መደቡን በወራሾቹ ቁጥር እናባዛለን፤ ተባዝቶ የተገኘውም ውጤት ዋና መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። አሁን የሁለቱንም ምሣሌዎች በቅደም ተከተል እንመለከታለን። መጀመሪያ የምስማሙበትን እንመልከት።

ለምሣሌ፡- ወራሾቹ አንዲት ምስትና ስድስት አኅቶች ቢሆኑ መደቡ ከ 4 ይሆናል። ምስት 1/4 ስሰጣት የተቀረውን ስድስቱ አኅቶች ይካፈላሉ። አኅቶቹ የደረሳቸው ድርሻ እና ቁጥራቸው እኩል ስላልሆነ የምስማሙበትን መንገድ እንፈልጋለን። በ 1/3 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዝህ ሁለቱንም ቁጥሮች (3 እና 6ን) በ 1/3 እናባዛቸዋለን። $1/3 \times 3 = 1$ እና $1/3 \times 6 = 2$ ስለሚሆን 2ን ወስደን በዋናው መደብ በ 4 እናባዛለን። $2 \times 4 = 8$ ስለሚሆን 8 ዋና መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። ምስት የስምንትን $1/4 = 2$ ስትወስድ አኅቶቹ የተቀረውን ስድስቱን ይወስዱና አንዳንድ ይካፈላሉ።

አሁን ደግሞ የምለያዩበትን ምሣሌ እንመለከታለን። ወራሾቹ አንዲት ምስት፣ አንድ ወንድ ልጅ እና አንዲት ሴት ልጅ ቢሆኑ መደባቸው ከስምንት ይሆናል። ምስት አንድ ስምንተኛ ስትወስድ የቀረውን ሰባቱን ወንዱ ልጅ ሁለት እጅ ስወስድ ሴቷ ልጅ አንድ እጅ በመውሰድ ዐሰባ ሆነው ጨርሰው ይወርሳሉ። የልጆቹን ቁጥር እና የደረሳቸውን ድርሻ ስንመለከት የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ ምክኒያቱም፣ የደረሳቸው ድርሻ 7 ሲሆን ቁጥራቸው ደግሞ 3 ነውና[1] ። 7 እና 3 ደግሞ የተለያዩ (የማይስማሙ) ናቸው። ስለዚህ ሦስትን በመውሰድ በዋናው መደብ ከስምንት ጋር እናባዛለን። $3 \times 8 = 24$ ስለሚሆን መደቡ ከ 24 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል።

| 24 | |
|---|---|
| ምስት | 3 |
| ወንድ ልጅ | 14 |
| ሴቷ ልጅ | 7 |

ምሳሌ 2፡ ወራሾቹ ባል እና አምስት ወንድ ልጆች ቢሆኑ መደባቸው ከ 4 ይሆናል። ለባል $1/4 = 1$ እንሰጠዋለን። ቀሪውን ሦስቱን ልጆቹ ይወስዳሉ። የልጆቹን ቁጥር እና ድርሻቸውን ስንመለከት ልዩነት እናገኛለን። ምክኒያቱም ልጆቹ 5 ሲሆኑ ድርሻቸው ደግሞ 3 ነውና። ስለዚህ የልጆቹን ቁጥር አምስትን በመውሰድ

1 የልጆቹ ቁጥር ሦስት የሆነበት ምክኒያት አንድ ወንድ በሁለት ሴቶች ስለምቆጠር ነው።

በዋናው መደብ ከ አራት ጋር እናባዛለን። ተባዝቶ የተገኘውም ውጤት ዋና መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። ይኸውም 5 × 4 = 20 ስለሚሆን መደቡ ከ 20 ይሆናል ማለት ነው። ምስት 1/4 = 5 ስደርሳት ቀሪውን 5ቱ ልጆች እኩል ሦስት ሦስት ይካፈላሉ።

| 20 | |
|---|---|
| ባል | 5 |
| ልጅ | 3 |
| ልጅ | 3 |
| ልጅ | 3 |
| ልጅ | 3 |
| ልጅ | 3 |

ከዝህ በላይ መስማማት እና መለያየት ብለን ያየናቸው ምሳሌዎች ክፍፍሉ በአንድ ወገን ላይ ብቻ ያለ ቀሪ እኩል ሳይካፈል ስቀር ነው። ነገር ግን ክፍፍሉን ሁለት እና ከዝያ በላይ በሆኑ ወገኖች ላይ ያለ ቀሪ እኩል ማካፈል ካልተቻለ በዝህ ጊዜ የእያንዳንዱን ወገን ቁጥር (ብዛት) እና የደረሳቸውን ድርሻ ቀደም ብለን ባየናቸው በሁለቱ መመዘኛዎች ዜዴዎች ማለትም በመስማማት እና መለያየት እመለከታቸዋለን። ከተስማሙ የተስማሙበትን ቁጥር በእያንዳንዱ ወገን አጠገብ ላይ እንጽፋለን። ከተለያዩ ደግሞ የወራሾቹን ቁጥር እንመዘግባለን። በመቀጠል በሁለቱ ምዘናዎች ላይ ተንተርሰን የመዘገብናቸውን አዲሶቹን ቁጥሮች በአራቱ የምልከታ ዘዴዎች ማለትም መመሳሰል፣ መስማማት፣ መለያየት እና አንዱ በአንዱ ውስጥ መገኘት (አት-ተዳኹል) በምባሉት መመዘኛዎች በማዬት የተገኘውን ውጤት በመደቡ እናባዛለን። ተባዝቶ የተገኘውንም ውጤት ዋና መደብ አድርገን ክፍፍሉን ከእርሱ እንሰረዋለን።

የምናነጻጽራቸው ቁጥሮች የምመሳሰሉ (አንድ ዓይነት) ከሆኑ ከሁለቱ አንዱን እንወስዳለን፤ የምለያዩ ከሆኑ ደግሞ አንዱን በአንዱ እናባዛለን፤ የምስማሙ ከሆነ የተስማሙበትን ቁጥር በሌላኛው ሙሉ እናባዛለን፤ አንዱ በአንዱ ውስጥ የምገኝ ከሆነ ደግሞ ትልቁን ቁጥር በመውሰድ ትንሹን እንተወዋለን።

# እንክሳር በሁለት ወገኖች ላይ ሲሆን እና በወራሾች መካከል መመሳሰል ሲኖር

ለምሣሌ ፡- ወራሾቹ ሁለት ምስቶችና ሁለት ወንድሞች (በእናትም በአባትም በኩል ወንድም የሆኑ) ቢሆኑ መደባቸው ከ 4 ይሆንና ለምስቶቹ 1/4 ስሰጣቸው የቀረው ሦስቱ ለሁለቱ ወንድሞች ይሰጣል ዐሰባ ስለሆኑ።

| 4 | | |
|---|---|---|
| ወራሾች | የወራሾች ብዛት | የውርስ ድርሻ |
| ምስት | 2 | 1 |
| ወንድም | 2 | 3 |

ነገር ግን ሁለቱንም ወገኖች (ሁለቱን ምስቶች እና ሁለቱን ወነድሞች) ስንመለከት የደረሳቸው ድርሻ እና ቁጥራቸው እኩል አይደለም፤ ምክኒያቱም፣ ምስቶቹ ቁጥራቸው ሁለት ሲሆን የደረሳቸው ድርሻ ግን አንድ ነው። እንደዚያውም ወንድሞቹ ቁጥራቸው ሁለት ሲሆን ድርሻቸው ዴግሞ ሦስት ነው። ስለዚህ የሁለቱንም ወገኖች ብዛት ከጎናቸው እንመዘግባለን። ከመዘገብን ቡኃላ የመዘገብናቸውን ቁጥሮች በአራቱ የምልከታ ዜዴዎች ስንመለከታቸው ተመሳሳይ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምስቶች ብዛታቸው 2 ሲሆን ወንድማማቾቹም 2 ናቸው። ሁለት ከሁለት ጋር ስለምመሳሰል አንዱን ብቻ በመውሰድ ከመደቡ ጋር እናባዛለን። 2 × 4 = 8 ስለሚሆን መደቡ ከስምንት ይሆንና ክፍፉ እንደሚከተለው ይሰራል።

ምስቶች 1/4 = 2 ይወስዱና አንዳንድ ይካፈላሉ።

የተረፈውን ሁለቱ ወንድሞች እኩል ሦስት ሦስት ይካፈላሉ።

| 8 | |
|---|---|
| ምስት | 1 |
| ምስት | 1 |
| ወንድም | 3 |
| ወንድም | 3 |

**ምሣሌ 2፡-** ወራሾቹ አራት ምስቶች እና አራት አኅቶች ቢሆኑ መደባቸው ከአራት ይሆናል። ምስቶቹ 1/4 = 1 ስወስዱ የተረፈውን ሦስቱን አኅቶቹ ዐሰባ ስለሆኑ ጨርሰው ይወርሳሉ።

| 4 | | |
|---|---|---|
| ወራሾች | የወራሾች ብዛት | የውርስ ድርሻ |
| ምስት | 4 | 1 |
| አኅት | 4 | 3 |

በመቀጠል ሁለቱንም ወገኖች የደረሳቸውን ድርሻ እና ቁጥራቸውን ስንመለከት ልዩነት እንዳለው እናያለን። ምስቶቹ አራት ሲሆኑ የደረሳቸው ድርሻ አንድ ነው። እንደዝያውም አኅቶቹ አራት ሲሆኑ የደረሳቸው ድርሻ ሦስት ነው። 1 እና 4 ይለያያሉ። 3 እና 4ም እንደዝያው ይለያያሉ። በመቀጠል የምስቶቹን ብዛት ለብቻ የአኅቶቹንም ለብቻ መዝግበን ስንመለከታቸው ተመሳሳይ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምክኒያቱም ምስቶቹም አራት አኅቶቹም አራት ናቸውና። ስለዚህ አንዱን ወስደን ከመጀመሪያው መደብ (4) ጋር እናባዛለን። 4 × 4 = 16 ስለሆነ መደባቸው 16 ይሆናል ማለት ነው። በዝህ ጊዜ ምስቶቹ 1/4 = 4 ስደርሳቸው የተረፈው 12ቱ የአኅቶች ይሆንና ሦስት ሦስት ይካፈላሉ።

| 16 | |
|---|---|
| ምስተ | 1 |
| ምስት | 1 |
| ምስት | 1 |
| ምስት | 1 |
| አኅት | 3 |
| አኅት | 3 |
| አኅት | 3 |
| አኅት | 3 |

# እንከሳር በሦስት ወገኖች ላይ ስገኝ እና ተዳኹል እና ተኻሉፍ የምባሉት አሰራሮች ሥራ ላይ ስውሉ

ለምሣሌ በአንድ ውርስ ላይ አራት ምስቶች፣ ሦስት ሴት ልጆች እና ሁለት እህቶች (በሁለቱም በኩል እህት የሆኑ) ቢገኙ መደባቸው ከ 24 ይሆናል። ለአራቱ ምስቶች 1/8 = 3 ይሰጣቸዋል፤ ሴት ልጆች 2/3 = 16 ይወርሳሉ፤ እህቶች ደግሞ ከሴት ልጆች ጋር ሲሆኑ ዐሰባ መዐል ገይር ስለሚሆኑ የተረፈውን 5ቱን ይወስዳሉ።

በመቀጠል ወራሾቹን እና የደረሳቸውን ድርሻ ስንመለከት ልዩነት እናገኛለን። ምክኒያቱም ምስቶች አራት ሲሆኑ የደረሳቸው ድርሻ 3 ነው። ልጆቹ ሦስት ሲሆኑ ድርሻቸው 16 ነው። እንደዝያውም እህቶች ሁለት ሲሆኑ ድርሻቸው ደግሞ 5 ነው። ስለዚህ የደረሳቸውን ድርሻ በመተው የወራሾቹን ቁጥር ብቻ ማለትም 4፣ 3 እና 2ን እንመለከታለን። በምንመለከትበት ጊዜ 2 በ4 ውስጥ የምገኝ ወይም 4 ለ 2 ያለቀሪ የምካፈል ሆኖ እናገኛለን። ስለዚህ ተዳኹል ስለሆነ 4ን በመውሰድ 2ን እንተዋለን። በመቀጠል 3 እና 4ን እናያለን። በምናይበት ጊዜ ተኻሉፍ (የማይስማሙ ወይም የተለያዩ) ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ እናባዛቸዋለን። ይኸውም 4 × 3 = 12 ስለሚሆን 12ን በመውሰድ ከመጀመሪያው መደብ (24) ጋር እናባዛለን። አባዝተን ያገኘነውን ቁጥር ዋና መደብ በማድረግ ክፍፍሉን ከእርሱ እንሰራለን። ይኸውም 24 × 12 = 288 ስለሆነ መደቡ 288 ይሆናል ማለት ነው።

አራቱ ምስቶች 1/8 = 36 ስደርሳቸው እያንዳንዳቸው ዘጠኝ ዘጠኝ ይደርሳቸዋል።

ሦስቱ ሴት ልጆች 2/3 = 192 ስደርሳቸው እያንዳንዳቸው 64 ፣ 64 ይደርሳቸዋል።

እህቶች የተረፈውን 60 ስወስዱ እያንዳንዳቸው 30 ፣ 30 ይደርሳቸዋል።

| መደብ = 288 | |
|---|---|
| ምስት | 9 |
| ምስት | 9 |
| ምስት | 9 |
| ምስት | 9 |

| | |
|---|---|
| ሴት ልጅ | 64 |
| ሴት ልጅ | 64 |
| ሴት ልጅ | 64 |
| እህት | 30 |
| እህት | 30 |

# እንከሳር በአራት ወገኖች ላይ ሲሆን እና መስማማት ስኖር

አራት ምስቶች፣ አንዷት እህት (በሁለቱም በኩል እህትየሆነች)፣ አስራ ሁለት እህቶች በአባት በኩል ብቻ እና አስር አጎቶች ቢሆኑ መደባቸው ከ 12 ይሆናል። ምስቶች 1/4 = 3 ይሰጣቸዋል፤ በሁለቱም በኩል እህት ለሆነችው ግማሹን 6 እንሰጣታለን፤ በአባት በኩል እህት ለሆኑት 1/6 (የሁለት ሶስተኛ ማሟያ) = 2 እንሰጣቸዋለን፤ የተረፈውን 1 ለአጎቶቹ እንሰጣቸዋል። በመቀጠል ወራሾቹን እና የደረሳቸውን ድርሻ እንደሚከተለው እናያለን።

ምስቶቹ 4 ሲሆኑ ድርሻቸው 3 ነው። ይለያያሉ። ስለዚህ 4ን ለብቻ እንመዘግባለን። እህት 1 ስትሆን ድርሻዋ 6 ነው። እንደዝሁም በአባት በኩል እህት የሆኑት ቁጥራቸው 12 ሲሆን ድርሻቸው 2 ነው። ስለዚህ በግማሽ ስለምስማሙ ሁለቱንም በ 1/2 እናባዛቸዋለን። ስናባዛቸው 6 ይመጣል። አሁንም 6ን ለብቻው እንመዘግባለን። አጎቶች 10 ሲሆኑ ድርሻቸው ግን አንድ ነው። ስለምለያዩ 10ንም ለብቻ እንመዘግባለን።

ከዝያም እነዚህን ለብቻ የመዘገብናቸውን ቁጥሮች (4፣ 6 እና 10)ን እንመለከታለን። ስንመለከታቸው በግማሽ የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ 4 እና 10ን እያንዳንዳቸውን በ 1/2 እናባዛቸዋለን። ስናባዛቸው 2 እና 5 ይመጣሉ። በመቀጠል 2 እና 5ን እናባዛለን። 2 × 5 = 10 ይመጣል። ከዝያም 10ን በ6 እናባዛለን። 10 × 6 = 60 ስለሆነ 60ን ከመጀመሪያው መደብ ከ 12 ጋር እናባዛለን። 60 × 12 =

720 ስለሚመጣ መደቡ ከ 700 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሰራል።

ለምስቶች 1/4 = 180 ስደርሳቸው እያንዳንዳቸውን 45፣ 45 ይደርሳቸዋል።

በሁለቱም በኩል እህት ለሆነችው (1/2) = 360 ይደርሳታል።

በአባት በኩል ብቻ እህት ለሆኑት 1/6 = 120 ስደርሳቸው እያንዳንዳቸው አስር አስር ይደርሳቸዋል።

ለአጎቶች የተረፈውን = 60 ስንሰጣቸው እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ይደርሳቸዋል።

| መደብ = 720 | | | |
|---|---|---|---|
| ወራሾች | የወራሾች ብዛት | የውርስ ድርሻ | በነፍስ ወከፍ የምደርሳቸው |
| ምስቶች | 4 | 180 | 45 |
| እህት | 1 | 360 | 360 |
| እህቶች | 12 | 120 | 10 |
| አጎቶች | 10 | 60 | 6 |

## መለያየት እና ምሳለው

5 ሴት ልጆች

3 ሴት አያቶች

4 አራት ምስቶች

7 አጎቶች ቢሆኑ መደባቸው ከ 24 ይሆናል። ሴቶቹ ልጆች 2/3 = 16 ይወስዳሉ፤ ሴት አያቶች 1/6 = 4 ይወርሳሉ፤ አራቱ ምስቶች 1/8 = 3 ስወርሱ አጎቶች ደግሞ ዐሰባ ስለሆኑ የተረፈውን 1 ይወርሳሉ። በመቀጠል የወራሾቹን ቀጥር እና ድርሻቸውን ስንመለከት የማይስማሙ ወይም የምለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ እንደገና የወራሾቹን ቀጥር ብቻ እንመለከታለን። በምንመለከትበት ጊዜ የማይስማሙ ወይም የምለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ አንዱን በአንዱ እናባዛለን። 5 × 3 × 4 ×

7 = 420 ስለሚሆን ይህንኑ ውጤት በድጋሚ ከመጀመሪያው መደብ ከ(24) ጋር እናባዛለን፡፡ 420 × 24 = 10080 ስለምመጣ መደቡ ከእርሱ (10080) ይሆንና ክፍፍሉ እንደሚከተለው ይሰራል፡፡

| የወራሾች ብዛ ት በቁጥር | መደብ = 10080 | | ለእያንዳንዳቸው በነፍስ ወከፍ የምደርሳቸው ድርሻ ድርሻ |
|---|---|---|---|
| | ወራሾች | የውርስ ድርሻቸው | |
| 5 | ሴት ልጆች | 2/3 = 6720 | 1344 |
| 3 | ሴት አያቶች | 1/6 = 1680 | 560 |
| 4 | ምስቶች | 1/8 = 1260 | 315 |
| 7 | አኅቶች | 420 | 60 |

## ሽረት (አልሙናሰኻ)

ነስኽ ወይም ሽረት ማለት አንድን ሽሪዓዊ ድንጋጌ በሌላ ሽሪዓዊ ድንጋጌ መተካት ማለት ነው፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ከሞተ ቡኃላ ውርሱ ለወራሾቹ ከመከፋፈሉ በፊት ከእርሱ ወራሾች መካከል አንድ ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ ነው፡፡ይህም በሶስት ይከፈላል፡፡

1ኛ፡ የሁለተኛው ሟች ወራሾች የመጀመሪያው ሟች ወራሾች ሲሆኑ እና አወራረሳቸውም ከመጀመሪያው ሟች አወራረስ ጋር አንድ ዓይነት ሲሆን

2ኛ፡ የሁለተኛው ሟች ወራሾች የመጀመሪያው ሟች ወራሾች ሲሆኑ እና ነገር ግን አወራረሳቸው የተለዩ ሲሆን ወይም ከእነርሱ ጋር ሌላ ተጨማሪ ወራሽ ስገኝ

3ኛ፡ የእያንዳንዱ ሟች ወራሾች ከእርሱ ሌላ ሌላውን ሟች መውረስ የማይችሉ ሲሆኑ

የሁለተኛው ሟች ወራሾች የመጀመሪያው ሟች ወራሾች ሲሆኑ እና አወራረሳቸውም ከመጀመሪያው ሟች አወራረስ ጋር አንድ ዓይነት ሲሆን

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው አስር ወንድ ልጆች ትቶ ይሞታል፤ ከዚያም ውርሱ ሳይከፋፈል ልጆቹ አንድ በአንድ እየሞቱ ሁለት ልጆች ብቻ ይቀራሉ። በዝህ ጊዜ መደባቸው በቁጥራቸው ልክ ከሁለት ይሆንና አንዳንድ ይካፈላሉ። የሟቹ ምስት (ማለትም የልጆቹ እናት) አብሯቸው ብትኖር እና እሷም ከሞቱት ልጆች ጋር ሞታ ቢሆንም እንኳ ውርሱ ያው እንደ መጀመሪያው ውርስ በቁጥራቸው ልክ ይሆናል። ምክኒያቱም ወራሾቹም ሆኑ አወራረሱ ምንም አልተለወጠምና።

የሁለተኛው ሟች ወራሾች የመጀመሪያው ሟች ወራሾች ሲሆኑ እና አወራረሳቸው የተለዬ ሲሆን ወይም ከእነርሱ ጋር ሌላ ተጨማሪ ወራሽ ስገኝ

በዝህ ጊዜ የመጀመሪያውን ውርስ በመስራት ለእያንዳንዱ ወራሽ ምን ያህል እንደምደርሰው እንረዳለን። በመቀጠል ሁለተኛውን ውርስ በመስራት ለወራሾቹ እናከፋፍላለን። ከዝያም የሁለተኛውን ሟች ድርሻ እና የሁለተኛውን መደብ እንመለከታለን። በምንመለከትበት ጊዜ ከሚከተሉት ሶስቱ አንዱን ሆኖ እናገኘዋለን። እነሱም፡-

1ኛ፡ የሟች ድርሻ ለሁለተኛው መደብ የምካፈል መሆን

2ኛ፡ መስማማት (ተዋፉቅ)

3ኛ፡ መለያዬት (ተባዩን) ናቸው።

የሟች ድርሻ ለሁለተኛው መደብ የምካፈል ከሆነ የመጀመሪያው መደብ በተሠራበት መንገድ ሁለተኛውም መደብ ይሰራል። ለምሳሌ የመጀመሪያው መደብ 24 ከሆነ ሁለተኛውም መደብ 24 ይሆናል ማለት ነው።

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ምስቱን፣ ሴት ልጁን እና ወንድሙን (በሁለቱም በኩል ወንድሙ የሆነውን) ትቶ ቢሞት እና ውርሱ ሳይከፋፈል ሴት ልጁ ባሏን እና ወንድ ልጇን ትታ ብትሞት የመጀመሪያው ውርስ መደቡ ከ8 ይሆናል። ምስት 1/8 = 1 ትወስዳለች፤ ሴቷ ልጅ ግማሽ = 4 ትወስዳለች፤ የተረፈውን 3ቱን ወንድም ይወርሳል።

ሁለተኛው መደብ ዴግሞ ከ 4 ይሆናል። ባል 1/4 = 1 ስወስድ የተረፈውን (3ቱን) ልጇ ይወስዳል። በመቀጠል ሟቿ ከመጀመሪያው ውርስ ያገኘችውን ድርሻ (4ን) እና ሁለተኛውን መደብ (4ን) ስንመለከት የልጅቷ ድርሻ (4) ለሁለተኛው መደብ (4) የምካፈል ሆኖ እናገኛለን። ስለዚህ የሸረት መደቡም 8 ይሆናል ማለት ነው።

| ወራሾች | የመጀመሪያው መደብ = 8 | | ሁለተኛው መደብ = 4 | የሽረት መደብ = 8 |
|---|---|---|---|---|
| ምስት | 1 | - | - | 1 |
| ሴት ልጅ | 4 | ሟች | - | - |
| ወንድም | 3 | - | - | 3 |
| | | ባል | 1 | 1 |
| | | ልጅ | 3 | 3 |

ለምሳሌ አንዲት ሴት ባሏን፣ እናቷን፣ አንድ ወንድ ልጇን እና አንዲት ሴት ልጇን ጥላ ብትሞት እና ውርሱ ሳይከፋፈል ባል ወንድ ልጁን እና ሴት ልጁን ትቶ ቢሞት ውርሱ እንደሚከተለው ይሆናል። የመጀመሪያው ውርስ መደቡ ከ 12 ይሆናል፡- ባል 1/4 = 3 ይሰጠዋል፤ እናት 1/6 = 2 ይሰጣታል፤ የተረፈውን ሰባቱን ወንዱ ልጅ እና ሴቷ ልጅ ዐሰባ በመሆን ጨርሰው ይወርሳሉ። አወራረሳቸው ወንዱ ሁለት እጅ ስወስድ ሴቷ አንድ እጅ ትወስዳለች። ነገር ግን ሰባትን ያለቀሪ ለሶስት ማካፈል ስለማይቻል ትክክለኛውን መደብ ለማግኘት የልጆቹን ቁጥር እና ድርሻቸውን እንመለከታለን። ስንመለከት የምለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምክኒያቱም ሰባት እና ሶስት ይለያዩሉና።

(የልጆቹ ቁጥር ሶስት የሆነበት ምክኒያት አንድ ወንደ በሁለት ሴቶች ስለሚቆጠር ነው።) ከዝያም ድርሻቸውን ትተን ቁጥራቸውን (ሶስትን) በመውሰድ ከመጀመሪያው መደብ (12) ጋር እናባዛለን። 3 × 12 = 36 ስለሚሆን መደቡ ከ36 ይሆንና ውርሱ እንደሚከተለው ይከፋፈላል።

ባል 1/4 = 9

እናት 1/6 = 6

ወንዱ ልጅ = 14

ሴቷ ልጅ = 7 ይወርሳሉ።

ሁለተኛው መደብ ዴግሞ ከሶስት ይሆንና ወንዱ ሁለት ስወስድ ሴቷ አንድ ትወስዳለች። በመቀጠል የባልን ድርሻ (ዘጠኝን) እና ሁለተኛውን መደብ ሶስትን ስንመለከት ዘጠኝ

ለሶስት የሚካፈል ሆኖ እናገኛለን። ስለዚህ መደቡ እንደመጀመሪያው ከ 36 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። መደቡም የሸረት መደብ ይባላል።

| | 3 | | | 3 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወራሾች | መደብ 12 | መደብ 36 | | መደብ 3 | መደብ 36 (የሸረት መደብ) |
| | ባል | 3 | 9 | ሟች | - | - |
| | እናት | 2 | 6 | - | - | 6 |
| ብዛት3 3{ | ወንድ ልጅ | 7 | 14 | ወንድ ልጅ | 2 | 20 |
| | ሴት ልጅ | | 7 | ሴቷ ልጅ | 1 | 10 |

ከላይ ያሉት ቁጥሮች ማባዣ ቁጥሮች ናቸው።

የሁለተኛው ሟች ድርሻ እና ሁለተኛው መደብ የምስማሙ ከሆነ የተስማሙበትን የጋራ ቁጥር በሁለተኛው መደብ በማባዛት የተገኘውን ውጤት እንደገና ከመጀመሪያው መደብ ጋር እናባዛለን። ከዝያም የተገኘው ውጤት የሸረት መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል።

**ለምሳሌ፡-** አንድ ሰው ምስቱን፣ አንዲት ሴት ልጁን እና እህቱን (በሁለቱም በኩል እህቱ የሆነችውን) ጥሎ ቢሞት እና ውርሱ ሳይከፋፈል ከወራሾቹ መካከል የሟች ሴት ልጅ እናቷን፣ ባሏን እና አንድ ወንድ ልጇን ትታ ብትሞት ውርሱ እንደሚከተለው ይሆናል። የመጀመሪያው መደብ ከ 8 ይሆንና ምስት 1/8 = 1 ትወስዳለች፤ ሴቷ ልጅ ግማሽ = 4 ስትወስድ የተረፈውን (3) ደግሞ እህት ትወስዳለች፤ ምክኒያቱም እህት ከሟች ሴት ልጅ ጋር ስትሆን ዐሰባ ትሆናለችና።

ሁለተኛው መደብ ደግሞ ከ 12 ይሆናል። እናት (በመጀመሪያው ውርስ ላይ ምስት የነበረችው) 1/6 = 2 ትወስዳለች፤ ባል 1/4 = 3 ይወስዳል። የተረፈውን (7) ልጇ ይወስዳል።

የሸረት መደቡን ለመስራት የሟችን ድርሻ (4)ን እና ሁለተኛውን መደብ (12)ን እንመለከታለን። በምንመለከትበት ጊዜ በ 1/4 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ ሁለቱንም በ 1/4 እናባዛቸዋለን። 1/4 × 4 = 1 እንደዚሁም 1/4 × 12 =

3 ስለሚሆን 3ን ወስደን ከመጀመሪያው መደብ ከ 8 ጋር እናባዛለን። 3 × 8 = 24 ስለሆነ የሸረት መደቡ 24 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሰራል። ድርሻቸውም በሸረት መደቡ ስር በወራሾቹ ትይዩ ይቀመጣል። አሰራሩን ከሠንጠረዡ ይመልከቱ።

| 3 | | | 1 | |
|---|---|---|---|---|
| ወራሾች | የመጀመሪያው መደብ = 8 | | ሁለተኛው መደብ = 12 | የሸረት መደብ = 24 |
| ምስት | 1 | እናት | 2 | 5 |
| ሴት ልጅ | 4 | ሟች | - | - |
| እህት | 3 | - | - | 9 |
| | | ባል | 3 | 3 |
| | | ልጅ | 7 | 7 |

ከሠንጠረዡ እናት ላይ የተጻፉት 3

3 እና 1 ማባዣ ቁጥሮች ናቸው።

5 = 3 × 1 + 2

9 = 3 × 3

2ኛ ምሳሌ ፡- አንዷት ሴት ባሏን፣ አንዷት ሴት ልጇን እና ወንድሟን ትታ ብትሞት እና ውርሱ ሳይከፋፈል ከወራሾች መካከል ሴቷ ልጅ ባሏን እና አንድ ወንድ ልጇን ትታ ብትሞት የመጀመሪያው ውርስ መደቡ ከ 4 ይሆናል። ባል 1/4 = 1 ይወስዳል፣ ሴቷ ልጅ ግማሽ = 2 ስትወስድ የተረፈውን 1 ወንድሟ ይወስዳል። ሁለተኛው መደብም ከ 4 ይሆናል። ባል 1/4 = 1 ስወስድ የተረፈውን ሶስቱን ደግሞ ወንዱ ልጅ ይወስዳል።

በመቀጠል የልጅቷን ድርሻ እና ሁለተኛውን መደብ ስንመለከት ተስማምተው እናገኛቸዋለን። ምክኒያቱም የልጅቷ ድርሻ 2 ሲሆን ሁለተኛው መደብ ደግሞ 4 ነውና። ስለዚህ 2 እና 4 በ ግማሽ ማለትም በ 1/2 ይስማማሉ። ስለዚህ ሁለተኛውን መደብ (4) ን በ 1/2 ስናባዛ 2 ይሆናል። ሁለትን ከመጀመሪያው መደብ ከ(4) ጋር ስናባዛ ስምንት ይመጣል። 1/2 × 4 = 2 በመቀጠል 2 × 4 = 8 ስለሚሆን የሸረት መደቡ 8 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። ድርሻቸው በስማቸው ትይዩ የሸረት መደቡ ስር ይቀመጣል።

| 2 | | | 1 | |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ወራሾች | የመጀመሪያው መደብ = 4 | | ሁለተኛው መደብ = 4 | የሽረት መደብ = 8 |
| ባል | 1 | | | 2 |
| ሴት ልጅ | 2 | ሟች | - | - |
| ወንድም | 1 | | - | 2 |
| | | ባል | 1 | 1 |
| | | ወንድ ልጅ | 3 | 3 |

የሟቹ ድርሻ እና ሁለተኛው መደብ የምለያዩ ወይም የማይስማሙ ከሆነ ሁለተኛውን መደብ ከአንደኛው ጋር በማባዛት የምናገኘውን ውጤት የሽረት መደብ እናደርጋለን። በመጀመሪያው መደብ ውስጥ ድርሻ ያለው ሰው በሁለተኛው መደብ ተባዝቶ ይሰጠዋል፤ በሁለተኛው መደብ ውስጥ ድርሻ ያለው ደግሞ ከሟች ድርሻ ጋር ተባዝቶ ይሰጠዋል። ድርሻቸው በስማቸው ትይዩ የሽረት መደቡ ስር ይቀመጣል።

ለምሣሌ፡- አንድ ሰው እናቱን፣ እህቱን (በአባት በኩል) እና አጎቱን ትቶ ብሞት እና ውርሱ ሳይከፋፈል ከወራሾቹ መካከል እህቱ ባሏን እና አንድ ወንድ ልጇን ጥላ ብትሞት የመጀመሪያው ውርስ ከስድስት ይሆናል። እናት 1/3 = 2 ትወስዳለች፤ እህት ግማሽ = 3 ስትወስድ የተረፈውን አንዱን አጎት ይወርሳል።

ሁለተኛው መደብ ደግሞ ከአራት ይሆናል። ባል 1/4 = 1 ስወስድ የተረፈውን ሶስቱን ልጁ ይወስዳል። በመቀጠል የሟችን ድርሻ እና ሁለተኛውን መደብ ስንመለከት የማይስማሙ (የምለያዩ) ሆነው እናገኛቸዋለን። ምክኒያቱም 3 እና 4 መስማማት አይችሉምና። ስለዝህ ሁለተኛውን መደብ (4ን) ከመጀመሪያው መደብ ከ (6) ጋር እናባዛለን። 6 × 4 = 24 ስለሚሆን የሽረት መደቡ 24 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሰራል።

| 4 | | | 3 | |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ወራሾች | የመጀመሪያው መደብ = 6 | | ሁለተኛው መደብ = 4 | የሽረት መደብ = 24 |
| እናት | 2 | | - | 8 |
| እህት | 3 | ሟች | - | - |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እኅት | 1 | - | - | 4 |
| | | ባል | 1 | 3 |
| | | ወንድ ልጅ | 3 | 9 |

ከላይ የተጻፉት ቁጥሮች 3 የሟች ድርሻ ሲሆን 4 ሁለተኛው መደብ ነው።

**ምሣሌ 2፡-** አንድ ሰው ምስቱን፣ 3 ወንድ ልጆቹን እና አንዲት ሴት ልጁን ጥሎ ብሞት እና ውርሱ ሳይከፋፈል ምስቱም እነዚህን ልጆች ጥላ ብትሞት የመጀመሪያው መደብ ከ 8 ይሆናል። ምስት 1/8 = 1 ትወስዳለች፤ ወንዶቹ ልጆች 6ቱን ይወስዱና እኩል ሁለት ሁለት ይካፈላሉ፤ ቀሪውን አንድ ደግሞ ሴቷ ልጅ ትወስዳለች። (ሴቷ የወንዱን ግማሽ ትወስዳለች ማለት ነው።)

ሁለተኛው መደብ ከ 7 ይሆናል። ለእያንዳንዱ ወንድ ልጅ ሁለት ሁለት ስደርሰው ሴቷ ልጅ የወንዱን ግማሽ አንድ ትወስዳለች። በመቀጠል የሟችን ድርሻ (1) እና ሁለተኛውን መደብ (7)ን ስንመለከት የምለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ስለዚህ የሸረት መደቡን ለማግኘት ሁለተኛውን መደብ እና የመጀመሪያውን መደብ እናባዛለን። 7 × 8 = 56 ስለሆነም የሸረት መደቡ 56 ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። በመጀመሪያው መደብ ውስጥ ድርሻ ያለው ሰው በሁለተኛው መደብ ተባዝቶ ይሰጠዋል፤ በሁለተኛው መደብ ውስጥ ድርሻ ያለው ደግሞ ከሟች ድርሻ ጋር ተባዝቶ ይሰጠዋል። ድርሻቸው በስማቸው ትይዩ የሸረት መደቡ ስር ይቀመጣል።

| | | | 1 | 7 |
|---|---|---|---|---|
| ወራሾች | የመጀመሪያው መደብ = 8 | | ሁለተኛው መደብ = 7 | የሸረት መደብ = 56 |
| ምስት | 1 | ሟች | - | - |
| ወንድ ልጅ | 2 | ወንድ ልጅ | 2 | 16 |
| ወንድ ልጅ | 2 | ወንድ ልጅ | 2 | 16 |
| ወንድ ልጅ | 2 | ወንድ ልጅ | 2 | 16 |
| ሴት ልጅ | 1 | ሴት ልጅ | 1 | 8 |

16 = (7 × 2) + (2 × 1)

8 = (7 × 1) + (1 × 1)

## የእያንዳንዱ ሟች ወራሾች እሱን እነጂ ሌላውን መውረስ የማይችሉ ሲሆኑ

በዝህ ጊዜ ቅድሚያ የመጀመሪያውን የውርስ በመስራት ለእያንዳንዱ ወራሽ ምን ያህል እንደምደርሰው ማወቅ ይኖርብናል። ከዝያም ለእያንዳነዱ ሟች የውርስ መደቡ ተሠርቶ ለወራሾች ይከፋፈላል። በመቀጠል የሟች ድርሻ እና ሁለተኛው መደብ መስማማታቸውን ወይንም መለያየታቸውን አልያም ለሁለተኛው መደብ ተካፋይ መሆኑን እና አለመሆኑን እናያለን።

የሟች ድርሻ ለመደቡ የምካፈል ከሆነ የመጀመሪያው ውርስ ከተሠራበት መደብ ሁለተኛውም ውርስ ይሰራል። ለምሳሌ የመጀመሪያው ውርስ መደቡ 12 ከሆነ ሁለተኛውም ውርስ መደቡ 12 ይሆናል። የሟች ድርሻ ለመደቡ የምይካፈል ከሆነ ግን የምስማማ ወይንም የማይስማማ ልሆን ስለምችል መዝግበን እናቆያቸዋለን። በመቀጠል መዝግበን ያቆየናቸውን ቁጥሮች ቀደም ብለን በገለጽናቸው አራቱ ምልከታዎች እናያቸዋለን።

ከምልከታው ቡኃላ ያገኘነውን ውጤት ማባዣ አድርገነው ከመጀመሪያው መደብ ጋር እናባዛዋለን፤ ተባዝቶ የተገኘው ውጤት የሸረት መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል። ከዚያም ከመጀመሪያው መደብ ድርሻ ያለው ሰው ከአራቱ ምልከታዎች ቡኃላ በተገኘው ማባዣ ቁጥር ተባዝቶ ይሰጠዋል። እንደዝያውም የእያንዳንዱ ሟች ድርሻ በማባዥያው ቁጥር ይባዛል። የተገኘውም ውጤት ለእርሱ ወራሾች ይከፋፈላል።

የዝህ ምሳሌ አንድ ሰው ሶስት ወንድ ልጆችን ጥሎ ይሞታል፤ ከዚያም ውርሱ ሳይከፋፈል ከልጆቹ መካከል አንዱ ሁለት ልጆቹን ትቶ ብሞት እና ሁለተኛው ልጅ ዴግሞ ሶስት ልጆችን ትቶ ቢሞት እና ሶስተኛው አራት ልጆችን ጥሎ ቢሞት (ሁሉም ወንዶች ቢሆኑ) የመጀመሪያው መደብ በቁጥራቸው ልክ ከ 3 ይሆንና እያንዳንዳቸው አንዳንድ ይወስዳሉ።

በመቀጠል የልጆቹን ስንመለከት የመጀመሪያው ልጅ ሁለት ልጆችን ትቶ ስለሞተ መደባቸው ከሁለት ይሆናል፤ ሁለተኛው ልጅ ሶስት ልጆችን ትቶ ስለሞተ መደባቸው ከሶስት ይሆናል፤ ሶስተኛው ልጅ ዴግሞ አራት ልጆችን ጥሎ ስለሞተ መደባቸው ከአራት ይሆናል። የውርስ መደባቸው በወራሾቹ ቁጥር ልክ ስለሆነ ሁለተኛው መደብ እና ድርሻቸው የተለያዩ (የማይስማሙ) ይሆናሉ ። ስለዚህ ሶስቱንም

መደቦች መደብ ሁለት፣ መደብ ሶስት እና መደብ አራትን በአራቱ የምልከታ ዜዴዎች እንመለከታቸዋለን።

በምንመለከትበት ጊዜ የመጀመሪያው መደብ በሶስተኛው መደብ ውስጥ የምገኝ (ተዳኹል) ሆኖ እናገኘዋለን። ምክኒያቱም የመጀመሪያው መደብ 2 ሲሆን ሶስተኛው መደብ ዴግሞ 4 ነውና። ሁለት በአራት ውስጥ ስለሚገኝ አራትን በመውሰድ ከሁለተኛው መደብ (ከ3) ጋር እናባዛለን፤ ምክኒያቱም 3 እና 4 ይለያያሉና። ስናባዛቸው 4 × 3 = 12 ስለሚሆን 12 ማባዣ ቁጥር ይሆንና ከመጀመሪያው መደብ (ልጆቹ አባታቸውን የወረሱበት መደብ (3) ጋር) ይባዛል። 12 × 3 = 36 ስለዚህ ለሶስቱ ልጆች ለእያንዳንዳቸው 12 ይደርሳቸዋል።

የመጀመሪያው ሟች 12 ስደርሰው ለልጆቹ ለእያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ይደርሳቸዋል።

ሁለተኛው ሟች 12 ስደርሰው ለልጆቹ ለእያንዳንዳቸው 4 ይደርሳቸዋል።

ሶስተኛው ሟች 12 ስደርሰው ለልጆቹ ለእያንዳንዳቸው 3 ይደርሳቸዋል።

## የውርስ ክፍፍል

በዝህ ዘርፍ የውርስ ክፍፍል ዋናው እና ተፈላጊው ነጥብ ነው። የውርስ ህግጋቶችን ማወቅ የተፈለገበትም ምክኒያት ለዝሁ ዓላማ ነው። ስለዚህ ተገቢውን ድርሻ ለባለ ድርሻው ለማድረስ የውርስ ክፍፍሉ እንዴት እንደሆነ ማወቅ ግድ ይላል። የምወረሱ ንብረቶች (ሐብቶች) ሁለት ዓይነት ናቸው። እነሱም :- ለክፍፍል የምመቹ እና የማይመቹ ናቸው።

ለክፍፍል ምቹ የምባሉት ለምሣሌ:- ጥሬ ገንዘብ ፣ ልመዘን የምችል፣ የምሰፈር ወይም የምቆጠር፣ ወዘተ ኛቸው።

ለክፍፍል የማያመቹ ዴግሞ ከእነዚህ ውጭ ያሉ ነገሮች ናቸው። ሆኖም ግን ሁለቱም አሰራሮች ይመሳሰላሉ።ንብረቶችን ለማከፋፈል የተለያዩ አሰራሮች ብኖሩም እዝህ ጋር ሁለቱን አሰራሮች ብቻ እንመለከታለን። እነሱም:- የምወረሰው ነገር ጥሬ ገንዘብ (ካሽ) ሲሆን እና ንብረት ሲሆን ናቸው።

## ውርሱ ጥሬ ገንዘብ ሲሆን

በዚህ ጊዜ ወራሾቹን በማየት የውርሱን መደብ እንወስናለን። ከዚያም የብሩን መጠን ከጎን እናስቀምጣለን። በመቀጠል ብሩ እና የውርስ መደባቸው መመሳሰላቸውን፣

መስማማታቸዉን እና መለያየታቸውን /አለመስማማታቸውን/ እናያለን። የምመሳሰሉ ከሆነ ጉዳዩ ገር ይሆናል። ምክኒያቱም የወራሾቹን ድርሻ ቀጥታ ብሩ ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። ከብሩ የምደርሳቸው ድርሻም እርሱ ይሆናል።

**ለምሣሌ፡-** አንድ ሰው 24 ግራም ወርቅ ትቶ ቢሞት እና ወራሾቹ ምስቱ፣ እናቱ እና አንድ ወንድ ልጁ ቢሆኑ መደባቸው ከ 24 ይሆናል። እናት 1/6 = 4 ትወስዳለች፤ ምስት 1/8 = 3 ትወስዳለች፤ የተረፈውን 17 ዴግሞ ልጁ ይወስዳል። በመቀጠል የውርስ መደባቸውን እና የወርቁን መጠን ስናስተያይ የምመሳሰሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ የወራሾቹን ድርሻ በቀጥታ ወርቁ ስር ባለው ባዶ ቦታ እናስቀምጣለን።

| ወራሾች | 24 | 24 ግራም ወርቅ |
|---|---|---|
| ምስት | 3 | 3 |
| እናት | 4 | 4 |
| ወንድ ልጅ | 17 | 17 |

**የሚስማሙ ከሆነ** መደቡ እና የብሩ መጠን የተስማሙበትን የጋራ ቁጥር ከብሩ እና ከመደቡ ጋር እናባዛለን። ከብሩ ጋር አባዝተን ያገኘነውን ውጤት ከወራሾች የድርሻ መጠን ጋር ማባዣ ቁጥር አድርገነው የመደቡ አናት ላይ እናስቀምጠዋለን። ከመደቡ ጋር አባዝተን ያገኘነውን ውጤት ዴግሞ ከብሩ ጎን ባለው ሳጥን ውስጥ እንመዘግባለን።

በመቀጠል መደቡ አናት ላይ ያስቀመጥነውን ማባዣ ቁጥር በቅደም ተከተል አንድ በአንድ ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን። የተገኘውን ዉጤት ከብሩ ጎን ባለው ሳጥን ውስጥ ላለው ቁጥር እናካፍላለን። የተገኘዉ ውጤት ቀሪ ከሌለው ከብሩ ስር ባላው ባዶ ቦታ እንመዘግበዋለን፤ ቀሪ ካለው ዴግሞ ቀሪውን ብቻ ነጥለን ከብሩ ጎን ካለው ቁጥር ስር እንመዘግበዋለን። ቀሪው ከብሩ ጎን ከተመዘገበው ቁጥር አካል ነው።

ሥራችን ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ መጀመሪያ ያለቀሪ የተመዘገቡትን ቁጥሮች አንድ ላይ እንሰበስባቸዋለን፤ በመቀጠል ቀሪ የሆኑትን እንሰበስባለን፤ ከዚያም ሁለቱንም (ቀሪ የሆኑትን እና ያልሆኑትን) አንድ ለይ እንደምራቸዋለን፤ ስንደምራቸዉ ከብሩ መጠን ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። ካል ሆነ ግን እንደገና አስተካክለን መስራት ይኖርብናል።

ለምሣሌ፡- አንዲት ሴት ባሏን፣ አንድ ወንድ ልጇን እና 4,000 ብር ትታ ብትሞት የውርስ መደባቸው ከ4 ይሆናል። ባል 1 ስሰጠው ልጁ 3 ይሰጠዋል። በመቀጠል የውርስ መደባቸውን እና የብሩን መጠን ስናስተያይ በ1/4 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ የተስማሙበትን ቁጥር (1/4)ን ከመደቡ እና ከብሩ ጋር እናባዛለን። ከመደቡ ጋር አባዝተን ያገኘነውን ውጤት ከብሩ ጎን ባለው ባዶ ሳጥን ውስጥ እነመዘግበዋለን። ከብሩ ጋር በማባዛት ያገኘነውን ውጤት ዴግሞ ከመደቡ አናት ላይ በማስቀመጥ መደቡ ሥር ባሉት የወራሾች ድርሻ እናባዛለን። ተባዝቶ የተገኘውን ውጤት ብሩ ጎን ላለው ቁጥር እናካፍላለን። አካፍለን ያገኘነውን ውጤት ቀሪ የሌለውን ከብሩ ስር ባሉ ባዶ ቦታዎች በወራሾቹ ትይዩ እነመዘግባለን። ቀሪውን ዴግሞ ብሩ ጎን ባለው ቁጥር ስር እንመዘግባለን። መጨረሻ ላይ ስንደምራቸው ከብሩ ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑ ይረጋገጣል።

ለምሣሌ፡- አንዲት ሴት

1000 መመ ማባ

| ወራሾች | መደብ = 4 | 4000 | 1 = (1/4 × 4) |
|---|---|---|---|
| ባል | 1 | 1000 | - |
| ልጅ | 3 | 3000 | - |

ከላይ የተጻፈው 1000 = (መደቡ ስር ካሉት ቁጥሮች ጋር ማባዣ ቁጥር ሲሆን 1/4 ከ 4000 ጋር ስባዛ የተገኘ ውጤት ነው።)

ምሣሌ 2፡- ወራሾቹ ባል፣ እናት እና ወንድም ቢሆኑና ያለው ብር ዴግሞ 6000 ቢሆን መደባቸው ከ6 ይሆናል። ባል ግማሽ = 3 ይወስዳል፤ እናት 1/3 = 2 ትወስዳለች፤ ወንድም የተረፈውን 1 ይወስዳል። (ወንድም ስንል በሁለቱም በኩል ወንድም የሆነ ወይም በአባት በኩል ብቻ ወንድም የሆነውን ለማለት ነው።)

በመቀጠል መደቡን እና ብሩን ስንመለከት በ1/6 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ ሁለቱንም በ1/6 እናባዛቸዋለን። 1/6 × 6 = 1 እና 1/6 × 6000 = 1000 ስለሚሆን 1ን ከብሩ ጎን ባለው ባዶ ሳጥን ውስጥ እናስቀምጣለን። 1000ውን ዴግሞ ከመደቡ አናት ላይ አድርገን መደቡ ስር ካሉት ቁጥሮች ጋር እናባዛለን። የተገኘውንም ውጤት ብሩ ጎን ላለው ቁጥር እናካፍላለን። ከተገኘው ውጤት ያለቀሪ የተካፈለውን ከብሩ ስር ባሉት ባዶ ሳጥኖች ውስጥ ከወራሾቹ ትይዩ እንመዘግባለን። ቀሪውን ዴግሞ ብሩ ጎን ላይ ከተጻፈው ቁጥር ስር እንመዘግባለን።

መጨረሻ ላይ ብሩ ስር ያሉትን ቁጥሮች እና ከብሩ ጎን ባለው ቁጥር ስር የተመዘገቡትን ቁጥሮች አንድ ላይ ስንደምራቸው ከብሩ ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። ካልሆኑ እንደገና እንሰራለን።

1000

| ወራሾች | 6 | 6000 | 1 |
|---|---|---|---|
| ባል | 3 | 3000 | - |
| እናት | 2 | 2000 | - |
| ወንድም | 1 | 1000 | - |

የውርስ መደቡ እና የብሩ መጠን የምለያዩ (የማይስማሙ) ከሆነ መጀመሪያ መደቡን እና ብሩን ጎን ለጎን እንመዘግባቸዋለን። ቀጥለን መደቡ ስር የወራሾቹን ድርሻ እናስቀምጣለን። በመቀጠል በሶስተኛው ሳጥን ውስጥ ከብሩ ጎን መደቡን እንመዘግባለን። ከዝያም የብሩን መጠን የመደቡ አናት ላይ በማስቀመጥ መደቡ ስር ባሉት የወራሾች ድርሻ እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ለመደቡ እናካፍላለን። አካፍለን ካገኘነው ቁጥር ያለቀሪ የተካፈለውን በብሩ ስር እንመዘግባለን። ቀሪውን ዴግሞ በብሩ ጎን ባለው መደብ ስር እንመዘግባለን። መጨረሻ ላይ ብሩ ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች እና በጎን ባለው ቁጥር ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች ተደምረው ብሩ ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። ካልሆነ ግን እንደገና እንሰራለን።

ለምሣሌ፡- አንድ ሰው ምስቱን፣ እናቱን እና አባቱን እንደዝሁም 235 ግራም ወርቅ ትቶ ብሞት አወራረሳቸው እንደሚከተለው ይሆናል፡- የውርስ መደባቸው ከ 12 ይሆናል። ምስት 1/4 = 3 ትወስዳለች፤ እናት 1/3 = 4 ትወስዳለች፤ አባት የተረፈውን = 5 ይወስዳል።

በመቀጠል የውርስ መደቡን እና የወርቁን መጠን ስናስተያይ የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምክኒያቱም 12 እና 235 አይስማሙምና። ስለዚህ ወርቁን የመደቡ አናት ላይ በማስቀመጥ መደቡ ስር ባሉት የወራሾች ድርሻ እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ለመደቡ እናካፍላለን። ይኸውም፡ 235 × 3/12 = 705/12 = 58. 75 ስለሚሆን 58ን በወርቁ ስር እንመዘግባለን፤ 0.75ን ዴግሞ ብሩ ጎን ባለው መደብ ስር እንመዘግባለን። 235 × 4/12 = 940/12 = 78.3 ስለሚሆን 78ን ከወርቁ ስር እንመዘግባለን። 0.3ን ዴግሞ መደቡ ስር እንመዘግባለን። እንደዝያውም 235 ×

5/12 = 1175/12 = 97.91 ስለሚሆን 97ን ከወርቁ ስር እንመዘግባለን። 0.91ን ደግሞ መደቡ ስር እንመዘግባለን። አቀማመጡ ከሰንጠረዡ ይመልከቱ።

| 235 | | | |
|---|---|---|---|
| ወራሾች | 12 | 235 | 12 |
| ምስት | 3 | 58 | 0.75 |
| እናት | 4 | 78 | 0.33 |
| አባት | 5 | 97 | 0.916 |

## ውርሱ ንብረት ሲሆን

የምወረሰው ነገር ንብረት ሲሆን አወራረሱ በቂራጥ ይሆናል። ቂራጥ ማለት የውርሱን ንብረት 24 ቦታ መክፈል ሲሆን እያንዳነዱ ክፍልፋይ ቂራጥ ይባላል። አሰራሩም ከብሩ አሰራር ጋር ምንም ልዩነት የለውም፤ ያለው ልዩነት በብሩ ቦታ 24ን መተካት ብቻ ነው። እሱም ቂራጥ ይባላል። ይህንን ቂራጥ የውርስ መደቡ አጠገብ እንመዘግባለን። ከዚያም የውርስ መደቡን እና 24ን እንመለከታለን። የምመሳሰሉ ከሆነ ጉዳዩ ገር ነው። የእያንዳንዱን ወራሽ ድርሻ ፊት ለፊቱ ላይ ከቂራጡ ስር እናስቀምጣለን። እሱም ድርሻቸው ይሆናል።

ለምሣሌ፡- አንድ ሰው ምስቱን፣ እናቱን እና አንድ ወንድ ልጁን ትቶ ቢሞት መደባቸው ከ 24 ይሆናል። እናት 1/6 = 4 ትወስዳለች፤ ምስት 1/8 = 3 ትወስዳለች፤ የተረፈውን 17 ደግሞ ልጁ ይወስዳል። በመቀጠል የውርስ መደባቸውን እና ቂራጡን (24ን) ስናስተያይ የምመሳሰሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ የወራሾቹን ድርሻ በቀጥታ 24 ስር ባለው ባዶ ቦታ በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን።

| ወራሾች | 24 | 24 ግራም ወርቅ |
|---|---|---|
| ምስት | 3 | 3 |
| እናት | 4 | 4 |
| ወንድ ልጅ | 17 | 17 |

የመስማማት ምሳሌ፡- ወራሾቹ ባል፣ እናት እና አንድ ወንድ ልጅ ቢሆኑ መደባቸው ከ 12 ይሆናል።

ባል 1/4 = 3

እናት 1/6 = 2

ልጁ የተረፈውን = 7 ይወስዳል።

በመቀጠል መደቡን እና 24ን ስንመለከት በ 1/12 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ ሁለቱንም በ 1/12 እናባዛቸዋለን። 1/12 × 12 = 1 እና 1/12 × 24 = 2 ስለሚሆን 1ን ከቂራጡ (24) ጎን ባለው ሳጥን ውስጥ እናስቀምጣለን። 2ን ደግሞ ከመደቡ አናት ላይ አድርገን ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ቂራጡ ጎን ላለው ቁጥር (ለ 1) እናካፍላለን። አካፍለን ያገኘነው ቁጥር ቀሪ ከለሌው ከቂራጡ ስር ባለው ክፍት ቦታ በወራሾቹ ትይዩ እንመዘግበዋለን። ቀሪ ካለው ደግሞ ከ 1 ስር እንመዘግባለን።

በመጨረሻም ሥራችን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ በ24 ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች እና በ 1 ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች ተደምረው ከ 24 ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። እኩል ካልሆኑ እንደገና መስራት አለብን። አሰራሩን ከዚህ በታች ይመልከቱ።

| | 2 | | |
|---|---|---|---|
| ወራሾች | መደብ = 12 | ቂራጥ = 24 | 1 = (12 × 1/12) |
| ባል | 3 | 6 | - |
| እናት | 2 | 4 | - |
| ወንድ ልጅ | 7 | 14 | - |

ለምሳሌ፡- አንዲት ሴት ባሏን፣ እናቷን፣ አንድ ወንድ ልጇን እና አንዲት ሴት ልጇን ጥላ ብትሞት ውርሱ እንደሚከተለው ይሆናል። የውርስ መደባቸው ከ 12 ይሆናል፡- ባል 1/4 = 3 ይሰጠዋል፤ እናት 1/6 = 2 ይሰጣታል፤ የተረፈውን ሰባቱን ወንዱ ልጅ እና ሴቷ ልጅ ዐሰባ በመሆን ጨርሰው ይወርሳሉ። አወራረሳቸው ወንዱ ሁለት እጅ ስወስድ ሴቷ አንድ እጅ ትወስዳለች። ነገር ግን ሰባትን ያለቀሪ ለሶስት ማካፈል ስለማይቻል ትክክለኛውን መደብ ለማግኘት የልጆቹን ቁጥር እና ድርሻቸውን እንመለከታለን። ስንመለከት የምለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምክኒያቱም ሰባት እና ሶስት ይለያዩሉና።

(የልጆቹ ቁጥር ሶስት የሆነበት ምክኒያት አንድ ወንደ በሁለት ሴቶች ስለሚቆጠር

ነው።) ከዝያም ድርሻቸውን ትተን ቁጥራቸውን (ሶስትን) በመውሰድ ከመጀመሪያው መደብ (12) ጋር እናባዛለን። 3 × 12 = 36 ስለሚሆን መደቡ ከ36 ይሆንና ውርሱ እንደሚከተለው ይከፋፈላል።

ባል 1/4 = 9

እናት 1/6 = 6

ወንዱ ልጅ = 14

ሴቷ ልጅ = 7 ይወርሳሉ።

በመቀጠል ሁለተኛውን መደብ (36ን) እና 24ን ስናስተያይ በ 1/12 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ ሁለቱንም በ 1/12 እናባዛቸዋለን። 1/12 × 36 = 3 እና 1/12 × 24 = 2 ስለሚሆን 3ን ከቂራጡ (24) ጎን ባለው ሳጥን ውስጥ እናስቀምጣለን። 2ን ደግሞ ከመደቡ አናት ላይ አድርገን ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ቂራጡ ጎን ላለው ቁጥር (ለ3) እናካፍላለን። አካፍለን ያገኘነው ቁጥር ቀሪ ከለሌው ከቂራጡ ስር ባለው ክፍት ቦታ በወራሾቹ ትይዩ እንመዘግበዋለን። ቀሪ ካለው ደግሞ ከ3 ስር እንመዘግባለን።

በመጨረሻም ሥራችን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ በ24 ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች እና በ3 ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች ተደምረው ከ24 ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። እኩል ካልሆኑ እንደገና መስራት አለብን። አሰራሩን ከዚህ በታች ይመልከቱ።

(የልጆች ቁጥር)

↓

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | **3** | **2** | | |
| | ወራሾች | መደብ 12 | መደብ 36 | (ቂራጥ) 24 | 3 = (36 × 1/12) |
| | ባል | 3 | 9 | 6 | - |
| | እናት | 2 | 6 | 4 | - |
| 3{1 | ወንድ ልጅ | 7 | 14 | 9 | 1 |
| | ሴት ልጅ | | 7 | 4 | 2 |

ምሳሌ 2 ፡- ወራሾቹ ምስት፣ እናት እና ወንድም ቢሆኑ መደባቸው ከ 12 ይሆናል። ምስት 1/4 = 3 ትወስዳለች፤ እናት 1/3 = 4 ትወስዳለች፤ ወንድም ደግሞ የተረፈውን = 5 ይወስዳል። በመቀጠል 12ን እና 24ን ስናስተያይ በ 1/12 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ ሁለቱንም በ 1/12 እናባዛቸዋለን። 1/12 × 12 = 1 እና 1/12 × 24 = 2 ስለሚሆን 1ን ከቂራጡ ጎን ባለው ሳጥን ውስጥ እናስቀምጣለን። 2ን ዴግሞ ከመደቡ አናት ላይ አድርገን ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ቂራጡ ጎን ላለው ቁጥር (ለ1) እናካፍላለን። አካፍለን ያገኘነው ቁጥር ቀሪ ከለሌው ከቂራጡ ስር ባለው ክፍት ቦታ በወራሾቹ ትይዩ እንመዘግበዋለን። ቀሪ ካለው ዴግሞ ከ1 ስር እንመዘግባለን።

በመጨረሻም ሥራችን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ በ24 ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች እና በ1 ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች ተደምረው ከ24 ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። እኩል ካልሆኑ እንደገና መስራት አለብን። አሰራሩን ከዚህ በታች ይመልከቱ።

| | | 2 | |
|---|---|---|---|
| ወራሾች | 12 | 24 | 1 |
| ምስት | 3 | 6 | - |
| እናት | 4 | 8 | - |
| ወንድም | 5 | 10 | - |

የውርስ መደቡ እና ቂራጡ የምለያዩ (የማይስማሙ) ከሆነ መጀመሪያ መደቡን እና ቂራጡን ጎን ለጎን እንመዘግባቸዋለን። ቀጥለን መደቡ ስር የወራሾቹን ድርሻ እናስቀምጣለን። በመቀጠል በሶስተኛው ሳጥን ውስጥ ከቂራጡ ጎን መደቡን እንመዘግባለን። ከዚያም ቂራጡን የመደቡ አናት ላይ በማስቀመጥ መደቡ ስር ባሉት የወራሾች ድርሻ እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ለመደቡ እናካፍላለን። አካፍለን ካገኘነው ቁጥር ያለቀሪ የተካፈለውን ከቂራጡ ስር በወራሾቹ ትይዩ እንመዘግባለን። ቀሪውን ዴግሞ ከቂራጡ ጎን ባለው መደብ ስር እንመዘግባለን። መጨረሻ ላይ ቂራጡ ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች እና በጎን ባለው ቁጥር ስር የመዘገብናቸው ቁጥሮች ተደምረው ቂራጡ ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን። ካልሆነ ግን እንደገና እንሰራለን።

ለምሣሌ፡- አንድ ሰው ምስቱን፣ እናቱን እና በአባት በኩል የሆኑ ሁለት እህቶቹን ትቶ ብሞት አወራረሳቸው እንደሚከተለው ይሆናል፡- የውርስ መደባቸው ከ 12 ይሆናል። ምስት 1/4 = 3 ትወስዳለች፤ እናት 1/6 = 2 ትወስዳለች፤ ሁለቱ እህቶች 2/3 = 8 ይወስዳሉ። ስለዚህ ከ 12 የነበረው መደባቸው ወደ 13 ከፍ ይደረጋል።

በመቀጠል 13ን እና 24ን ስንመለከት የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ 24ን የመደቡ አናት ላይ በማስቀመጥ መደቡ ስር ባሉት የወራሾች ድርሻ እናባዛለን። ያገኘነውን ውጤት ለመደቡ እናካፍላለን። ይኸውም፡ 24 × 3/13 = 72/13 = 5.53 ስለሚሆን 5ን በ24 ስር እንመዘግባለን፤ 0.53ን ደግሞ 24 ጎን ባለው መደብ (13) ስር እንመዘግባለን። 24 × 2/13 = 48/13 = 3.69 ስለሚሆን 3ን ከ24 ስር እንመዘግባለን። 0.69ን ደግሞ 13 ስር እንመዘግባለን። እንደዝያውም 24 × 8/13 = 192/13 = 14.76 ስለሚሆን 14ን ከ24 ስር እንመዘግባለን። 0.76ን ደግሞ 13 ስር እንመዘግባለን። አቀማመጡ ከሰንጠረዡ ይመልከቱ።

| 24 | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወራሾች | 12 | 13 | 24 | 13 |
| ምስት | 3 | 3 | 5 | 0. 53 |
| እናት | 2 | 2 | 3 | 0.69 |
| እህት | 4 | 4 | 7 | 0.38 |
| እህት | 4 | 4 | 7 | 0.38 |

## የኹንሳ /የወንዳገረድ/ አወራረስ

ወንዳገረድ ማለት ስወለድ ወንድ ይሁን ሴት መሆኑ ያልታወቀ ሰው ማለት ነው። ወይም የወንድ እና የሴት ብልት ያለው ለማለት ነው። የዝህ ዓይነት ሰው ጉዳዩ ግልጽ እስከሆን ድረስ እንድቆይ ደደረጋል። ወንዳገረድ ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው ካደገ በኃላ ግልጽ ልሆን የምችል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ካደገ በኃላም ግልጽ ልሆን የማይችል ነው።

እንደ ወንድ ታይቶ ከሆነ የወንድ ግማሽ ይሰጠዋል። እንደ ሴት ታይቶ ከሆነ ደግሞ የሴት ግማሽ ይሰጠዋል። ነገር ግን ህፃን ሆኖ እስክያድግ ድረስ ጉዳዩ ግልጽ መሆን ካልቻለ ውርሱ በሁለቱም መንገድ (እንደ ወንድ እና እንደ ሴት) ተሠርቶ ለወራሾቹ

እርግጠኛው ድርሻቸው ብቻ ይሰጣቸዋል። ቀሪው ደግሞ የወንዳገረዱ ጉዳይ እስከጣራ እንደቆይ ይደረጋል።

ወንዳገረዱ አንድ ብቻ ከሆነ የውርስ መደቡ ሁለት ጊዜ ይሰራል፤ ሁለት ከሆነ አራት ጊዜ ይሰራል፤ ሶስት ከሆነ ስድስት ጊዜ ይሰራል፤ አራት ከሆነ ስምንት ጊዜ ይሰራል።

ግልጽ ሳይሆን በህፃንነቱ ከሞቴ ወይም ካደገ ቡኃላም ግልጽ ሳይሆን ከቀረ በውርስ ጊዜ የወንዱን ግማሽ እና የሴቷን ግማሽ እንደምወርስ አንዳንድ ምሁራን ይናገራሉ።

ጉዳዩ ግልጽ መሆኑን ማወቂያ መንገዶች ብዙ ናቸው። ከእነዚህ መካከል፡

- ሽንቱን ከሁለቱ ብልቶች በየትኛው እንደሚሸና በማየት
- የወር አበባ ይኑረው አይኑረው በማየት
- ጡቶቹን በማየት
- የፂም አበቃቀሉን በማየት ... ወዘተ ናቸው።

ሽንቱን በሁለቱም ብልቶች የምሸና ከሆነ በየትኛው ቀድሞ እንደምሸና እናያለን። እኩል የምጀምሩ ከሆነ በብዛት ሽንቱ የምወጣበትን መንገድ እናስቀድማለን። ሌሎችንም እንደዝሁ በንጽጽር በማየት እንወስናለን። ለጊዜው ግልጽ ሳይሆን ቀርቶ ወራሾቹ ውርሱን መከፋፈል ከፈለጉ እርግጠኛው ድርሻቸው ብቻ ይሰጣቸውና ቀሪው የወንዳገረዱ ጉዳይ እስከጣራ እንድቆይ ይደረጋል። የውርስ አሰራሩም በሁለት መንገድ ይሰራል።

መጀመሪያ ወንድ እንደሆነ ታስቦ ይሰራል፤ በመቀጠል ሴት እንደሆነ ታስቦ ይሰራል፤ ከዝያም ሁለቱንም የውርስ መደቦች (እንደ ወንድ ታስቦ የተሰራበትን እና እንደ ሴት ታስቦ የተሰራበትን መደብ) በአራቱ የምልከታ ዜዴዎች እንመለከታለን፤ የተገኘውን ውጤት ትክክለኛው የውርስ መደብ አድርገን በመውሰድ በሁለቱ አሰራሮች የተገኙትን ውጤቶች ከእርሱ ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። ቀሪውን ደግሞ የወንዳገረዱ ጉዳይ እስከጣራ እናቆየዋለን። ቡኃላም ተጣርቶ ወንድ መሆኑ ከታወቀ ለወንዳገረዱ ይሰጠዋል። ሴት ከሆነ ደግሞ ለወንዱ ልጅ ይሰጣል። ግልጽ ሳይሆን ከቀረ ግን በመካከላቸው በስምምነት ይከፋፈላሉ።

ለምሳሌ፡- ወራሾቹ አንድ ኹንሳ እና አንድ ወንድ ልጅ ቢሆኑ የውርስ መደባቸው መጀመሪያ እንደ ወንድ ታይቶ ከሁለት ይሰራል። ከዝያም አንዳንድ ይካፈላሉ። በመቀጠል እንደ ሴት ታይቶ ከሶስት ይሰራል። ከሶስት የሆነበት ምክኒያት አንድ

ወንድ በሁለት ሴት ስለምቆጠር ነው። ከዝያም ወንዱ ልጅ ሁለት ስወስድ ኹንሳው አንድ ይወስዳል።

በመቀጠል ሁለቱንም መደቦች በአራቱ የምልከታ ዜዴዎች ስንመለከት የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ አንዱን በአንዱ እናባዛለን። ይኸውም 2 × 3 = 6 ስለሚሆን መደቡ ከ 6 ይሆንና በመደብ 2 እና በመደብ 3 ያገኙትን ውጤት ደምረን መደብ 6 ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። የተረፈውን 1 ዴግሞ የኹንሳው ጉዳይ ግልጽ እስከሆን እናቆያለን።

| ወራሾች | 2 | 3 | 6 |
|---|---|---|---|
| ኹንሳ | 1 | 1 | 2 |
| ወንድ ልጅ | 1 | 2 | 3 |

ቡኃላም ተጣርቶ ወንድ መሆኑ ከታወቀ ለወንዳገረዱ ይሰጠዋል። ሴት ከሆነ ዴግሞ ለወንዱ ልጅ ይሰጣል። ግልጽ ሳይሆን ከቀረ ግን በመካከላቸው በስምምነት ይከፋፈላሉ።

ጉዳዩ ግልጽ ካልሆነ እና ወንድ ወይም ሴት መሆኑን መለየት ካስቸገረ እና ወደፊትም መለየት እንደማይቻል ከታመነበት የውርስ መደቡ እንደመጀመሪያው (እንደ ወንድ እና እንደ ሴት ታይቶ) ከሁለት ይሰራል። ከዝያም ሁለቱንም የውርስ መደቦች (እንደ ወንድ ታስቦ የተሰራበትን እና እንደ ሴት ታስቦ የተሰራበትን መደብ) በአራቱ የምልከታ ዜዴዎች እንመለከታለን፤ በምልከታው የተገኘውን ውጤት በሁለት እናባዛለን፤ በሁለት የምናባዛበት ምክኒያት በሁለት መንገዶች ስለሠራን ነው። የተገኘውን ውጤት ትክክለኛው የውርስ መደብ አድርገን በመውሰድ ለመጀመሪያዎቹ መደቦች እናካፍላለን። የተገኘውን ውጤት ከመጀመሪያዎቹ መደቦች አናት ላይ በማስቀመጥ ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን። ከዝያም ለሁለት እናካፍላለን። አካፍለን ያገኘነው ውጤት የወራሾቹ ድርሻ ስለሆነ በትልቁ መደብ ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። ከዝያም ስንደምራቸው ከትልቁ መደብ ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል ይሆናል። ካልሆነ ግን እንደገና እንሠራለን።

**ለምሣሌ፡-** ወራሾቹ ወራሾቹ አንድ ኹንሳ እና አንድ ወንድ ልጅ ቢሆኑ የውርስ መደባቸው መጀመሪያ እንደ ወንድ ታይቶ ከሁለት ይሰራል። ከዝያም አንዳንድ ይካፈላሉ። በመቀጠል እንደ ሴት ታይቶ ከሶስት ይሰራል። ከሶስት የሆነበት ምክኒያት

አንድ ወንድ በሁለት ሴት ስለምቆጠር ነው። ከዝያም ወንዱ ልጅ ሁለት ስወስድ ኹንሳው አንድ ይወስዳል።

በመቀጠል ሁለቱንም መደቦች በአራቱ የምልከታ ዜዴዎች ስንመለከት የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ አንዱን በአንዱ እናባዛለን። ይኸውም 2 × 3 = 6 ስለሚሆን ስድስትን በሁለት እናባዛለን፤ በሁለት የምናባዛበት ምክኒያት በሁለት መንገዶች ስለሠራን ነው። ይኸውም 2 × 6 = 12 ስለሆነ ትክክለኛው የውርስ መደብ 12 ይሆናል። በመቀጠል 12ን ለሁለቱ መደቦች (ለመደብ 2 እና ለመደብ 3) እናካፍላለን፤ ይኸውም 12/2 = 6 እና 12/3 = 4 ስለሚሆን 6ን እና 4ን የመጀመሪያዎቹ መደቦች አናት ላይ በማስቀመጥ ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን፤ ከዝያም ለሁለት እናካፍላለን፤ አካፍለን ያገኘነው ውጤት የወራሾቹ ድርሻ ስለሆነ በትልቁ መደብ (12) ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። ከዝያም ስንደምራቸው ከ12 ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል ይሆናል። ካልሆነ ግን እንደገና እንሠራለን።

| | 6 | 4 | |
|---|---|---|---|
| ወራሾች | 2 | 3 | 12 |
| ኹንሳ | 1 | 1 | 5 |
| ወንድ ልጅ | 1 | 2 | 7 |

5 = 10/2

7 = 14/2

ምሣሌ 2፡- ወራሾቹ ወራሾቹ አንድ ኹንሳ እና ሁለት ወንድ ልጆች ቢሆኑ የውርስ መደባቸው መጀመሪያ እንደ ወንድ ታይቶ ከ3 ይሰራል። ከዝያም አንዳንድ ይካፈላሉ። በመቀጠል እንደ ሴት ታይቶ ከ5 ይሰራል። ወንዶቹ ሁለት ሁለት ስወስዱ ኹንሳው አንድ ይወስዳል። በመቀጠል ሁለቱን መደቦች ስንመለከት የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ ስለዚህ እናባዛቸዋለን። 3 × 5 = 15 ስለሚሆን 15ን በሁለት እናባዛለን፤ 15 × 2 = 30 ስለሚሆን ዋናው መደብ 30 ይሆናል፤

በመቀጠል 30ን ለ5 እና ለ 3 እናካፍላለን፤ 30/3 = 10 እና 30/5 = 6 ስለሚሆን 10ን እና 6ን የመጀመሪያዎቹ መደቦች አናት ላይ በማስቀመጥ ከወራሾች ድርሻ ጋር እናባዛለን፤ ከዝያም ለሁለት እናካፍላለን፤ አካፍለን ያገኘነው ውጤት የወራሾቹ ድርሻ ስለሆነ በትልቁ መደብ (30) ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። ከዝያም

ስንደምራቸው ከ30 ጋር እኩል ከሆኑ ሥራችን ትክክል ይሆናል። ካልሆነ ግን እንደገና እንሠራለን።

| | 10 | 6 | |
|---|---|---|---|
| ወራሾች | 3 | 5 | 30 |
| ኹንሳ | 1 | 1 | 8 |
| ወንድ ልጅ | 1 | 2 | 11 |
| ወንድ ልጅ | 1 | 2 | 11 |

8 = 16/2

11 = 22/2

## ጽንስ

ሆድ ውስጥ ያለ ጽንስ ሁለት ቅድሜ ሆኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር አይወርስም አይወረስም። እነሱም፡-

01 ኛ፡ ሟች ስሞት ጽንሱ ሆድ ውስጥ መኖሩ መረጋገጥ

02 ኛ፡ ስወለድ ሙሉ በሙሉ ህይወት ያለው መሆኑ መረጋገጥ

ስወለድ ህይወት እንዳለው ማረጋገጥ የምቻለው ካለቀሰ ወይም ካስነጠሰ ወይም ከጠባ ወዘተ ነው። ጽንስን በተመለከተ አብረውት የምወርሱ ወራሾች ጽንሱ እስከወለድ ይጠብቃሉ። መጠበቅ ካልፈለጉ የወንዳገረዱን አወራረስ እንዳየነው የእነርሱም ይሰራል። ስለዚህ የጽንሱ ምንነት እስከታወቅ ድረስ ልደርሳቸው ከምችሉ ድርሻዎች ውስጥ አነስተኛው ድርሻ ይሰጣቸዋል። ቀሪው ዴግሞ የጽንሱ ምንነት እስከታወቅ እንድቆይ ይደረጋል።

**ለምሳሌ፡-** አንድ ሰው እርጉዝ ምስቱን ትቶ ቢሞት ከባሏ ንብረት መውረስ የምትችለው 1/8ውን ብቻ ነው። ይህም የምሆነው ጽንሱ ህያው ሆኖ ከተወለደ ነው። ስወለድ ህይወት ከለሌው ግን 1/4 ትወርሳለች። ስለዚህ እስከትወልድ መጠበቅ ይኖርባታል፤ መጠበቅ ካልፈለገች ግን 1/8 ብቻ ይሰጣትና ቀሪው ልጁ እስከወለድ ይጠበቃል፤ ስወለድ ህይወት ያለው ከሆነ ምንም አይሰጣትም፤ የለሌው ከሆነ ግን ቀሪው 1/8 ይጨመርላታል።

እዝህ ጋር መታወቅ ያለበት ጉዳይ ሆድ ውስጥ ያለ ጽንስ ስወለድ ከ6 ነገሮች በአንዱ ይጠበቃል። እነሱም፡-

01 ህይወት የለሌው ልሆን እንደምችል

02 አንድ ሴት ልጅ

03 አንድ ወንድ ልጅ

04 አንድ ወንድ ልጅ እና አንድ ሴት ልጅ

05 ሁለት ሴት ልጆች

06 ሁለት ወንድ ልጆች ሲሆኑ ከሁለት በላይ እጅግ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር አይከሰትም።

ወራሾቹ እርጉዟ እስክትወልድ መጠበቅ አለባቸው። መጠበቅ ካልፈለጉ ውርሱ በስድስቱም በኩል ተሠርቶ ከ6ቱ አሰራሮች አነስተኛው ድርሻ ታይቶ ይሰጣቸዋል። ቀሪው ጽንሱ እስከወለድ ይጠበቃል። አሰራሩ ከወንዳገረዱ አሰራር ጋር አንድ ዓይነት ነው።

## የጠፋ ሰው

የጠፋ ሰው ማለት የት እንደ ደረሰ የማይታወቅ፣ ስለ እርሱ ምንም ዓይነት ፍንጭ ያልተገኘ እንድሁም በህይወት ይኑር አይኑር የማይታወቅ ነው። ይህም በሁለት ይከፈላል።

1ኛ፡ በአብዛኛው በህይወት እንዳለ የምገመት ለምሳሌ፡- ለሥራ ወይም እውቀት ፍለጋ የወጣ ሰው፣ ወዘተ

2ኛ፡ በአብዛኛው ልሞት ይችላል ተብሎ የምገመት ለምሳሌ፡- ለጦርነት ዘምቶ ሳይመለስ ብቀር፣ በባህር ላይ በመርከብ እየተጓዙ የተወሰኑት ሰጥመው፣ የተወሰኑት ጠፍተው፣ የተወሰኑት በህይወት ብተርፉ እና እርሱ ከጠፉት መካከል ቢሆን ወዘተ

**ለምሳሌ** ፡- አንድ ሰው ሁለት ወንዶች ልጆች ትቶ ቢሞት እና ከሁለቱ ልጆች አንዱ የጠፋ ቢሆን ውርሱ የጠፋው ልጅ እስከገኝ ወይም መሞቱ እስከረጋገጥ እንድቆይ ይደረጋል። በአካል ያለው ልጅ መጠበቅ ካልፈለገ ግማሽ ይሰጠዋል። ግማሹ ደግሞ የጠፋው ልጅ በህይወት መኖሩ እና አለመኖሩ እስከረጋገጥ እንድቆይ ይደረጋል። በህይወት መኖሩ ከታወቀ ይቀመጥለታል። ካልኖረ ግን በህይወት ያለው ልጅ አጠቃሎ ይወስዳል።

**ምሳሌ 2**፡- አንድ ሰው ምስቱን፣ እናቱን እና ሁለት ወንድሞቹን ትቶ ቢሞት እና

ከወንድሞቹ መካከል አንዱ የጠፋ ቢሆን ውርሱ በሁለት መንገድ ይሰራል። አንደኛው በህይወት እንዳለ ታይቶ ይሰራል። ሁለተኛው ደግሞ እንደሞተ ተወስዶ ይሰራል።

በህይወት እንዳለ ተደርጎ ስሰራ መደቡ ከ12 ይሆናል። ምስት 1/4 = 3 ይሰጣታል፤ እናት 1/6 = 2 ይሰጣታል፤ቀሪውን (7) ሁለቱ ወንድሞች ይወስዳሉ።

በመቀጠል ወንድሞቹን ስንመለከት ድርሻቸው 7 ሲሆን እነርሱ 2 ናቸው። ሰባትን ለሁለት ማካፈል ስለማይቻል ሁለትን ከመደቡ ጋር እናባዛለን። 2 × 12 = 24 ስለሚሆን መደባቸው ከ24 ይሆናል። ምስት 1/4 = 6 ይደርሳታል፤ እናት 1/6 = 4 ይደርሳታል፤ የተረፈውን ሁለቱ ወንድሞች ሰባት ሰባት ይካፈላሉ።

በህይወት እንደሌሌ ተደርጎ ስሰራ ዴግሞ መደቡ ከ 12 ይሆንና ምስት 1/4 = 3 ትወስዳለች፤ እናት 1/3 = 4 ትወስዳለች፤ የተረፈውን 5ቱን ወንድም ይወስዳል። በመቀጠል የመጀመሪያውን መደብ (24ን) እና ሁለተኛውን መደብ (12ን) ስንመለከት በ1/12 የምስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ ሁለቱንም በ1/12 እናባዛቸዋለን። ይኸውም 1/12 × 12 = 1 ሲሆን 1/12 × 24 = 2 ይሆናል። ስለዚህ 2ን ከሁለተኛው መደብ (12) አናት ላይ እናስቀምጣለን፤ 1ን ዴግሞ ከመጀመሪያው መደብ (24) አናት ላይ እናስቀምጣለን። 2ን ከሁለተኛው መደብ ጋር ስናባዛ 24 ይመጣል። 2 × 12 = 24 ስለሚሆን 24 ማስተካከያ መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሆናል።

በመቀጠል ከመጀመሪያው መደብ አናት ላይ ያስቀመጥናትን 1ን እርሱ ስር ባሉት የወራሾቹ ድርሻ እያባዛን ከማስተካከያው መደብ (24) ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን።

| | 1 | 2 | | |
|---|---|---|---|---|
| ወራሾች | 12 | 24 | 12 | 24 |
| ምስት | 3 | 6 | 3 | 6 |
| እናት | 2 | 4 | 4 | 4 |
| ወንድም | 7 | 7 | 5 | 7 |
| ወንድም | | 7 | | |

በማስተካከያው መደብ ስር ያስቀመጥናቸው የወራሾች ድርሻ ስንደምራቸው 17 ይሆናሉ። ቀሪው ሰባቱ የጠፋው ልጅ ድርሻ ነው። በህይወት መኖሩ ከተረጋገጠ

እስከመጣ ድረስ ይቀመጥለታል፤ እንደ ሞተ ከታመነ ግን ለእናት ድርሻዋን 1/3 ሞልተንላት ቀሪውን በህይወት ላለው ወንድም እንሰጠዋለን።

በውሃ የተበሉ፣ ጋራ ተንዶባቸው ወይም ቤት ፈርሶባቸው የሞቱ፣ በቃጠሎ፣ በመኪና አደጋ ፣ በወረርሽኝ ወዘተ የሞቱ

በተጠቀሱት አደጋዎች ህይወታቸው ያለፈ ሰዎችን አስመልክቶ በአምስት እንከፍላቸዋለን።

01 ኛ፡ አንዱ ከአንዱ ቀድሞ የሞተ ከሆነ ለሴኮንዶችም እንኳ ቢሆን፡ በዝህ ጊዜ ዘግይቶ የሞተው ቀድሞ የሞተውን ይወርሳል። በዝህ ላይ ምሁራን ተስማምተዋል።

02 ኛ፡ በአንድ ጊዜ የሞቱ ከሆነ፡ በዝህ ጊዜ መወራረስ አይችሉም። በዝህ ላይም ምሁራን ተስማምተዋል።

03 ኛ፡ የትኛው ቀድሞ እንደሞተ ሳይታወቅ ስቀር፡

04 ኛ፡ አንዱ ከአንዱ ቀድሞ መሞቱ ታውቆ ነገር ግን የትኛው እንደቀደመ ሳይታወቅ ስቀር

05 ኛ፡ ቀድሞ የሞተው ከታወቀ ቡኃላ ከተረሳ

ከተራ ቁጥር 3-5 ያሉት አይወራረሱም። እያንዳንዳቸውን ዘመዶቻቸው ይወርሷቸዋል።

**ለምሳሌ፡-** ሁለት ወንድማማቾች ከላይ በጠቅስናቸው አደጋዎች በአንዱ ቢሞቱ እና አሟሟታቸውም አንድ ጊዜ ቢሆንና ቀድሞ የሞተው ባይታወቅ አንደኛው ሟች፡ - ምስቱን፣ አንድ ሴት ልጁን እና አጎቱን ትቶ ቢሞት እና ሌላኛው ዴግሞ ሁለት ሴት ልጆቹን እና የጠቀስነውን አጎቱን ትቶ ቢሞት እያንዳንዱ ዘመድ ሟች ዘመዱን ብቻ ይወርሳል። የአንዱ ወራሽ ሌላኛውን ሟች አይወርስም።

የመጀመሪያው ሟች ወራሾች መደባቸው ከ8 ይሆናል። ምስት 1/8 = 1 ትወስዳለች፤ ሴቷ ልጅ ግማሽ = 4 ትወስዳለች፤ የተረፈውን 3 ዴግሞ አጎት ይወስዳል።

የሁለተኛው ሟች ወራሾች ዴግሞ መደባቸው ከ3 ይሆናል። ሁለቱ እህቶች 2/3 = 2 ስወስዱ አጎት 1 ይወስዳል። ይህ ሟቾቹ በማይወራረሱ ጊዜ ነው። ሟቾቹ የምወራረሱ ከሆነ ዴግሞ አሰራሩ ከዝህ ይለያል።

## የዝምድና ባለቤቶች እና አወራረሳቸው

ዘመድ በማለት ለመግለጽ የተፈለገው ዘመድ ሆነው የውርስ ድርሻቸው በቁርኣን ያልተገለጸ ለማለት ነው። እነርሱም 11 ዓይነት ሲሆኑ ሁላቸውም ከዙፈርድ እና ከዐሰባ ውጭ ያሉ ዘመዶች ናቸው።

01 የሴት ልጅ ልጆች (ወንድ ይሁኑ ሴት)፣ የወንድ ልጅ ሴት ልጅ ልጆች እንደዝያውም የልጅ ልጆቻቸው

02 የእህት ልጆች (ወንድ ይሁኑ ሴት)

03 የወንድም ሴት ልጆች (ወንድምነታቸው በእናት በኩል ብቻ ያልሆነ) የወንድ ልጆቻቸው ሴት ልጆችም እንደዝያው

04 የወንድም ልጆች (ወንድምነታቸው በእናት በኩል ብቻ የሆነ)

05 የእናት አጎት (የሟች ወይም የአባቱ ወይም የአያቱ አጎት ቢሆንም እንኳ)

06 የአባት እህት (የሟች ወይም የአባቱ ወይም የአያቱ እህት ቢትሆንም እንኳ)

07 የአጎት ሴት ልጆች (ማንኛቸውም ቢሆኑ) የወንድ ልጆቻቸው ሴት ልጆችም እንደዝያው

08 የእናት ወንድሞች እና የእናት እህቶች (ማንኛቸውም ቢሆኑ)

09 ይወርሳሉ ተብለው ያልተጠቀሱ ወንድ አያቶች (በአባትም ይሁን በእናት በኩል) ለምሳሌ፡ የእናት አባት፣ የእናት አባት አባት

10 ይወርሳሉ ተብለው ያልተጠቀሱ ሴት አያቶች (በአባትም ይሁን በእናት በኩል) ለምሳሌ፡ የእናት አባት እናት፣ የወንድ አያት እናት

11 ከዝህ በላይ በጠቀስናቸው ዘመዶች በአንዳቸው በኩል ለሟች ዝምድና ያለው ሰው ለምሳሌ፡ የሴት አክስት አክስት (በእናትም ይሁን በአባት በኩል)፣ የእናት አባት አባት፣ የአጎት ወንድም (በእናት በኩል)፣ የእርሱ አጎት ወይም አክስት፣ ወዘተ ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ ከውርስ ምያገኙት ድርሻ ዝምድናቸው የተገኘበት ሰው የምያገኘውን ድርሻ ነው። ለምሳሌ ዝምድናቸው በአባት በኩል ከተገኘ አባት የምያገኘውን ድርሻ ያገኛሉ።

የውርስ መንገዳቸውም በ3 በኩል ነው። እነርሱም፡- በአባት በኩል፣ በእናት በኩል እና በልጅ በኩል ናቸው።

## በአባት በኩል ያሉት፡- ይወርሳሉ ተብለው ያልተጠቀሱ ወንድ አያቶች

እና ሴት አያቶች በአባት በኩል የሆኑ ለምሳሌ፡ የእናት አባት አባት፣ የአባት እናት አባት እናት፣ የወንድ አያት አባት እናት፣ አጎትነቱ በእናት ኩል የሆነ የአባት አጎት፣ የአባት እናት ወንድሞች፣ የአባት አክስቶች፣ የወንድም እና የእህት ሴት ልጆች እና ልጆቻቸው፣ የእህት ልጆች፣ የአጎት ሴት ልጆች እና የወንድ ልጆቻቸው ሴት ልጆች ናቸው።

በእናት በኩል ያሉት፡- ይወርሳሉ ተብለው ያልተጠቀሱ ወንድ አያቶች እና ሴት አያቶች በእናት በኩል የሆኑ ለምሳሌ፡ የእናት አባት፣ የእናት አባት እናት፣ የእናት እናት አባት፣ የእናት እናት አባት አናት፣ የእናት አጎቶች እና አክስቶች፣ የእናቷ ወይም የአባቷ ወንድ አጎቶች እና ሴት አጎቶች፣ የእናቷ ወንድሞች እና እህቶች (በአባት ይሁኑ በእናት)፣ እንደዝያውም የአባቷ እናት ወይም የእናቷ እናት ወንድሞች እና እህች ናቸው።

**በልጅ በኩል ያሉት፡-** የሴት ልጅ ልጆች፣ እና የልጅ ልጆቻቸው፣ … ናቸው።

የዝምድና ባለቤቶች ይወርሳሉ አይወርሱም በምለው ላይ በምሁራን መካከል የአቋም ልዩነት አለ። ከፍሎቹ አይወርሱም ስሉ ከፍሎቹ ይወርሳሉ ብለዋል። መውረስ አይችሉም ከምሉት መካከል ከፊል ሶሓቦች (ረ.ዐ)፣ ታቢዒዮች፣ እማሙ ማሊክ፣ እማሙ ሻፊዒይ፣ … (አላህ ይዘንላቸው) ይገኙበታል።

ከምያቀርቧቸው ምክኒያቶች መካከል አላህ (ሱ.ወ) በመጽሐፉ (በቁርአን) ውስጥ እንድወርሱ አልጠቀሳቸውም፤ አላህ (ሱ.ወ) ውርስን አስመልክቶ ወራሾች እነማን እንደሆኑና ድርሻቸው ምን ያህል እንደሆነ የወሰነው ራሱ ነው፤ እነዝህን ዴግሞ ከዐሰባም ሆነ ከዙፈርድ ውስጥ አላካተታቸውም ስለዚህ መውረስ አይችሉም ይላሉ።

ይወርሳሉ ከምሉት መካከል አቡ ሐኒፋ፣ እና እማሙ አሕመድ ይገኙበታል። እንደመረጃ ከምያቀርቧቸው መካከል ትርሚዚ እና አቡዳውድ የዘገቡት ሐዲስ ሲሆን ሐዲሱም ደካማ እንደሆነ ይነገራል። ሐዲሱ እንዲህ ይላል፡- “የእናት ወንድም ወራሽ የሌለው ሰው ወራሽ ነው። «الخال وارث من لا وارث له»ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ብለዋል የምል ሲሆን ይበልጥ ተቀባይነት ያለው ግን ይወርሳሉ የምለው ነው። የዝምድና ባለቤቶች ዘመድ ናቸው፤ ዝምድናን መቀጠል ዴግሞ ግዴታ ነው፤ ከሟች ጋር የምያስተሳስራቸው የስጋ ዝምድና እና እስላም ነው። በይተልማልን (እስላማዊ ግምጃ ቤትን) ከወሰድን ለሟች የምቀርበው በእስላም በኩል ብቻ ነው። ስለዚህ ከበይተልማል ይልቅ እነርሱ መውሰድ አለባቸው የምለው ነው።

## አወራረሳቸው

- የምያገኙት የውርስ ድርሻ ሟቹን እና ወራሹን ያስተሳሰራቸው ዘመድ ምያገኘውን ድርሻ ነው። ለምሣሌ፡ ዝምድናቸው በአባት በኩል ቢሆን አባት የምያገኘውን ድርሻ ያገኛሉ፤ በልጅ በኩል ከሆነ ልጅ የምያገኘውን ያገኛሉ፤ በእናት በኩል ከሆነም እናት የምታገኘውን ድርሻ ያገኛሉ።
- ወንድ እና ሴት እኩል ይወርሳሉ።
- ዝምድናቸው በተመሳሳይ በኩል ሆኖ ደረጃቸው ብለያይ ማለትም አንዱ ልጅ ሆኖ አንዱ ወንድም ቢሆን ድርሻቸው እንደደረጃቸው ይሆናል።
- ከእነርሱ መካከል ብቻውን የሆነ ሰው ሁሉንም ሐብት አጠቃሎ ይወርሳል።
- ተሰባስበው ስገኙ እንደ መደበኛ ወራሾች በደረጃ ከፍ የምለው ዐሰባ በደረጃ ዝቅ የምለውን ዐሰባ ይጋርዳል፤ በእናት እና በአባት በኩል ወንድም የሆነው በአባት በኩል ብቻ ወንድም የሆነውን ይጋርዳል።
- ዙፈርድ ወይም ዐሰባ ካለ የዝምድና ባለቤቶች አይወርሱም፤ ከዙፈርድ የተረፈ ነገር ካለ ለዙፈርዶች ይጨመርላቸዋል።
- በደረጃ እና በዝምድና እኩል ከሆኑ በአወራረስም እኩል ይሆናሉ፤ አንዱ ከአንዱ አይበልጥም፤ ሴቷ የወንዱን ግማሽ ትወርሳለች።
- ዝምድናው በወራሽ በኩል የሆነ ሰው ይወርሳል፤ ዝምድናው በወራሽ በኩል ያልሆነ ግን ያጣል። ለምሳሌ፡ አንድ ሰው የወንድ ልጁን ሴት ልጅ ሴት ልጅ እና የሴት ልጁን ወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ትቶ ቢሞት የዝምድና ደረጃቸው እኩል ቢሆንም መውረስ የምትችለው የወንዱ ልጅ ሴት ልጅ ሴት ልጅ ነች፤ ምክኒያቱም፣ ዝምድናዋ በወራሽ በኩል ነውና። የሴት ልጅ ወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ዴግሞ ዝምድናው ወራሽ ባልሆነ ሰው መንገድ ስለሆነ አይወርስም፤ ምክኒያቱም፣ የሴት ልጅ ወንድ ልጅ አይወርስምና።

## ለምሳሌ፡- ወራሾቹ የሚከተሉት ቢሆኑ፡-

- የእህት ሴት ልጅ (በአባትም በእናትም በኩል እህት የሆነች)
- የእህት ሴት ልጅ (በአባት በኩል ብቻ እህት የሆነች)
- የእህት ሴት ልጅ (በእናት በኩል ብቻ እህት የሆነች)
- የአጎት ሴት ልጅ (በሁለቱም በኩል አጎት የሆነ) ቢሆኑ 1/6 የምወርስ ሰው

ስላሌ መደባቸው ከ6 ይሆናል። በሁለቱም በኩል የእህት ልጅ ለሆነቸው ግማሽ (3) ይሰጣታል የእናቷ ድርሻ ስለሆነ፤ በአባት በኩል ብቻ እህት ለሆነችው 1/6 (2/3 ማሟያ) ይሰጣታል የእናቷ ድርሻ ስለሆነ፤ በእናት በኩል ብቻ እህት ለሆነችውም 1/6 ይሰጣታል የእናቷ ድርሻ ስለሆነ፤ የተረፈውን ደግሞ የአጎት ልጅ ትወርሳለች የአባቱ ድርሻ ስለሆነ።

| ወራሾች | 6 |
|---|---|
| የእህት ሴት ልጅ (በሁለቱም በኩል እህት የሆነች) | 3 |
| የእህት ሴት ልጅ (በአባት በኩል ብቻ እህት የሆነች) | 1 |
| የእህት ሴት ልጅ (በእናት በኩል ብቻ እህት የሆነች | 1 |
| የአጎት ሴት ልጅ (በሁለቱም በኩል አጎት የሆነ) | 1 |

ወራሾቹ የእናት እህት እና የአባት እህት ቢሆኑ መደባቸው ከ3 ይሆናል። የእናት እህት 1/3 = 1 ይሰጣታል፤ ምክኒያቱም ዝምድናዋ ለሟች በእናት በኩል ስለሆነ የእናት ድርሻ ይሰጣታል።

የአባት እህት ደግሞ የተረፈው 2ቱ ይሰጣታል፤ ምክኒያቱም ዝምድናዋ ለሟች በአባት በኩል ስለሆነ የአባት ድርሻ ይሰጣታል። ስለዚህ በወንድሟ ቦታ ትሆንና ዐሰባ ሆና ትወርሳለች።

| ወራሾች | 3 |
|---|---|
| የእናት እህት | 1 |
| አባት እህት | 2 |

ወራሾቹ:- የሴት ልጅ የልጅ ልጅ፣ የወንድም ሴት ልጅ (በእናት በኩል ያልሆነች) እና የእናት ወንድም bi ቢሆኑ መደባቸው ከ6 ይሆናል። የሴት ልጅ የልጅ ልጅ የእናቷን ድርሻ ግማሽ (3) ትወስዳለች፤ የእናት ወንድም 1 ይወስዳል የእህቱን ድርሻ፤ የወንድም ሴት ልጅ ደግሞ የአባቷን ቦታ ተክታ ቀሪውን 2 ዐሰባ ሆና ሆና ትወርሳስለች።

| ወራሾች | መደብ 6 |
|---|---|
| የሴት ልጅ የልጅ ልጅ | 3 |
| የወንድም ሴት ልጅ (በእናት በኩል ያልሆነች) | 1 |
| እና የእናት ወንድም | 2 |

ረድ ማለት የወራሾቹን ዕጣ (መደብ) ቀንሶ ድርሻቸውን መጨመር ነው። የዐውል ተቃራኒ ነው። ይህ የምሆነው ዐሰባ ሳይኖር ስቀር ነው። በዝህ ጊዜ ከዙፈርዶች የተረፈው ሐብት ተመልሶ ለዙፈርዶች ይጨመራል። ባል እና ምስት ስቀሩ። ባል እና ምስት ረድ ውስጥ አይካተቱም። ረድ የምደረግለት ሰው አንድ ሰው ብቻ ቢሆንም እንኳ ቀሪውን ሐብት አጠቃሎ ይወርሳል።

ለምሳሌ፡ ወራሿ አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ብትሆን መጀመሪያ ዙፈርድ ሆና በቁርኣን የተወሰነላትን ድርሻ ትወርሳለች፤በመቀጠል ዐሰባ (የተረፈውን አጠቃሎ መውረስ የምችል ሰው) ባለመኖሩ ረድ በምባለው አሰራር መሠረት ከእርሷ ድርሻ የተረፈውን ንብረት መልሳ ትወርሳለች።

ከአንድ በላይ ሆነው የውርስ ድርሻቸው እኩል የሆኑ ሰዎች ከሆኑ ለምሣሌ የእናት ልጆች ወይም የሟች ሴት ልጆች ውም የሟች ልጅ ሴት ልጆች የመሳሰሉት ቢሆኑ በመደበኛው ውርስም ሆነ ከውርስ ቡኃላ ረድ (ተመላሽ) በምደረግ ንብረትም የውርስ መደባቸው በቁጥራቸው ልክ ይሆናል። ከክፍፍሉ ቡኃላ የደረሳቸው የውርስ ድርሻ እና ቁጥራቸው ብለያይ ከመደብ ስድስት የደረሳቸው ድርሻ አንድ ላይ ተሰብስቦ ይደመራል። ተደምሮ የተገኘው ውጤት የረድ መደብ ይሆንና ክፍፍሉ ከእርሱ ይሰራል።

ከክፍፍሉ ቡኃላ ወራሾቹን እና የደረሳቸውን ድርሻ ስንመለከት ከሶስት አንድ ሆኖ እናገኛለን። ይኸውም:- ለወራሾቹ ያለ ቀሪ እኩል የምካፈል ሆኖ እናገኘዋለን፤ ወይም ቁጥራቸው እና ድርሻቸው የምስማሙ ወይንም የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለወራሾቹ ያለ ቀሪ እኩል የምካፈል ከሆነ ጉዳዩ ተፈጸመ። የማይካፈል ከሆነ የወራሾቹን ቁጥር ማባዣ ቁጥር አድርገን ከረድ መደብ ጋር እናባዛለን። በመቀጠል ማባዣውን ቁጥር ወራሾች ካገኙት ድርሻ ጋር እያባዛን እንሰጣቸዋለን።

የዝህ ምሳሌው:- ወራሾቹ እናት እና በእናት በኩል የሆኑ ሁለት እህቶች ቢሆኑ መደባቸው ከ6 ይሆናል። እናት 1/6 = 1 ትወስዳለች፤ ሁለቱ እህቶች 1/3 = 2 ይወስዳሉ። ቀሪ ሶስት ስላሌ መደባቸውን ወደ 3 እንመልሰዋለን፤ ምክኒያቱም ለወራሾቹ የደረሳቸውን ድርሻ ስንደምር 3 ይሆናልና። በዝህ ጊዜ እናት 1 ስትወስድ እህቶቹ ዴግሞ 2 ወስዳሉ። በመደበኛው ውርስ እና በረድ ውርስ ያገኙት ድርሻ እኩል ነው። የእህቶቹን ድርሻ ስንመለከት ለቁጥራቸው የምካፈል ሆኖ እናገኘዋለን።

| ወራሾች | 6 | 3 |
|---|---|---|
| እናት | 1 | 1 |
| እህቶች | 2 | 2 |

ወራሾቹ አንዷት ሴት ልጅ እና አምስት የወንድ ልጅ ሴት ልጆች ቢሆኑ መደባቸው ከ6 ይሆናል። ሴቷ ልጅ 3 ስትወስድ የልጅ ልጆች 1 ይወስዳሉ። ቀሪ ድርሻ ስላሌ መደባቸውን ወደ 4 እንመልሳለን። አሁንም ሴቷ ልጅ 3 ስትወስድ የልጅ ልጆች 1 ይወስዳሉ። የልጅ ልጆቹን ድርሻ እና ቁጥራቸውን ስንመለከት ልዩነት እናገኛለን። ስለዚህ የልጅ ልጆቹን ቁጥር (5ን) ማባዣ አድርገን ከመልሱ መደብ ጋር እናባዛለን፤ ይኸውም 5 × 4 = 20 ስለሚሆን 20 ማስተካከያው መደብ ይሆናል፤የወራሾቹንም ድርሻ በ5 እያባዛን በወራሾቹ ትይዩ ፊትለፊት 20 ስር እናስቀምጣለን። 5 × 3 = 15 የሴቷ ልጅ ድርሻ ሲሆን 5 × 1 = 5 ዴግሞ የልጅ ልጆቹ ድርሻ ይሆናል። ስለዚህ የልጅ ልጆቹ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ይደርሳቸዋል ማለት ነው።

5

| ወራሾች | 6 | 4 | 20 |
|---|---|---|---|
| የሟች ሴት ልጅ | 3 | 3 | 15 |
| የወንድ ልጅ ሴት ልጆች | 1 | 1 | 5 |

አንድ ሰው ምስቱን እና 14 ሴት ልጆቹን ጥሎ ቢሞት የውርስ መደባቸው ከ8 ይሆናል። ምስት አንድ ስደርሳት ቀሪው ሰባቱ ለ 14ቱ ልጆች ይሆናል። የልጆቹን ቁጥር እና ድርሻቸውን ስንመለከት የምስማሙ ሆነው እናገኛለን፤ ምክኒያቱም 7 እና 14 በ 1/7 ይስማማሉና። ስለዚህ ሁለቱንም በ 1/7 እናባዛቸዋለን። 1/7 × 7 = 1 ሲሆን 1/7 × 14 = 2 ይሆናል። ስለዚህ 2ን ማባዣ ቁጥር አድርገን ከመደቡ ጋር እናባዛለን። 2 × 8 = 16 በመቀጠል የወራሾቹንም ድርሻ በ2 እያባዛን በአዲሱ መደብ ስር በወራሾቹ ትይዩ እናስቀምጣለን። ስለዚህ ምስት 1 × 2 = 2 ስትወስድ ልጆቹ ዴግሞ 7 × 2 = 14 ይወስዳሉ። እያንዳንዳቸው አንዳንድ ይወስዳሉ።

2

| ወራሾች | 8 | 16 |
|---|---|---|
| ምስት | 1 | 2 |
| 14ቱ ልጆች | 7 | 14 |

በአላህ እርዳታ ተፈጸመ!

IslamHouse.com

IslamHouseAM/ Bengali.IslamHouse islamhouse.com/am/

channel/UC0T_q-4JkqIMTfmxa1L3kTw

For more details visit
www.GuideToIslam.com

GUIDE TO ISLAM

contact us :Books@guidetoislam.com

GuidetoIslam.org Guidetoislam1 Guidetoislam www.Guidetoislam.com


المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة

هاتف: ٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ٩٦٦١١٤٩٧٠١٢٦+ ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧

ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH

P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126

# እስላማዊ የውርስ ህግጋት

የሞች ንብረት ክፍፍል በኢስላም ውስጥ በቂ መመሪያ ያለው ጉዳይ ነው ይህ መጽሃፍ ስለዚሁ ጉዳይ ትምህርት በውስጡ ይዘዋል አንብበው ዕውቀት እንድቀስሙ ተስፋ እናደርጋለን።




IslamHouse.com
OsoulCenter
www.osoulcenter.com